ትዝታችሽን ፡ ለእኔ
ትዝታዬ ፡ ለኪነቺ

@shuktus_books

እሱባለው አበራ ንጉሤ

ሐምሌ 2012 ዓ.ም

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ

እሱባለው ካበቤ ንጉሤ

ሐምሌ ፳፻፲፱ ዓ.ም

@shuktus_books

©ትዝታዊሽን ለእኔ፣ ትዝታዊዬ ለአንቺ
እሱባለው ካበሬ ንጉሤ
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All right reserved.
© 2012/20 ዓ.ም.

የመጀመሪያ ህትመት 2,000 ቅጂ ሐምሌ ፭ሺ፲፪ ዓ.ም
ሁለተኛ ህትመት 3,000 ቅጂ ነሐሴ ፭ሺ፲፪ ዓ.ም

የሽፋን ሥዕል እና የውስጥ ገጽ ቅንብር መ·ለ·ቀን አሥራት
0913450005 / Email.mlknasrt@yahoo.com

ለአስተያየትዎ፡- esubalewabera3@gmail.com - 0940538295

ምስጋናዬን

ለልዑል እግዚአብሔር፣ ለውድ ቤተሰቦቹ ለአቶ አበራ ንጉሤ፣ ለወ/ሮ በየነች ንጉሡ፣ ለገዛኸኝ፣ ለታደሰ፣ ለአብርሃም፣ ለብዙነሽ፣ ለይርጋዓለም፣ ለወዳጆቹ ለሚስባህ ሳኒ፣ ለአቤል ዓለም፣ ለሄኖክ ኃይሌ (ዲ/ን)፣ ለሮቤል ተገኘ፣ ለሊዲያ ታደሰ፣ ለአስማማው ጥጋቡ፣ ለዘገነት በርሔ፣ ለዳዊት ካሣ፣ ለደረጀ ከበበው፣ ለመነን ገሠሠ፣ ለዳግም ታዬ (ዲ/ን)፣ ለጽዕፋር ሺፋ፣ ለሔርሜላ መላኩ፣ ለረድኤት አሰፋ ፣ ለሮማን ተወልደብርሃን፣ ለልዑል ዘወልደ፣ ለዮናስ አድማው (ዶ/ር)፣ ለምንተስኖት ከሃሊው (ዶ/ር)፣ ለዮሴፍ ጥሩነህ (ጋዜጠኛ)፣ ለዳዊት ብርሃኑ፣ ለሄኖክ ዕቀለ፣ ለአልማዝ ወርቁ እሰጣለሁ።

@shuktus_books

ለዩ ምስጋና

ለሰይፈዲን ሙሳ

ሕዋ፡

የጠፈር ባይተዋር

በመስከረም ወር በፀሐያማ ቀን ከሰማይ ማጎፀን አንዲት የዝናብ ዘለላ ተምጣ ተወልዳ ነበር።

○

ጠብታዋ በወረደችበት የጊዜ አጥቅ ላይ ሰዎች ይዳራሉ። እህሎች ያናፋሉ። ውሾች ይጮሃሉ። ጅቦች ይሸሻሉ። ንቦች ጥዝጥዝታን፤ ዝንቦች እዝእዝታን ያሸበሽባሉ። ቀንዳውጣዎች ይጎተታሉ። እቦ ሸማኔዎች ይወረወራሉ። እባቦች በየዓለቱ ይሳባሉ። ጥንቸሎች ይፈተለካሉ። አይጦች ጉድባ ይወርዳሉ። ድመቶች ኑትተው ያደፍጣሉ። ጉንዳኖች ውዳቂ አጥንት ይወርራሉ። እናብስት የሚዳ

[1] እንጀራ 1

[2] መንገድ ስጡኝ ሰፊ — ንብረ ክርስቶስ ደስታ

አህያን ያሳድዳሉ። ወፎች ለጎጆዋቸው ስንጥር ይለቅማሉ። ሸረሪቶች ድርን ያደራሉ። ወንዞች በትክክለኛ ቦይ ይፈስሳሉ። ነፋሳት ቅጠላትን ያረግፋሉ። እበቶች ትልን ይወልዳሉ። መንገዶች ጉም ይለብሳሉ። እውሮፕላኖች ገረሜ ሰማይ ላይ ከንፋቸውን ይዘረጋሉ። የጎዳና ላይ መብራቶች ያለ ውል ይቀያየራሉ። ውዳቂ ፈስታሎች በስስ ነፋስ እየተገፉ ወደ ፦ማያውቁት አገር ያርጋሉ። ጠብቀው ያልተዘጉ በሮች ያለሙቢታ ይወዛወዛሉ። በራድ ነፋሶች በየቢሉ የመስከት ደዩ ሥር ‹አንቺ ሆዬ› ያቷሟሉ። አንሺ ያጡ ስልኮች ይቅጨለጨላሉ። ተመልካች አልባ ቴሌቪዥኖች ምስል ይከስታሉ። ድካም የተጫናቸው ገላዎች ያንጎላጅጃሉ። ሕፃናት የአዋቂ ሕልምን ያልማሉ። ሽማግሌዎች እንደ ልጅ ታሸቦተው ከአልጋ በብርክ ይነሣሉ።

○

የምድር ማኅፀን የፀሐይን ምዕዛር ለመሰበሰብ እግሯን ከፋፍታለች። እንደ ብራና የተዘረጋው ሜዳ የሱፍ እበባ ወጋገንን ለብሷል። እብድ ውሻ የሰማይ አሞሮችን ጥላ ምድር ላይ ያሳድዳል። እረኞች በጎቻቸውን ለግጦሽ አሠማርተው ከዋሽንታቸው ጋር ጨዋታ ጀምረዋል። ስለከብቶቻቸው መርባት፣ ስለሸፐረቶቻቸው መጥራት፣ ስለ እዝመራዎቻቸው ማሸት፣ ስለሚዳዎቻቸውና ስለተራራዎቻቸው አረንጓዴያማነት ያዜማሉ። ቀለም የተነከሩ ቢራቢሮዎች የአደይ አበባን መዓዛ በመሻተት በሐሴት ሰክረዋል። አንዲን ቀስመው አይጠግቡም። ወደ ሌላኛዋ እየተነሙ

ይበርራሉ። ሕይወታቸው ትጽበታሚት ናት። ውበታቸውና ጉጉታቸው ግን — የዘለዓለም። የጊዜ ቀለበት ለእፍታ የገጠመ፣ ምድርና ሰማያም ለትጽበት የተሳሳሙ ይመስላሉ።

○

ከጠበታዋ ጋር ስንወርድ የምናገኘው የሱፋኒያ መስከ ላይ በጀርባው የተንጋለለውን — ‹ገ›[1] ን ነው። ጀርባውን የደረቀ

---

[1] ከጣራዎቻቸው ጉልላት ላይ ጀሬ የጣሉ እሞራዎች ሞትና ሕይወት እዲስ ቀን፣ እዲስ ምዕራፍ ይዘው የሰው ልጆችን ደጆች ሲያንኳኩ ይታዘባሉ። እንዱ ደጅ ጥሩምባ ይነፋል። ደረት ይደቃል፣ ጸጉር ይነጫል። ራሱን እጥፍጥ የነጋበት‘ጸ’ አለ። ወዲህ ደግሞ ቢላዋ ይፋጫል። ቀበቶ ይላላል፣ ይባቢው ይቀልጣል። በወይዘሪርት መካከል ተወልዶ የነጋለት አለ። የሞተው ሕይወቱን ብቻ ሳይሆን፣ ስሙንም ይነጠቃል። ተቀምሮ እንዳልተኰላ፣ ሮጦ እንዳልዘለለ፣ በለቶ እንዳልተጸዳደ፣ ጉሽ ጠላ እንዳልጠጣ፣ ለፍትውቴ እንዳላደረ፣ በመከራ ተሳክሮ፣ በተስፋ መቁረጥ ሲሸመቀቅ፣ በማማጀ እጻፋ ጨርቅ፣ እንገቱን ሲታነቅ፣ ሕይወት ሲጠናቀቅ፣ ትንፋሹ ረጭ ሲል፣ ለብታው ሲያልፍበት፣ ንላው ጸጸል የተለየው፣ ብርሃን የማይገባው ጥቁር ጸላም በድን ሲሆን፣ ሞቶ ከቤት ሲገኝ እስከሬን ይባላል።

‘ር’ የሚሏት፣ ያቺ ቀይ፣ ቀጭን ሰገበሌጥ፣ ጠንካራ እመቤት፣ በክረምት ወራት የመውለጃ ሰዓቷ ደርሶ የምትጨብጠው፣ የምትይዘው ስታጣ፣ በላብ ስትዘፈቅ፣ በግፊ ባደ ወይዘሪርቶች ተከብባ በ‘እሀ’ ታ ኪታምጥ፣ ሚች በገመድ ታንቆ፣ ዓይኑ ሲፈጥጥ፣ ጥርሱ ሲገጥጥ፣ እግሩ ሲንፈራገጥ፣ ነፍሱም ልትወጣ ከጫፍ ሲደርስ ነበር› ‘ፓ’ ሲወለድ፣ ሚች የተደበረች ነፍሱን ይዞ ከዚህ ዓለም ተሰናበተ። ከሞት በኋላ ያለውን አጽናፍ እናውቅም። እንዴት ያለ ነው? ምን አለ? ምንስ የለም? ሰዎች ስለሞት የጠረቁት ተስፋ ያደረጉትን ነገር እንጂ ያዩትን እውነት አይደለም። ዛሬም ድረስ የሞት ሬቱ በውል አይታወቅም። ኪሕይወት በላይ ምሥጢራዊ ነው። እኛ ግን በሕይወትና በሞት መካከል ስለተዘረጋው ቀጭን ክር እንተርካለን ። እንመላለሰለንም።

ወዲህ ስንመለስ ሕፃኑን ከእናቱ ከ‘ር’ እቅፍ ላይ እያለቀሰ እናገኘዋለን። ከመወለዱ ሰምንት አስቀድሞ ድርጊቶች በሊምንትኛ ተዘገረዋል። ነገር ግን ያንን የተረዳ፣ ያስተዋለ ሰው አልነበረም። ከሚዳሩ ሰዎች ራስ እንዳንድ ዘለላ ጠጉር ረግፏል። የዶሮዎች የጎጋት ብሥራት ድምፅ በድገነት ሰልሏል። የዝንቦች ከነፍ ተበጥሶ ወድቋል። የጉም ጭጋግ ተበትኖ

አከርማ ይኮረኮረዋል። እጆቹ ግራና ቀኝ ተዘርግተው ሳምሳም ሣር ይዳብሳሉ። በግድ የለሽነት አመልማሎ ሰማይ ይመለከታል። ለጋ ደመናዎች እዚህና እዚያ ይሽከረከራሉ። ሙዚቃ እነኚ ተቀረጸባቸው ሸክላዎች አየር ላይ ሰፍፈው ምድርን ይዘራሉ። ዓኒ እይታው ይገባሉ። ከዚያም ይሠወራሉ። ልቡ፣ መንፈሱ፣ አነሱ ወደ የሚያውቀው፣ ወደ ተረዳው፣ ደግሞም ወደ ነማያውቀው፣ ወደ አልተረዳው ሥፍራና ረቂቅ ትላንት ይንቀሳቀሳል። ሐሳቡና ግንድ ትውስታዎቹን ተደግፈው አንጎሉ ውስጥ ያናውዛሉ።

○

የግጥምን ተፈጥሯዊነት፣ የትያትርን የመድረክ ዓለምነትንና ውስንነት፣ የፊልምን እውነተኛ ነጸብራቃዊ ብርሃንነት፣ የሥዕልን — ከሥዕልም በላይ ሠዓልያን ለሥዕሎቻቸው የሚሰጡትን መጠሪያ ርእሶች፣ የቤተ መጻሕፍትን ጸጥታና የአሮጌ መጻሕፍት

ጠፍቷል= ውኃ ወደ ላይ ፈስሷል። እሞራና ቅል ተጋብተዋል። የሰው ልጆች ሕልም በብዙኃ ተጠቅቷል= ከእናቱ ማኅፀን ተጎትቶ ሲወጣ ወደ ሕሊናው ማሕደር የቅዠት ናዳ እንደ ፉር ጨርቅ ተመዝምዟል። ጩኸቱን ለቅቆታል። እኮ ሲወለድ ለምን አለቀሰ? ለምን 'እረ' አለ? በእናቱ ማኅፀን እያለ የደረሰበት ግፍ ስላለ ነው? ወይስ ሲወለዱ ማዶቀስ ወግ ስለሆነ? 'ግ' በውልደቱ ቀን ለሞቱና እየሞቱ ላሉ የሕይወት አካላት ነበር እነባውን የዘራው= 'ሮ'ን የከበቧት እዋላጅ ባለቴቶች፣ የ'ጎ' ን ለቅሶ አጅበው ፈንጠዝያ ያዙ፣ ውስ ረገጡ= 'እለለ እለልለ፣ አሰይ እሰይይይ፣ ቱ ቱ ቱ' አሉ – ከዓይን ያውጣህ እንደማለት= ስንት ቡዳ አለ?

'ግ' የተወለደው በዚህ መንገድ ነበር።

ሽታ፣ የተርታ መንገደኞችን ጨዋታና ፈገግታ፣ የሰግይን ሰግያዊነትንና ጨለምታ፣ የውኃን ንጽሕናትና ተለም አልባነት፣ የተራራና ኮረብታን ጠጣርነትና በድንነት፣ የሸንተረርና የእረንጓዴ ሚዳን እውላላነትና ሕያው ሽራነት፣ የእርጥብ አፈር ሽታንና የበረዶ ገነናምን ሐሜ ከምር፣ የወተት በቡና አረፋን በማንኪያ መስፈር፣ መኪናዎች በፍጥነት ሲያልፉ የሚያሰሙትን ሽውታንና የጊዜ በራሪነት ማየት፣ የዝናም አውታሮች በጣሪያ ላይ ሲወርዱ የሚያሰሙትን መንጠባጠብ መስማት፣ የመካነ መታብሮችን ጸጥተኝነትና የሰውን ልጅ አላፊነት ማሰብ፣ የሴት ልጅ ገላ ላይ ያለን የግርያም ስመትና የከንፈር እንትስታሴን መታዘብ፣ የመስኮትን አሻጋሪነትንና ተካፋችነት፣ በቱሜሮን ቀዳዳዎች ሾልከው የሚገቡ የብርሃን ነዶዎችን መመልከት ይመስጡታል።

○

የሕፃናት ጫጫታን፣ የሰዎችን ስብስብና ጋጋታን፣ የማያልቅ ሐሜትንና ሹክሹክታን፣ የማስመሰል ላቅንና እምንታን፣ የዚህ እገር ፖለቲካን፣ የጦር መሣሪያንና የጦር ወሬን፣ ቴሌቪዥንንና ራዲዮ ላይ የማይጠፉ ታዋቂ ሰዎችን፣ የአምቡላንስ ዋይታን፣ ድንቁርናንና ኋላ ቀርነትን፣ የግለሰቦችን ራስ በራስ እምላኪነት፣ ገደብ ያለፈን ቁሳዊነት፣ የታይታ ጻድቆችንና ራእይ ቢስ ሐዋርያትን፣ ከእኔ በላይ እናውቅልሃለን ባይ ሰባኪዎችን ይጠላል። ደረቱ ላይ 'እሳት ወይ አበባ' የሚል እሮጌ መጽሐፍ ተጋድሟል። ሽፋሽፍቱን እየከደነና እየገለጠ የካንሳስን 'ደስት ኢን ዘ ዊንድ' ከስልኩ ያደምጣል።

‘I close my eyes

Only for a moment, and the moment’s gone

All my dreams

Pass before my eyes, a curiosity’[4]

○

ዕድሜው ሁለቱ እንደማይሻገረው የወንዝ ውኃ ይወርዳል። ዘመኑ ከሸማኔ መደወሪያ ይልቅ ይፈጥናል። ቀኖቹ ግን የተደገሙ ያህል ተመሳሳይ ናቸው። ሰዎች ልጅ ወልደው ሊጥሉ፣ ግደያ ሊያሳድጉ፣ ቀሚስ ሊገልቡ፣ የታረዘ ሊያለብሱ፣ ሕሊና ሊያደሙ፣ ቂስል ሊያጠግጉ፣ የቆመውን ሊዘረጥጡ፣ የወደቀውን ሊያነሡ፣ ሊመዘብሩ፣ ሊመጸውቱ፣ እምነት ሊያጎድሉ፣ ባህል ሊጠብቁ፣ ብሉን ሊያጠፉ፣ ዓይን ሊሰግሱ፣ ሰው ፊት ላይ እንቅረው ሊተፉ፣ የተበዳይ እንባን ዝቅ ብለው ሊያብሱ፣ ሠርተው ሊያገኙ፣ ዘርፈው ሊከብሩ፣ ወጥመድ ሊያበጃጁ፣ ጥርጊያውን ሊያቀኑ፣ አሳልፈው ሊሰጡ፣ ሸሽገው ሊያስመልጡ፣ ሊያገላግሉ፣ ሊያቀያይሙ፣ ከወገብ በላይ ታቦት፣ ከወገብ በታች

[4] ዓይኖቼን ስጨፍን በቅጽበት ይጠፋል የጊዜ እፍታ
ሕለሜም እያየሁት በንጉት ይቀራል ያለፋል ሳይፈታ (የትርጉም ቅርበት)

ጣዖት ሊሆኑ. . . ከትላንት የቀጠለ ሌላ ዕለት። ተጨማሪ ንጋት። የሸኘነው ቀን ካለንበት ዛሬ በምን ይለያል?

○

ወግ አያተርምና ሲነጋ ግን አዲስ ቀን ይባላል። መሽቶ ሲነጋ የአገሩ ገበሬዎች እጆቻቸውን አንከርፍፈው፣ ወደ ሰማይ እንጋጠው ፈጣሪን ያመሰግናሉ። ካህናት በቤተ ማቅደስ ያቀርባሉ። መስጂዶች አዛን ያሰማሉ። አማኒያን ውዱህ ያደርጋሉ። ሶኋት ይሰግዳሉ። ቁርአን ይቀራሉ። መሽቶ ባይነጋ ምን ይፈጠራል? እንደነጋ ቢቀር፣ የ‘ገ’ ሕይወትና ዕድሜ በአንድ ወጥ ዕለት ቢያልፍ? ጊዜውን እንዴት ይከፋፍሉዋል? ከትላንት ወዲያ፣ ትላንት፣ ነገ የሚባሉ የጊዜ አጥቆች ባይኖሩት? የሕይወት ታሪኩ በአንድ ቀን ቢጠናቀቅ? ሁሉም ዛሬ ቢሆን፣ ፅንሰቱ፣ ውልደቱ፣ ሕፃንነቱ፣ ጉርምስናው፣ ወጣትነቱ፣ እርጅናው እና ሞቱ ዛሬ በዛሬ ቢሆኑ ምን ይፈጠራል? ልቡና ትከሻው እነዚህን ሁሉ እካላዊና ስሜታዊ መለዋወጦች በአንዴ ማስተናገድ ይችላሉ? የመሽቶ መንጋቱ ጥቅም የመቻል ትከሻን ማስፋት እንደሆነስ? እንኪማ አዲስ የፀሐይ አወጣጥ፣ አዲስ ምሥራቅስ የታለ? ...እና ይሄ ውደት የጥንት ነው። ፀሐይ እንዲህ ስትጠልቅ ስንት ትውልድ አልፏል? ስትወጣስ ስንት ትውልድ መጥቷል? ሁሉ ነገር ዘመን ከተቆጠረለት ጥንታዊ ነው። ጊዜ የበረረውን ያህል የትዝታ ባሕር መዝገብም ይደልባል።

○

[5]የትዝታን ፈረስ በምን ‘ቺ’ ይሉታል? ወዲህ ወዲያ ሲሞልል የምናየው እሮጌ በር ‘ቺ’ አያስብልም? ዝገቱና ንትናቴው ከሕይወታችን አንዱ ሰበዝ ጋር በሆነ መንገድ ቢዛመድስ? የአሮጌ በር መቀርቀሪያ... ማስታወስ ከማንፈልገው የከፉ ሰው ትዝታ ጋር ቢዛነቅስ? እንዲያው በባዶ ሜዳ ‘እህህ’ እያልን መቅረታችን አይደለምን? በዚህ ትዝታ ስንረታ ለስንተኛ ጊዜ ነው? በልጅነት የቀመስናቸው ኩርኩሞች በጉልምስናችን ሲታወሱን... ሞች ሳሳ ይላሉ? የትላንቱ ጥንካሬያቸው ዛሬም ባለበት አይደለ?

○

ማንን በምን እናስታውሳለን? የእንቅስቃሴዎች፣ የጠረኖች፣ የቀለማቶች፣ የድምፆች፣ የግዑዛን ቅርጾች ውልብታ ጣፋጭ ወይም መራራ ትዝታን ይቀሰቅስብናል። ትዝታ ከየት እንደሚነሣ በውል እንደማናውቀው ነፋስ ነው። ሲደርስብን እንደ ስጥ እንበተናለን፣ እንተራመሳለን፣ እንረበሻለን። ለትዝታዎቻችን ያለን ስሜት እንደምናስታውሰው ነገር ይወሰናል። ምናልባት እንፈግጋለን፣ እንኳሻለን፣ እንተክዛለን፣ እንናፍቃለን፣ እናለቅሳለን፣ እንቆጣለን፣ እንመረራለን። ያማረ ትላንት ለሌለው

[5] ማቢያ 1

‘ን’ን አማሃይ ስፍራ ላይ ብናቆመው ትላንቱን፣ ዛሬውን፣ ነገውን የምናገናኛቸው ቱቦ ብሎ በሚጓዝ በአንድ የጊዜ መሥመር ላይ ነው፣ እርሱ ያለፈውን እንጂ የሚመጣውን አያውቅም። እኛ ግን እናውቃለን፣ ‘ያ’ እርሱን ሰው ሲያደርገው እኛን ደግሞ ፈጣሪ ያደርገናል። ያለፈውን በማውቁ ውስጥ በደማችም በነፍሱም ትላንትን እያንዣ እንዲኖር ተረግሟል። ታካቱት ቢረሳም በግድ እንዲያስታውስ ይደረጋል። ፈልጎ አይደለም። የትዝታ ድንገተኝነት ልክ እንደ ትንታ በመሆኑ ነው። ማንነቱ እዚህ ላይ የደረሰው ትላንትን አንድ ብሎ ነው። እና ምንም ያህል ቢሞክርም፣ ትላንቱን ፈጽሞ መካድ አይችልም። እዚህ ሲደርስ — እዚህ ያደረሰው፣ እንዲህ ሲሰማው — እንዲህ እንዲሰማው ያደረገው፣ ሲንኮታኮት — ያሸቀነጠረው፣ ሳያምን ሲቀር — የከዳው፣ ሲፈራ — ያስደነገጠው፣ ሲያለቅስ — የመታው፣ ሲስት — የኮረኮረው አለ። ውጤት ካለ መንስዔ አለ። ትላንት የሌለውን ዛሬ ያየ ማን ነው?

○

በቅርቡ ወደ ካምፓስ ይመለሳል። እዚያ የአገሩ ልጆች ሊገድሉት ይፈልጋሉ።

ሰው ትዝታ ምንድር ነው? የሚያጥመለመል፣ እንቅልፍ የሚያሳጣ፣ ልብን የሚያነብድ፣ ጎዘን ላይ የሚጥል ቸሸታ አይደለምን?

@shuktus_books

መዲናና ዘለሰኛ[6]

ለኔ መቶ መረጥከኝ ለብቻዬ እንገርገር?[7]

አባቱ እዚህ የገጠር ጥግ ይወለድ፣ ከከተማ ይምጣ ለይቼ አላውቅም።

○

ከታላት ጋር እንደማይተዋወቅ ሰው ነው። በቢት ውስጥ አያወራም። በረንዳ ላይ አይናገርም። በራምቹን ጠምዶ ሲያርስ — 'ምሽ' አይልም። ጀርባቸው ላይ ጅራፍ አያማታም። የእግር አጣጣሉ እንደ ላባ ይወድቃል። በከረምት ጨፌ ሲራመድ የረገጠው ምድር አይሰረጉድም። አገራሩን ሲፈታ አያፏሽክም። በርጩማ ላይ ሲተመጥ 'እንዘጭታ' የለውም። ማዕድ ቀርቦ

[6] እንጀራ 2
[7] ደበቃኛል—ግርማ በየነ

እጆቹን በገበቱ ሊታጠብ የመፋተግ ድምፅ አይመጣውም። በዝምታ የአፈር ቅራሪ ይፈስሰዋል። ሶጋ ጣቶቹ ላይ ሪዙ እንደ ጥቁር ጥጥ ይፍተለተላል። ዓይኖቹ ውቅያኖስ ላይ እንደሚንሳፈፉ ቅጠላት ይንከላወሳሉ። አብገዙ ይጠግባል። ወደ ሰማይ ያንጋጥጣል። ለመከፈልት ሊቀርብ እንጀራ በትህትና ይቅርሳል። ወጥ በኪነ ጥበብ ያነካካል። ለነፍሰ ሥጋ ማቆያ ያህል ይመገባል። ሲያኝክ እያላምጥም። እያጣጥምም። ሲያዛጋ እያጓራም። ማሾ ሲያጠፉ 'እፍፍ' ታ የለውም። የዶሮ እንትልፉን ከመደቡ ላይ ሲተኛ እይገላበጥም። እያንኮራፋም። ሆዱ እያንቋርርም። ሲያመው እያቃስትም። ሲበርደው 'አት-ት' አይልም። ጥርሱን እያፏጭም። መዝጊያ ሲከፍት ያስታምማል። ጀምበር ስታዘቀዝቅ ጸዊት በለሆሳስ ያምበለብላል። ሌሊቱን ይሰግዳል። ይወድቃል። ይነሣል። መጽሐፈ መነኮሳት ያነባል። መቋጠሪያውን ይደባብሳል። የለንበት ተሲያቱን ከቡላ ፈረሱ ጋር ያሳልፋል።

○

'ጋሼ በርጩማው ላይ የእውነት ተቀምጠሃል?'

'ጋሻ መሬትህን ሰቅስቀህ አርሰሃል?'

'እጅህን ግን ታጥበሃል?'

'ቀኝ እጅህ ምን ሆኗል የተኮማተረው? በርዶታል?'

'እንጀራው ነፍስ አለው? የምትጠነቀቅለት'

'ወጡስ ሕዋስ አለው? በደምብ የማትጠቅሰው'

'እየተራመድክ ነው እየተንሳፈፍክ?'

'መደብህ ላይ ተንደባለሃል?'

'ለመሆኑ ክብደት አለህ?'

'ከእናቴ ጋር ለምን በአንድ አልጋ አትተኛም?'

'በምድር የሠራኸው ኃጢአት እኔ ነኝ? እኮ ለምን ትጸየፈኛለህ?'

‹እስኪ ፈረስህን ስትጋልብ ልይህ? ቡራት[8] ነው ይበርራል?›

‹እስኪ ድምፅ አውጥተህ ዳሮት ድገምልኝ?›

‹ሰውዬ እታወራም? ዲዳ ነህ?›

መጠየቅ እፈልጋለሁ።

○

አባቴን የማውቀው በሦስተኛ ወገን — በእናቴ በኩል ነበር። የዝምታ ደብር ነው። ተራራ ላይ ወጥቼ በአንከሮ አድምጫለሁ። እምባ ላይ ዓይናቼን ጨፍኜ፣ ጆሮዬን አቁሜ ከእርሱ ጋር የሚስተካከል አርምሞ ፈልጌያለሁ — አላገኘሁም። አካል የለበሰ ጽሞናው ይጨንቀኛል። መኖሩ ይከብደኛል። ጭምትነቱ ቢታችንን ገዳም ያደርገዋል። ገረገራውን ሲያልፍልኝ[9] ከነመፈጠሩ ጨርሼ እዘነጋዋለሁ። አባት አልባ እንዳልሆንኩ ትዝ የሚለኝ

[8] ከገፋም ፈረስ

[9] ከቤት ዘወር ካለ መስክ ነው። እርሻውን ያያል። የሚታረመውን ያርማል። አትክልት ይኮተኩታል። ርቆ ከከተማ አይወጣም። ከሰው አይገናኝም።

ከመስክ ተመልሶ በአንድ ጣሪያ ሥር ስንገናኝ ነው። እስከዚያው ‹ዓለም ላይ ማን ማን አለ?› ብባል ‹እኔና እናቴ ብቻ› ስል እመልሳለሁ። አባቴ በፎቶ ግራፍ ላይ እንዳለ ነፍት ቦታ ነው። አለም፣ የለምም።

○

በልጅነቴ ተራራ ወጥቼ በወረድኩበት አንድ ቀን እናቴ ጋቢዋን ደርባ በረንዳ ላይ ቆማ ትጠብቀኛለች። የዚያን ቀን የተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ መከራዬን በልቻለሁ። የውስጥ እግሬ ቆስሏል። ከንዶቼ ተገሽልጠዋል። ጣቶቼ ነደዋል። የደረስኩት ጀምበር አዘቅዝቃ ነው። እናቴ ፊት ፊቴን በቅያሜ ታየኛለች። አመድ ለብሻለሁ። የሰውነቴን ቅጽር ከጀርባዬ የሚመጣው ሰማያዊው የምሽቱ የጨረቃ ብርሃን ወርሶታል። ገላዬ በኪርሽ እንደተጠለፈ ዳንቴል ብርሃን ያሳልፋል። ነፍሴ የደከሙች ሰውነቴ ውስጥ ነፋስ እንደሚያንገላታት የላምባ ብርሃን ወዲህ ወዲያ ትነፍሳለች። እንደ በረደኝ፣ እንደ ራበኝ አስታውታለሁ።

‹የት ነበርህ?›

ማዶ ማዶውን እያሳየኋት

'እዚያያያ የተራራው ጫፍ ላይ'

'ተራራ ለተራራ ደግሞ ምን ታደርጋለህ?'

'ፍጹም ጸጥታ ፈልጌ'

'ተራራ ላይ ፍጹም ብቸኝነት እንጂ ፍጹም ጸጥታ የለም'

ትለኛለች።

○

ከምንም በላይ ብቸኝነትን አውቃለሁ። ዕድሜዬን በአራት ግድግዳና በአንድ የተደፋ ክላድ ሥር እንዳሳለፍኩ ይሰማኛል። በዓለም ላይ ስንትና ስንት ሰዎች አሉ? ስንትና ስንት አገራት ካርታ ላይ ሰፍረዋል? ...ሰባት ቢልየንና ከዚያ በላይ ሰዎች ይኖራሉ። እኔ ግን በዓለም ውስጥ እንደ ብቸኛ ሰው ነበርኩ። ልገልጻቸው የማልችላቸው ስሜቶች በደም ሥሬ ይርመሰመሳሉ። ደም ሥሬን በስል ምላጭ በጥሼ በሁለመናዬ የሚዘዋወረውን ድብርት ስለማፍሰስ አስባለሁ። ከሕይወት ወጥመድ በምን ይመለጣል? ሰው ከመሆን የሚታረፍበት ሌላ መንገድ የት

አለ? ...የሚሰማኝ ሰው መሆን ከባድ እንደሆነ ነው —በተለይ እኔን መሆን።

○

የነፍሴን ስርቅታ በጉያዬ ታትፌ ጎብረ ሰማይ እመለከታለሁ። እንደ ጥሎር ግምጃ በተንጣለለው ሰማይ ላይ ከዋክብት ፈሰሰዋል። በእኔና በከዋክብቱ መካከል በሚልየን የሚቆጠሩ የብርሃን ዓመታት ይኖሉሳሉ። የማያልቅ ሰማይ፣ ብትን ከዋክብት፣ ሽራፊ ጨረቃ ለከፋው ሰው ምንድር ናቸው? ማግር እንጂ ማሰብ በውስጣቸው የለም። ከዋክብት የታከተን ገላ አያቅፉም። አመድ ለብሶ የተረሳን ከንፈር 'እፍፍ' ብለው ትቢያውን አራግፈው በፍቅር አይሰሙም። ውስጡ በሐሳብ ስርዝ ድልዝ የተሞላን የራስ ጠጉር በጣቶቻቸው አያሻሹም። ደረት ሃት ነው — ጨረቃ እንጎል የላትም። ከከዋክብትም እንደ አንዱ አይደለሁም። ሕይወቴ ብርሃን የለውም። ወደ ውስጤ ስመለከት ድቅድቅ ጨለማን አያለሁ። ያልታከተኝ ውበት ምንድር ነበር?

'አባቴ ይወደኛል?'

'ፈልጎ ነው የወለደኝ?'

‹ስታምጪ አብሮሽ ነበር?›

‹ልጅ እንዳለው ያውቃል?›

‹ጠይምነቱን፣ ጠጉረ ከርዳዳነቱን፣ ልከኛ ቁመታምነቱን አይቷል?›

‹እርሱን እንደምመስል ይረዳል?› ብዬ እናቴን በተራዬ መጠየቅ እፈልጋለሁ። ይደከመኝና አተወዋለሁ። ያደግኩት የራሴን ድምፅ እንደ ገደል ማሚቶ ተጋጭቶ ሲመለስ እያደመጥኩ ነው።

‹በሰማይ ድምፄን የሚሰማ አለ?›

‹በምድርስ ሕመሜንና ሥቃዬን ማን ያደምጣል?›

○

...እያልኩ አውላላ መልካ ላይ እጮሃለው። ቃላቶቼ — ሸንተረሩን እየተንከባለሉ ይወርዳሉ። የሸለቆውን ሥርጥ ያካልላሉ። ከወንዝ ውኃ ጋር ይፈስሳሉ። ከቆሸሹ ልብሶች ጋር

በእንዶድ ይታጠባሉ። ከዓለት ጋር ይጋጫሉ። ከጥየል ቆዳ ጋር ተፍተው በሐይ ላይ ይሰጣሉ። እንደ ደበሎ ይለበሳሉ። እንደ ጠፈር አልጋ ይዘረጋሉ። ከሞኔ ጋር ክንፍ አውጥተው ይበርራሉ። እንደ እፅዋት ቅጠል አፈር ላይ ይበትላሉ። በቀሞኔ ይተነጠላሉ። በግመል ከርሰ ያድራሉ። ተተፍተው ዳግም ያመነሽጋሉ። እንደ ጢስ በንነው ያርጋሉ። አርያም ይነጠፋሉ። ጨረቃን ይረግጣሉ። ፕላኔት ለፕላኔት ይንከራተታሉ። በደመና ሆድ ይረገዛሉ። ወደ ምድር ተመልሰው ይዘንባሉ። በአጋሰስ ይጠጣሉ። በውሾች ይሸናሉ። ከርሰ ምድር ይሰርጋሉ። እንደ ሰው እግር በጋሬጣ ይዘነጠላሉ። እንደ አህያ ሥጋ በጅብ ይነከሳሉ። ውቅያኖሱን እንደ መርከብ፣ እንደ ታንኳ እየቀዘፉ — ከተማ ይገባሉ። ወደብ ይሻገራሉ። ድንበር ያቋርጣሉ። ሰሚና አለሁ ባይ ፍለጋ ሁሉም በታ ነበሩ? ወይስ የትም አልነበሩም?

○

እናቴን ከጓላዋ ተከትያት እገባለሁ።

[10]ሕይወት እንደ ፈጠራ ድርሳን ወጥ ምስልን አትሰጥም። በሠመረ ምክንያትና በተዋጣለት ድርጊት አትሰናሰልም። በትርጉም መፋለስ የተላለቆና የተጣጡ ሰዎች በእውነተኛው ዓለም በስተመጨረሻ አይገናኙም። ወደ አንድ መሥመር አይመጡም። አይገነዛዘቡም። አስተያየት የሚያደርግላቸው ሁሉን አወቅ ደራሲ አያገኙም። ግንኙም ለማስደሰትና ለማሳዘን አይደለም። ሕይወት ገለልተኛ መድረክ ናት። የባለወንጭፉ ዳዊትን ገድል ለማሳመር ብላ የባለ ስል ሰይፉ ጎልያድን ገድል አታበለሻሽም። ትዕይንቱ በተዋናዮቹ ኢምፕሮቫይዜሽን ይወሰናል። እስኪ የሕይወት መድረክ ላይ ወጣ ብለህ ስንት ዳዊቶች በአንድ የጎልያድ ሰይፍ እንደ ተገደሉ ቁጠር?

○

ሰዎች በሚያነቡት ምንባብ፣ በሚያዩት ቅርጽ፣ በሚያደምጡት ድምፀት ውስጥ የማያቋርጥ የትርጉም ጎሰሳን ያደርጋሉ። ምክንያታዊነትን ያጠይቃሉ። ሕይወት ላይ ግን 'ለምን እንዲህ ሆነ? ለምንስ እንዲያ አልሆነም?' ብለን መጠየቅ አንችልም። ከአልተመለሱልን ጥያቄዎች ጋር እንጓዛለን። ምክንያቱም ምድር

[10] ማቢያ 2

ላይ የታዘነው ሕይወት እንጂ ተውኔት አይደለም። የተሰጠን ቃለ ተውኔት የለም። ወደዚህ ምድር ስንመጣ የሕይወትን ትርጉም የያዘ ኑታብ በእንገታችን አሥረን አልተወለድንም። ምስኪኖች ነን። የገባ ታሪካችን ፍሰት የቱ ጋር እንደሚያበቃ አናውቅም። በዘፈቀደ ከምንኖረው ሕይወት፣ እንደ ቅሪላም ከምንገፋው ኑረታችን ያማረ፣ የተመጠነ፣ ስሜት የሚሰጥ ምልው ተረክ እንጠብቅም። ሕይወትም 'ከየት መጣን? ወደ የትስ እንሄዳለን?' ለሚል ብሱይ ጥያቄያችን የተሸሞነሞነ ትርጉም የመስጠት ግዴታ የለባትም። ምን አልባት እንዲት ብርትካናማ ሚኒስከርት የለበሰች ጠይም ፍልቅልቅ ሕፃን በውኃ በተብጣ በትንፋሷ 'እፍፍ' ባለችው የዐረፋ ኳስ ውስጥ ድንገት የተከሰትን ፍጡራኖች ነን። የዐረፋ ኳሱ አየር ላይ ሰፍፎ ሲፈነዳ ዘለዓለማዊነታችንም ተበትኖ ይጠፋል። እኮ ማን ያውቃል ህላዌያችን እንዲህ ባሉ ትርጉም በማይሰጡ ቅጽበታት እንደ ተከበበ?

○

ስለሕይወት መልከ ወርደን ስንጠይቅ ...ስንት ሻሂ፣ ስንት ቡና ጠጣን? ስንት ሲጋራ አጢሰን ስንት ቢራ ጨለጥን? ስንቴ በሰዓት ደርሰን ስንቴስ አረፈድን? ስንት ሳቆች ስቀን ስንት ፈገግታ ፈገግን? ስንቴ ተደብረን ስንቴ ጎዘን ገባን? ስንት ጨለማ አይተን ስንት እንባ አነባን? ስንት ሰው አወቅን? ስንት ሰው ጠበስን? ስንት ሰው ተኳርፈን ስንት ሰው ታረቅን? ስንት ሰው ጨብጠን ስንት ሰው አቀፍን? ስንት ሰው ሸኘተን ስንት ሰውስ ገፋን? ስንት ሰው ወደድን ስንት ሰውስ ጠላን? ስንት ሰው አፍቅረን ስንት

ሰሙስ ተኛን? ስንቱን ገላ ዳብሰን ስንቱን ተዳዳ አየን? ስንት ሴ
ፈሙሰን ስንት ሰው ገደልን? ስንት ሰምች ሰብረን ስንት ሰ
ጠገንን? ስንት ሰው አስቶን ስንቱን አስለተስን? ...ብለን ነው
ከዚህ ሌላ የምናወራርደው ሒሳብ የለብንም። የሕይወት መልክ
ያለው መዘርዝሩ[11] ውስጥ ነው።

○

አጥብቀን አሥረነው የተፈታብን የጫማ ክር የለም? ፈትፍን
ሳንፈታው እንዴት በራሱ ጊዜ ደጋግሞ ተፈታ? ቆም ብለን
የአፈታቱን ሂደት ማወቅ አንፈልግም? ሕይወት የጫማ ክራችን
በተፈታበት መንገድ ቢሆንስ ለእኛም የምትሠራው?

[11] In its details

አሞራ[12]

ዘቀ ያለ ከምደር

በልጅነቴ በየሄድኩበት መንገድ በሰማይ እያንጎበጎበ እንደ ጥላ የሚከተለኝ አንድ ጥቁር አሞራ ነበር።

○

ስደበት እንደማደርገው ሜዳውን ለሁለት ከፍሎ ወደሚፈስሰው ወንዝ ወረድኩ። ውኃ የጠገቡ ጠጠሮችና ሞላላ ድንጋዮች የወራጁን ዳርቻ ተከትለው ከአሸዋው ጋር ፈስሰዋል። ወንዙን ተሻግሮ አራት ጥቁር በነጭ ከሲታ ጥጃዎች ሰተት ያለ ሜዳ ላይ ተጋድመው ፀሐይ ይሞቃሉ። ሙጃ በትቷቸዋል። በላያቸው የትንኝ መንጋ ያንበገባል። ከብቶቹ ከእፋቸው እንትስታሌ እርስ

[12] እንደራ 3

በእርሳቸው የሚያወሩ ይመስላሉ። ካለሁበት ርቀት አንጻር ግ
ድምፃቸው አይሰማኝም። ከጆሮዬ አይደርስም። መዳፌ ላይ
መጠነኛ ቅሰት ያላቸውን ሦስት ጠፍጣፋ ነጫጭ የባልዲቂት
ድንጋዮችን መርጬ ከመሬት አነሣሁ። እየወረወርኩኝ፣ ቀለብኩ፣
እየቀለብኩኝ፣ ወረወርኩ። ከግይቤ እርቆ በተኛ የውኃ ሰገነት ላይ
ሁለቱን ድንጋዮች እፍታ እየሰጠሁ እያነጣጠርኩ የአግዳም
ወረወርኩ። የአነጣጠራቸውን ብዛትም ከጠለሉ ያማረ ተረተር ላይ
ቆጠርኩ። ከብቶቹ የውኃውን መገቦጫረቅ ሰምተው አልዘሩም።
ግድም የሰጣቸው አልመሰለኝም።

‘ታ! ታ! ታ! ታ!’

‘ታ! ታ! ታ! ታ! ታ!’

○

ድንጋዮቹ ሄደው፣ ሄደው ወንዙ ውስጥ ይጠልቃሉ። ከእይታዬ
ሰጥመው ይሠወራሉ። ሦስተኛውን ድንጋይ ልወረውር አሰቢ እኗ
እንዳነሣሁ ድርጊቴ ትርጉም አጣብኝ። ሰውነቴን ከየት እንደመላ
ያልገባኝ መሰልቸት ተቆጣጠረኝ። መንፈሴን አንዳች ነገር
ከበደኝ። ማረፍ ፈልጌ ፊቴን ከወንዝ ውኃው መለስኩኝ። ስዞር
በዓይናቹ ትይዩ ሣር ሚዳው ላይ የምስጥ ሰራዊት የሚበላው፣
ፀሐይና ዝናብ ተፈራርቀውበት ቢጫነትን ያገሥ የግንድ ጉማጇ

ተተምጧል። እርሱ ላይ ካረፈ ጥሎር አሞራ ጋር ዓይን ለዓይን
ተጋጨሁ። አትኩሮ በትዝብት ዓይን ሲያየኝ ከቆየ በኋላ
የማስካካት ድምፅ አሰማ። ከንዴን እወናጭፌ በእጇ የያዝኩትን
የመጨረሻ ድንጋይ ወረወርኩበት። ባልጩቷ እየተምዘገዘች ሄዳ
እሞራውን ቀንድባ ጣለችው። በዚያን ቅጽበት በሕይወቴ
ለመጀመሪያ ጊዜ በሥጋ የተደንሰች ነፍሴን ሀልዎት
ተጠራጠርኩኝ። ነፍሴ ኮብልላ ስትጠፋ፣ በቁሜ ስሞት፣
አለመኖር ሲወርሰኝና ከውስጤ አንዳች ነገር ሲጎድል ተሰማኝ።
የማላውቀው ትላንቴን ወይ ገና ያላየሁት ነገዬን እንዳያበላሽብኝ
ፈራሁ።

‘ታ!’

ድርጊቴ ንቃት የተለየው ነበር። አላሰብኩበትም። በሕሊናዬ
የሐሳብ ሕዋስ ስሌት አልተሠራበትም። ቅጽበታዊ ነው።
በተለምዶው እንዲህ አልነበርኩም። አልቀለጣጠፍም። ቀርፈፍ
ያልኩ ነኝ። ደንግጬ አሞራው ወደ ተፈነገለበት አቅጣጫ
በፍጥነት ሮጥኩኝ። ደርሼ ስመለከት ድንጋዩ ከመሣሪያ ምላጭ
ተስቦ እንደ ተተኮሰ ቀልሃ ጭንቅላቱን በርቅሶታል። ባልጩቷ
የወደቀችበት ሣር በደም ተለውሷል። ከው አልኩኝ። ለምን
እንዳደረግኩት አላወቅኩም። እጆቼ ይንቀጠቀጣሉ። ድርጊቴ
የተቀዳበትን የሰሜት ባሕር አልደረስኩበትም። ምስጢቹ ከነበሩበት

[13]የተቀባበሉ ጥይቶች ነን። እንደምንተኮስ እንጂ ግንን እንደምንመታ በውል አናውቅም። ስንወረውር — የምንመታውን፣ ስንሮጥ — የምንደርስበትን፣ ስንመርጥ — የመረጥነውን፣ ስንፈልግ — የፈለግነውን፣ ስንቀርብ — የተጠጋነውን፣ ስንወድድ — የወደድነውን፣ ስናፈቅር — ያፈቀርነውን፣ ስናምን — ያመነውን፣ ስንሸር — የሻርነውን፣ ስንሾም — የሾምነውን፣ ስንጠላ — የጠላነውን፣ ስንጋጭ — የተጋጨነውን፣ ስንጠልፍ — ያነቀፍነውን፣ ስንገድል — የገደልነውን አናውቅም።

[13] ማቢያ 3

አልተንቀሳቀሱም። አልተረበሹም። ከግንዱ ፈቀቅ አድርጊ ከዛፍ ላይ ተሰብሮ በወደቀ የደረቀ ቅርንጫፍ አፈር ምሺ በዝምታ ቀበርኩት። ራሴን አልነበርኩም። ከአሞራው ከንፍ ላይ ተነቅላ የወደቀች አንዲት ጥሩር ላባውን ይዤ ወደ ቤቴ በረርኩ። ሌሊቱን ራሴን አንድ ጥያቄ ደጋግሜ ስጠይቅ አደርኩኝ። 'ወደ ምንነት ነው የመጣሁት? ወደ ምንነት ነው የተቀየርኩት?'

○

ጸጸቱ እያደር አልቀለለኝም። አልከበደኝምም። አድጊም ግን ራሴን እጠይቃለሁ። 'ያንን አሞራ ለምን ነበር የገደልኩት?'

@shuktus_books

የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች[14]

ሕይወትን ወደ ግራ ለያነቡት ሞት ነው[15]

ከእናቴ ማኅፀን እየወጣሁ በነበረበት ተመሳሳይ ቅጽበት ላይ የምንኖርበት ዓለም አንድ ሺህ አንድ እንግዳ ክስተቶችን አስተናግዳለች።

○

[14] እንጀራ 4

[15] ለአባቴ—ገብረክርስቶስ ደስታ (መንገድ ስጠኝ ሰፊ)

'ጸ'

(ግራ)

ዝናብ እየጣለ ነው። በርዶኛል። ቆረን ይዞኛል። የተከናንብኩት የፌስታል ዝናብ ልብስ በሚናጠት ነፋስ እየተውለበለበ ያስቸግረኛል። ከፊቱ ተቦርትሮ እንደ አሞ አፍ የተከፈተ ጫማዬ የሞታ ደለል ተሸክሞ አላራምድ ይለኛል። በእግር ጥፍሬ የሚገባው ትዝታዬ እስከ ራስ ጸጉሬ ድረስ ይሰማኛል። በቀኝ እጄ የጨበጥኩት የዕንጨት ምርኩዝ ላይ ጣቶቼ ተኮማትረዋል። ከሳምንት በፊት የቀኝ እግሬን ቁርጭምጭሚት እንድ ነጃሳ ጥሎር ውሻ ነክሶኛል። በሽሚዝ ቅዳጅ የታሠረ ቍስሌ ይጠዘጥዘኛል። የዝናብ ውኃ ሳይሆን ጨው የተነሰነሰብኝ ያህል ይሰማኛል። ክቶኛ ያስነክሰኛል። ዝያለሁ።



በዚያ ላይ ሆዴ ባዶ ነው። እንጀቴ ይንዘፈዘፋል። ጨጓራዬም ባልጓል ምግብ ይጠይቀኛል። በግራ እጄ የታዝቡት ጥቁር ፌስታል ውስጥ ያለውን የፍርፍር ድርቆሽ እንዳልሰጠው ለበጓሳዬ ሰስቼለሰው። የቀረኝ አንድ ጉርሻ እንኳን በትሙ የማይሞላ የሻገተ መናኛ ፍርፋሪ ነው። እርሱንም አሁን ልሰጠው አልችልም። እስከሚበታተን ድረስ መራብ አለበት። አሁን ስጥቼው በጓሳ እኔ ምን ልሆንለት ነው? ብገሸለጥስ? ግድ ነው ትንሽ መታገስ አለበት። የዚህ ሁሉ ችግር መነሻ በደኅና ተኝቼ የነበረበት ስፍራ ላይ በድንገት መጥተው ቦታውን ለቅቂ እንድሄድ የነገሩኝ ፖሊሶች ናቸው።

ከዝህ ገለጻ በቅን ግረ
መገለገል ፈልጌያለሁ። ጥ
ሳሁን እንደ
እያወቅኩት ነው ልጥ
የምሸው። አመጣ
እያስደነገጠኝም። ድንገ
ሳላሰበው አልደረሰብኝም። ሂ
ጠራሁት እንጂ መ
አልጠራኝም። ግቃና ውስ
አልኩት እንጂ ተነሣና እንሂ
አላለኝም። ሞት ግን በዚህ
መንገድ እንቢ ቢለኝስ፣ ወይ
እንደ ሰው ቢቀልድብኝ
መረታትን ባይወጽ
የጨዋታውን ሕግ ሸር እን
ተገመለመለ ልኳሸበት በል
አይችልም፣ ጅርባዬ ላ
አንዲት የምትበላ ዝ
ቢለትብኝ? ትርጉም ቢኖረው
ባይኖረውም ወደ ሞ
እየሄድኩ በታትከብት ግዝ
መረለጊ መቼ ይቃረ
የመጨረሻዎቼ ደቂቃዎች ላ
ነኝ።

ይሄኔ ትንሽ እንቅልፍ አግኝቼ ቢሆን ኖሮ ጨጓራዬን ለተጨማሪ ሰዓታት መሸወድ እችል ነበር። አሁን እየተጓዝኩ ነው። በእያንዳንዱ እርምጃዬ ልከም እታመማለሁ። ዝናቡ ይነሚነሚል። ያሳዝናል። መንገዱ ጉም ለብሷል። መጠለያ ማግኘት ከብዶኛል። ቁልቁለቱን መውረድ እንደ ተያያዝኩ ያንተላፉትን ጉራንጉር ሰፈሮች ተመለከትኳቸው። እልፍ ቤቶች በጨለማ ባሕር ተውጠው አይታዩም። ጭጋግ ወርሷቸው እንቅልፋቸውን ይለጥጣሉ። እንደ ዐሣ ስንጥብ በስሱ ገርበብ ብሎ ከተከፈተ አንድ ቤት ብቻ ብርሃን ወደ ደጅ ይፈልቃል። በደመ ነፍስ ወደ እዚያው ተሳብኩኝ።

አንዲህ ዓይነት ቀልድ
አያበሰጅም፣ ብሎ መረጅ
አለብኝ። እዚህ የምናናቀው
ሰው የለም። የምናናቀው ከተማ
የለም። የምናናቀው አገር
የለም። የምጠፋው ነገ የለም።
ወደ ሞት ብሄሰማስ እርሱ ወደ
እኔ አልመጣም።
ዘግይቶብኛል። ልቤ ይመታል፣
የተለየ ኃይል አይደለም።
አልፈራሁም። ሁሉም ሰው
ብቻውን ነው የሚሞተው።
ሞቴን እንደ ጀግና
እጠብቀዋለሁ። ካንተላፉበት
ነቅቶ እየመጣ ይሆን፣ ከደጅ
በዝናቡ ውስጥ የሚጮህ ግቢ
ብረት በር በጋይል ሲጋጭ
እሰማለሁ። በሩን የቤቱ አከራይ
ሴትዮ ላሠሪዋለሁ። ሲሉ
ነበር። እርሳቸው በሩን
እምብዛም ስለማይከፍቱትና
ስለማይወጡበት ነው መሰል
አላነጋገሩትም። ከረቤ ጋር
እንጋገራለሁ።



ከጀርባዬ የጉርፍ ናዳ ይግተለተላል። ስደርስ የዋናው መግቢያ በር እያንከስ ይወዛወዛል። ግቢው ውስጥ እንደ ገባሁ በሩን ጋይለኛ ነፋስ አጋጨው። የተፈጠረው የድምፅ ሞገድ በዝናቡ ውስጥ ምን ያህል ሊጓዝ እንደሚችል አላወቅኩም። ሰውም ባይሆን አንዱ ጥግ ኩርምት ብሎ የተኛ ውሻ ካለ በበሩ ጩኸት ሊቀሰቀስ ይችላል። ደንግጬ በአለሁበት ተገትሬ ቀረሁኝ። የሚጋጭ የመስኮት ድምፅ ፊት ለፊቴ ካለ የድሮ ቤት እየተነሣ ይመጣል። የለበስኩት ፌስታል ካልበረርኩ ብሎ ከጀርባዬ ይርገበገባል። አፈትልኮ እንዳያመልጠኝ አጥብቄ ይዣዋለሁ። ልቤ በፍርሃት ደረቴን ሰንጥቆ ለመውጣት ይታገላል።

በግቢው ውስጥ የነቃ ሰው መኖሩን ለማወቅ ዙሪያዬን ማተርኩ። በተለየ ድምዕም፣ እንቅስቃሴም የለም። ምንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ ነበርኩ። መብረቅ ሲባርት የወገገው ብርሃን ብልጭ ብሎ ከሰመ። ከሰርቪስ ቤቶቹ ብርሃናማውን ቤት በቀስታ በሩን ስገፋው ከውስጥ የነበረው የማስደገፊያ ደንጊያ እየተንሸራተተ ሄዶ በማማሽ ተከፈተ። ከእንገቱ አስማጊ ወደ ውስጥ እየሁ። ደማቅ ቀይ ምንጣፍ የተዘረጋበት እንድ ክፍል ነው። ግራ እግሬን አስቀድሜ እየተንጀረከኩኝ መቃኑን ታክኪ ከማላውቀው ሰው ቤት ገባሁ። በተከፈተው በር ዝናቡ እየተራናጠቀ ሲገባ መልሼ ገጠምኩት።





ስሮር ፈጽሞ ያልጠበቅኩት ትዕይንት ገጠመኝ። ፊት ሰፊቴ ሰው ተሰቅሏል። ጀርባው ይታየኛል። ተገረምኩ እንጂ አልደነገጥኩም። የሞተ ሰው ላይ ይህ የመጀመሪያዬ አይደለም። የጎዳና ላይ ኅደኞቼ በረንዳ እንደ ተያዘች ዶሮ እሸልበው ከጎናቸው ነቅቻለሁ። በሕይወት መንገድ ላይ እንዴት አለመሞት እንደምችል እያሰብኩ ነው የመጣሁት። ኮሜዲኖው ላይ በተቀመጠ የጠፋ የኤሌክትሪክ ምድጃ ላይ መጠነኛ ድስት ተጥዷል። ፈስታሌን አስቀምጬ ድስቱን ከፍቼ እየሁት።

የስልስ ድልህ የበዛው እንጀራ ፍርፍር ነበረው። ከላዩ ላይ ትንሽ ተንሥቶለታል። አፈን ምራት ሞላው። በእጄ ገባሁበት። እንጋፍፈ ከጉረስኩ በኋላ ቀልቢን ለመሰብሰብ ሞከርኩ። የሰውዬውን ጀርባ እየተመለከትኩ ለማሰብ ሞከርኩ። ይህ ሰው ማን ነው?



ጥያቄዎች ነበሩኝ። ማለት ለመሞት የመጀመሪያውን እርምጃ ተራምዶ ሲያበቃ በሩን መዝጋት እየቻለ ገርበብ ማድረግ ለምን አስፈለገው? የሚጠብቀው ሰው ነበር? መፍጠን እንዳለብኝ ተሰምቶኛል። እርምጃዬን እየቆጠርኩ ቀረብኩት። እንደ ምንም ቀና ብዬ አትኩሬ ተመለከትኩት። ያየሁት ነገር እጅግ ያስደነግጥ ነበር። ዓይኖቹን ለማመን አልቻልኩም። ሰውዬው አልሞተም።



ከዚያም በላይ እየተሰቀልኩ የነበርኩት 'እኔ' ነኝ። የምለው እብደት እንደሆነ አውቃለሁ። በዚህ መንገድ ላስቀምጠው፡- የተሰቀለው ሰው በመልክ፣ በቁመት ከእኔ ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው። የተሰቀለው ማነው? እኔ ነኝ እሱ ነው? እንዴት አንድ አምላል ልንሆን እንችላለን? ዓይናቹን አላመንኩም። ግር አለኝ። ሰመመን እንዳይሆን ፈራሁ። በገዛ እጆቹ ፊቴን ጸፋሁ። እውነታው አልተቀየረም።



ራሴን አረጋግቼ ጠጋ ብዬ በአለማመን ደግሜ ተመለከትኩት። የደላው፣ ያማረበት 'እኔ' ተሰቅሎ ያገራል። የደፈረሱ ዓይኖቹ ቁልቁል እያዩኝ ይንከላወሳሉ። በፍርሃት ተተራምሰዋል። በመገረም እጁን ሰድጀ ነካሁት። ባለበት እንደ ደነበረ በሬ በረገገ። ቆዳው ተሸልቶ ሰውነቱ እንደሚንዘፈዘፍ የሙት በግ ሥጋ ተንቀጠቀጠ። ምን ላደርግለት እችላለሁ?



የወደቀውን ወንበር በፈረሳቱ እንዲረግጥ በርጎራጎ አስጠጋሁለት። በድፍ ቶመ። አስባለሁ። ሐሳቦቹ አይያዙልኝም። የተሰቀለው ሰው ማንም መሆን ይችላል — እኔንም ጭምር። ባድነው ግን ያመሰግነኛል ብዬ አላስብም። በየትኛው ልምዴ ላምነው እችላለሁ? ከዚህ በፊት አላውቀውም። ርጥባን እንኳን አልቸረችም። ባተርፈው ሞቱን እንዳበላሸሁበት ቢሰማውና ደስተኛ ባይሆንስ? ንብረቱን ጥሎ ሊሄድ የነበረው ሰው ነፍስ ሲዘራ 'ቢቱ ለምን ገባህ? አንተ ሴባ!' ቢለኝ? የከፋ ጣጣ ውስጥ ገባሁ ማለት አይደለም? ከዚህ ሁሉ ያገኘሁትን ዕድል ተጠቅሜ በጊዜ ከዚህ ቤት ብወጣስ? ከአግር እስከ ራሱ ተመለከትኩት።



ያደረገው ጫማ ያምራል።
ቁጥራችን ልክ ይሆን?
ላመልትበት ታገለኝ። ቁጣና
ኃይል ነበረው። አልገባኝም።
ምን ሆኖ ነው? እየሞተ እንኳን
ችር መሆን አልነበረበትም?
ትንሽ እንደ መናደድ አልኩኝ።
በሆነ መንገድ እኔ 'እሱን'
ከሆንኩኝ መራራት
አልነበረበትም? ምናልባትም
ይሄ ሰው ሞት ይገባዋል።
ለፍረጃ ችኩል ይሆናል። ግን
ጊዜ የለም። መፍጠን አለብኝ።
ሱሪውን በቅርብ እንደ ገዛው
ያስታውታል። እንዲያውም እኔ
ከለበስኩት ውራጅና ቅጸጅ
እንጻር ጥሬ ነው።

በሞት እየተረታ ነው። ፈሱን
አንባረጠ። ሽንቱም
አመለጠው። ሰውነቱ ሲነዛው
ደነገጠ። ውኃ የሚያስገባ
ጫማዬን፣ መቀመጫው ላይ
በተደጋጋሚ የተጣራ ሱሪዬን፣
የጀበንኩትንም የነበበ ሻማ
ጃኬት አመለትኩኝ።

በዚያ ደቂቃ መራት የረገጥኩት
የማውቀው 'እኔም' አየር ላይ
የተንጠለጠለው የማላውቀው
'እኔም' ዕርታናችንን ነበርን።
ጫማና ሱሪውን ቀይሬ ለበስኩ።
የሱሪውን ኪሶች ፈተሽኩ።
የመቶ ብር ኖቶች ተጣጥፈው
ተቀምጠዋል። መልሼ
ከተትኳቸው። ከወንበሩ ጋር
ወለሉ ላይ የወደቀውን ባለገበር
ኮትም አንሥቼ በላዩ ላይ
ደረብኩ። ተባይ የወረሳቸውን
ቅያሪ ልብሶቼንም በፌስታሉ
ሰብስቤ ያዝኩኝ።



8

የነፍሴ ሰረት ከገላዬ ሲላቀቅ
ተሰማኝ። በሕይወት ያለ ሌ
እኔን ዓይናቹ ስላዩ ሳቢ ግ
በሞት መረቃቸውን ፈጽ
አላመንም።

ከመውጣቴ በፊት ምን ልለው እችላለሁ? ይቅርታ መጠየቅ አለብኝ? ምስጋናስ ይገባዋል? ለምን? እንዲያው ግን በመኖር ያጣውን ነገር በሞቱ እንዲያገኘው እመኝለታለሁ። ዝናባማ ደጁን እንደ ረገጥኩ ሞቀኝ። የሞተ ሌላ እኔን ዓይናቹ ስላዩ ግን ልቤ በሕይወት መኖሬን ፈጽሞ አልተቀበለም።

[15]ጊዜ ያልፋል። ምናልባትም አላፊ ጊዜ እየተጠራቀመ የሚሄደው በከርሳችን ውስጥ ባለ ሥውር ቢላ ስፍራ ውስጥ ነው። የተገነባነው በስብ ብቻ አይደለም። ገላችን ውስጥ የጠለቀ የጀምበር መዐት አለ። እኛ ራሳችን ጊዜና ትዝታ ነን። ቁም ነገሮቻችንና ኩሸቶቻችን፣ ያኮረፍንባቸውና የሳቅንባቸው፣ የተቆጣንባቸውና የተረጋጋንባቸው፣ የሠራናቸው ክፉና መልካም ነገሮቻችን ሁሉ በአንድ ሕፃን ልጅ ተነበው እንደ ተጨረሱ የተረት መጻሕፍት በማምሻ ይከደናሉ።

○

የምድር ስፋት ሞታችንን ኢምንት አድርጎታል። ግልጹ የሚሰማው መርጹ ጹብ ዕጹነቱ ለሟች ቤተሰብ ብቻ ነው። ሟች በሄደ ጊዜ ...ሕይወት በሚወጹት ሰዎች ዘንድ ትቀዘቅዛለች። በቀሪው ዓለም ግግር በረጹ የሚያቀልጥ ነዲድ ፀሐይ እጹን ይዘረጋል። ሕይወት ሞቆ ይቀጥላል። የማናውቀው ሰው ሞት አያስገርመንም። አይከብደንም። ብዙ ሰዎች በከባድ ሕመም ውስጥ እንዳለፉ የምንረዳው ሞት ቅጥራችንን አልፎ

[15] ማቢያ 4

ቢተባባችንን፡ የእኛ የምለውን ሰው በጎበኘብን ጊዜ ነው፡
ያኔ! ...የማጽናናት ቃል ለልብ ጠብ እንደማይል እንታዘባለን፡

○

ጊዜና ትዝታ ነን። ቆዳችን ስባችንን ብቻ ሳይሆን የኖርነውን ጊዜ፡
ትዝታ ጭምር ነው የጋረደው። በዓይን ስንታይ አሁንን ነን። ኮር
ግን ዓመታትን በልተናል። በደማችን ውስጥ የሚርመሰመሰ
ሼንጉርጉር ትዝታ ነው። ያለፈውን ጊዜ፡ ያለፈውን ስሕተት ይ
ኋላ መልሶ የሚያስተራርም አዳኝ ልዕለ ሰብኡ የለንም። ሆነ
ሰዎች ነን። በዚህ ምድር ላይ ሰው ሆነን ስንኖር ይ
የመጀመሪያችን ነው? እናውቅም። ትውስታው የለንም። ወደ ኋ
መመለስ ቢቻል ብለን እናልማለን። ሕልሞቻችን በሕየው ሀ
ይተምሳሉ። ተስፋዎቻችንም በሰማያት ላይ ይዳምናሉ። ስለኖ
ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለናል። ስለሰላምም ጦርነት ይምተናል
አሁን ድረስ ልክነቱን እናውቅም። ቢያልፍም ጮክ ብ
የምንናገረው ጸጸት የለንም። ስለሞቱት ስንል፡ ስለከፈልነው
መሥዋዕትነት ስንል ዝም ግለትን እንመርጣለን።

○

ከእውናችን ውስጥ ግማሽ ኑረታችን እንዲሰረዝልን የምንሥ
አለን። ብንፈልግም እንደማይቻል እናውቃለን። ሆኖም አድ
ሰዎች ነን። ጨርሰን ባንድንም በትከሻችን ላይ መርላት የጉ
ይታት ከማፍሰስ አንቆጠብም። ስለጪሀና ስለሌሎች ነገሮች ሌ
ላይ ቆመናል። ነገን ተስፋ እናደርጋለን። ምናልባትም ድ

እናደርግም። ብርሃን ይዘው ይመጣሉ ብለን የጠበቅናቸው፡ ተስፋ
ያደረግናቸው ነገሎቻችን ...የጨለማ በርኖስ ሲያለብሱን
አይተናል። ፍርሃትና ድፍረት ተዳብለው በልባችን አሉ። ስንፈራ
ስላደረግናቸው አእላፍ ነገሮች ፈጣሪ እኛን ይቅር እንደሚለን
ተስፋ እንደርጋለን። ስንደፍር እኛም እርሱ በእኛ ላይ ስላደረገብን
አዕላፍ ነገሮች በተራችን ይቅር እንደምንለው ተስፋ እናደርጋለን።

ዘጠኝ ሞት[17]

ሞት ሳይሞቱት ነው እሚለመድ?[18]

ከተወለድኩበት ቀን እንስቶ በተሳሳተ ዓለም እንደ ተፈጠርኩ ይሰማኝ ነበር። የልጅነት ሕልሜ በወጣትነት መሞት ነበር። ጉርምስና እያቸገረኝ — በተጠሮው መጣ። እኔ ግን ሳልኖት በሕይወት ቆየሁ። ለምን?

○

የአገሬ ሰዎች በሕጻር በሽታ፣ በፈንጣጣ፣ በሳምባ ነቀርሳ በኩፍኝ፣ በልጅነት ልምሻ፣ በትክትክ፣ በመንጋጋ ቆልፍ፣ በሾደ ደግፍ፣ በወባ፣ በተቅማጥ፣ በጨብጥ፣ በፈስቱላ፣ በራቅ ተሠቃይተው ይሞታሉ። ተከፍነውና ሰሌን ተጠቅልለው እየ

[17] እነጀራ 5
[18] ገራ — ጸገመ

ይሰብሳሉ። ሲመለዱም፣ ሲሞቱም ፍጥነት አለው። እምና ገንፎ ያገነፉ መይጣዘርት በጎመሉ ጎናቸው ያነፍራሉ። ተገነፍር ያወጣሉ። ለልትሶ የተቀመጡ ጉበሮች የቦዙ ዓይናቻቸውን እያንከባለሉ በአንክላ ትራሪ ይጠጣሉ። በአዘቦትም ቀን አረቄ ጠጥተው ሞቅ ያላቸው ተርታ ሰዎች በ 'ለምን አየኸኝ' ሰበብ በሽመል ይፈነካከታሉ። የታሪክ ድርሳናቸው ቢገላበጥ ዘመናቸውን የሞላው የመርዝነት ዓይነትና የረሳ መወት ነው። ምንጅላቶቹ ድግ፣ ዝናር፣ ጠመንጃ፣ ጎራዴ ይታጠቃሉ። በእንገታቸው አሽከንታብና ድሪ፣ በጆሮዋቸው ሎቲ፣ ጉትቻ፣ ያደርጋሉ። ባለወርቅ ለምድ ይደርባሉ። ጣምራ ጦር ጨብጠው፣ ጋሻ ያንገባሉ። ፈረሶቻቸውን እየተመላለሙ በፍርሃት አልባነት ወደ ጦር ሜዳ ሽምጥ ይጋልባሉ። ወደ እንድ እይደለም። ወደ ዘጠኝ ሞት እየርከሩ፣ እየሸለሉ፣ እያትራሩ ይገሰግሳሉ።

○

ባንገቡት ነፍጥ ወራሪ ጠላትን ይወጋሉ። በጌትነት በለስ ባሪያ ያሳድራሉ። ሰው እንደ ወፍ ይገድላሉ። ተፈጥሯዊ ሞትን ነፍሳቸው ትጠየፈዋለች። 'እንደ ጀግና መሞትን' ይመርጣሉ። ባለእገር፣ ነገሥታት፣ መሳፍንት፣ ቀሳውስት፣ ጌታዎች፣ ሱሌዎች፣ ገረዶች፣ ሽፍታዎች፣ ገባር፣ ወዝአደር፣ ፈውዳል፣ ቡርጋ፣ ካፒታሊስት፣ ሶሻሊስት፣ ኮምዩኒስት፣ ኢምፔሪያሊስት፣ ሊብራል፣ አናርኪስት፣ ባንጻ፣ ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ መሐል ሰፋሪ፣ በዝባዥ፣ አድርባይ... በእልፍ ቃላት፣ በእልፍ አእላፍ መደብ ይታገላሉ። ደክሟቸው

አያውቅም። ከሞርነት ያረፉበትን ጊዜ በግል ይገዳደሉበታል። ደም ይታቡበታል። በበሽታ፣ በጠኔ፣ በድርቅ ተመትተው እንደ ጠወለገ ቅጠል ይረግፉበታል። በእብዮትና በፀረ እብዮት ይናጡበታል። ታሥረው ይረሸኑበታል። በአደባባይ ይሰቀሱበታል። ሬሳዎቻቸውን በዘማች እሞራዎች ያስበላሉ። የመቃብር ስፍራዎቻቸው በፀደይ ወራት በሐረግ ይወረሳሉ። በነዒሞ የሰንሰል አበቦች ይጀቦናሉ። ምልክት በሌለባቸው መካነ መቃብሮቻቸው ላይ የተሠሩ የሰቀላ ቤቶችና እንደ ጢቢኛ የተጠፈጠፉ ጠመዝማዛ የመንገደኛ ዳናዎች ይታያሉ። ሌሊት ሌሊት ቤተኞቹና መንገደኞቹ መግደልንና መገደልን ሲያልሙ ያድራሉ። በራሳቸው ሕልም ውስጥ ተሳዳጅ የሆኑት ሰዎች በሌላ ሰው ሕልም ውስጥ በአሳዳጅነት ይገለጣሉ።

○

አየሩ የቅድመ አያቶቹን እጽም በአመድነት ያዝላል። ሰማዩ ባኮረፉ ደመናዎች ይሞላል። በክረምት የሚጥለው ዝናብ እንደ ጥይት ይጮሃል። ነጎድጓዱ እንደ ጠመንጃ ይባርታል። አዕዋፋት በድንጋጤ ወደየ ጎጇቸው ይበተናሉ። ሰዎች መጠለያ ፍለጋ ይራወጣሉ። ውሾች በፍርሃት የሲርሲርታ ድምፅ ያሰማሉ፣ እንገታቸውን ደፍተው፣ ጭራቸውን ሸጉበው እንዲ ጥግ ኩርምት ብለው ይሸሸጋሉ። ማይ ነው አረሩ? ሲያባራ በረሰረሰው ምድር ላይ ሁሉ ነገር በቁጣ ያድጋል። የጠጅ ሣሩ፣ ቀጤማው፣ ጦስኙ፣ ዝንጅብሉ፣ ጤና አዳሙ፣ በሶ ብላው፣ ጥንቅሹ፣ የሸንኮራ እገዳው፣ ጤፉ፣ ማሽላው፣ ዘንጋዳው፣ ሰሊጡ፣ ቡናው፣

ጌሾው... እያደር ይመዘዛል። ከብቶች ይደልባሉ፣ ሙክቶች ይሰባሉ። የአበቦች ፍካት ያስደነግጣል። ከዚያ ውኃ ጠጥተው የኮረደዱ ልጃገረዶች ውበታቸው ገዳይ ነው። የእንገትና የድዳቸው ጉራማይሌ ንቅሳት ያፈዝዛል። ከፈገግታቸው ላይ ነጭ ማር ይቶረጣል። ኩታዎቻቸውን ተከናንበው፣ ዘንቢሎቻቸውን እንጠልጥለው፣ ዕንቅብና ሰፈዶቻቸውን ተሸክመው፣ ኋላና ፊት ሆነው በባዶ እግሮቻቸው እየተጀነኑ መንገድ ሲጓዙ በፍጹም መዋቲ አይመስሉም።

○

ሁሉም ሰው የራሱን ሞት እንደ ሚሞት አውቃለሁና —የገዛ ሞቴን አልፈራም። እንዲያውም በሕይወት ልምምድ የምሞትባቸው ብዙ ዕድሎች ነበሩኝ። ለምሳሌ ወንዝ ዳር ያበቡ አበባዎችን በተመስጥዖ እያየሁ መጫወት በምወድበት የግቲነት ዕድሜዬ በደራሽ ውኃ ተወስጄ፣ እዋዜ የተነከረ ቀይ ሥጋ እንድቀምስ እናቴ ባጎረሰችኝ ጊዜ ጉሮሮዬ ላይ ተወትፎብኝ፣ የንብ ቀፎ የተሰቀለበት ዛፍ ሥር ተዘርፍጭ... አሁን ድረስ ትርጉሙ ያልገባኝን የተጠላለፈ መሥመር ስጭር በንብ ምርኮ ተወርሬ፣ ታዛ ሥር ተጠለልኩ ስል በመብረቅ ተመትቼ፣ ፎሮፎር የወረረውን ጭንቅላቴን ከመጠን በላይ ስርክት እንደ ብርቱካን፣ እንደ መንደሪን፣ እንደ ቲማቲም እንጎሌ በጥፍሬ ተፈርጥቆ፣ እከክ የለቀቀበትን ሰውነቴን እንደ ክራር ስገርፍ ሆዴ ተቀርድዶ፣ በቂስ መምህሬ 'ፊደል ገደፍክ' ተብዬ በሚወርድብኝ የእለንጋ ብዛት ልቤ ደክማ፣ ብስክሊት ሳካልብ ገደል ገብቼ፣ ማትስ

ባላስኮረጅኳቸው የከፍሌ ልጆች በደቦ እንደ አህያ ተረግጬ፣ ዩኒቨርሲቲ ከገባሁ ለአንዱ መደብ በተተኮሰ ጥይት ደረቴን ተመትቼ እስክ መጨረሻው ላንቀላፋ እችል ነበር።

○

እኔ ግን ሳልሞት በሕይወት ቆየሁ። ለምን? በተአምር ነው ወይስ በመጥፎ ዕድል?

[19]የእኛ ሞት እንደ ኢየሱስ ከርስቶስ ሞት አይደለም። በስግችን ወንጌል የሚጽፉልን ሐዋርያት የሉንም። ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕትና ምዕራፍ አይደረስልንም። ማሕሌት አይቆምልንም። ቅዳሴ አይቀደስልንም። በጥይት ተገድለን የተጣልንበትን ጉድባ ወዳጆቻችን አይሳለሙትም። በመኪና ተገጭተን የወደቅንበትን አስፋልት ካህናት ዕጣን አያጥኑትም። ሻኮራ አይወዘውዙበትም። በነዲድ ራስ ምታት ተይዘን፣ በሳብ ተዘፍቀን፣ በስቃይ 'ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ኤልማስ ላማ ሰበቅታኒ'[20] ብለን ነፍሳችንን ያሳለፍንበትን የሙት አልጋ ቤተሰቦቻችን እንደ ታቦት ተሸክመውት በየአደባባዩ አይዞሩም። የመንደራችን ሰዎች አልጋችንን ከተሸከሙ የእጎትና የወንድሞቻችን እግር ሥር እየተከተሉ የዘምባባ ዝንጣፊ አያነጥፉም። ዝማሬም አያሰሙም። ለምንድን ነው በዝምታቸው ስንከሳራችንን ከአንድ ስንኝ የሚያሳንሱት? ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግብአተ መሬታችን በውሽት የልቅሶ ሳግ ታጅቦ ይፈጸማል። ምን ያህሉ እንባ፣ ምን ያህሉ ጸጥታስ እውነተኛ ነው? ሞተንም የሚያሞኙን አይጠፉም። መታብራችን ለሦስት ቀንና ሌሊት አይጠበቅም። ብንነታም የታፈነ ጩኸታችንን ሰምቶ የድንጋዩን ርብራብ የሚያነሣልን የለም።

[19] ማቢያ 5

[20] እምላኪ እምላኪ ስለምን ተውከኝ? ማቴ 27፣46

ስማችንም[21]፣ ሞታችንም ትርጉም የለውም። ስለዚህ ለምን እንሞታለን? ለምንስ እንኖራለን? በሕይወትም በሞትም ላለን እንረሳለን፣ እንዘነጋለን። በተለያየ ምክንያት በጥልቅ ያዘኑ፣ የተደበቱ፣ የተበደሉ፣ ያኮረፉ፣ ትርጉም ያጡ... ሰዎች በር፣ በራቸውን ጥርቅም አድርገው ዘግተው ባዶ ቤት ራሳቸውን አጥፍተዋል። ነገር ግን ይህ ሲሆን ዐሐይ በድንገት ስለማትጨልም፣ ጨረቃ ደም ስለማትመስል፣ ከዋክብትም ስለማይረግፉ፣ የቤተ መቅደስ መጋረጃዎችም ስለማይቀደዱ ስማቸውንም፣ መሞታቸውንም እናውቅም። የሞተ ያልነበረ፣ ያለም የማይሞት እንደ መሰለ —ሕይወት ይቀጥላል።

[21] ከዕለታት አንድ ቀን ደጃች 'ከ' (ኋላ ዐጤ 'ቴ' የተባሉ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ) የቁንጻላቸው ንጉንን የሚያምር፣ የገጻቸው ጠይም እሳትነት፣ የዓይናቸው መንተግተግ፣ የጠባያቸው ተለዋዋጭነት የሚያስፈራ፣ በዘመነ መሰፍንት እንደ ጎብስት የተቆራረሰች እገራቸውን እንድ ለማድረግ ቆርጠው ይነሣሉ። የእገራቸውንም ሰው 'ንብር ሥርዓት ግሃ' ቢሉት 'እምቢ' ብሉ ይጠላቸዋል። ከእንግሊዝ ጦር ጋርም ያብርባቸዋል። ዐጤውን ወደው የተከተሉዋቸው ሰዎች እንድ እርሳስ ፈርተው ጥለዋቸው ይሸሻሉ። እንደነታማኝ ወዳጃቸውና አገለጋያቸው ፈታውራሪ 'ገ' ያሉት በጀግንነት እየተዋጉ በሰናድር ጠመንጃ ግንባራቸውን ተመትተው ጦር ሜዳ ይወድቃሉ። ግርማዊነታቸው መቅደላ አፋፉ ላይ ብቻቸውን እስኪቀሩ ድረስ ከጀነራል 'ና' ሰራዊት ጋር ሲዋጉ፣ ሲዋጉ ቆይተው ራሳቸውን ያጠፉ።

እኩ ለምን ራሳቸውን ገደሉ? የልጅነት ሕልማቸው 'ያ' ስለነበር ነው?

ጽድቅና ኩነኔ[22]

መሆን አለመሆን

በአጠገባቸው እያለፍኩ ነበር።

○

የላይብረሪውን ብሎክ ጀርባ ተደግፈው ሦስት ወጣቶች ዋይፋይ ይጠቀማሉ። ስለ 'ያ' ትውልድ ሪቮልዩሽኒስቶች ይከራከራሉ። ኢንተርቪው፣ መጽሐፉ የሚያወራው ስለስልሳዎቹ አብዮተኞች ነው። ያ ትውልድ 'ይሄኛውን' ትውልድ አልተወውም። ይሄኛውም ትውልድ 'ያ' ትውልድን አልተወውም። ሰጪም ጊዜውም አልሄደም። ትላንት ሶሻሊዝም እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ይታይ ነበር። የማርክሳዊ ፍልስፍናን በቃላቸው የሚያንበለብሉ

[22] እገጀራ 6

ወጣቶች ፈውዳሊዝምን ሲታገሉ ተገድለዋል። 'ን' 'ሴባ' ሌላ እየተባሉ በቮልስ ዋገን ተሸኘተዋል። 'ደ' 'ሰቫሊስትና' ጊዚያዊ ወታደራዊ መንግሥት ነኝ' እያለ በሥልጣን መንበሩ ላይ ተተክቷል። 'መ' የአገር ፍትር ቢኖረውም ከነጭ ርግብ ይልቅ መጣሪያ ይወድ ነበር። 'የፍየል ወጠጤ ልቡ ያበጠበት...' ን እየዘፈነ በመንገዱ ያገኘውን ወጣት ረምርሟል። በተደጋ ገዱሐን ዜጎች አልቀዋል። እንደ አገዳ ተጨፍጭፈዋል። በቁም ያሉት የሚወዱትን፣ መልሰው በአካል የማያገኙትን ሰው እስከ መጨረሻው አጥተዋል። ለቀቀን ለብሰዋል። ያንን ጊዜ ዞረው ሲያዩት እንደ እግር እሳት ይፈሯቸዋል። ትዝታቸው ውስጥ በረሞተ የተዳፈነ እሳት ተኝቷል። ለመቀበል ይከብዳል። አሁን 'ያ' ጊዜ አልፏል።

○

'መ' በሽሽት 'ቪ' የተባለ አገር ከገባ ቆይቷል። ዕድሜው ሰማንያን ተሻግሯል። ምናልባት አይደለም ትላንትን ያህል ውስብስብ ነገር የሚግ ከርን ያህል ቀላል ነገር አስተካክሎ ማሠር እንደሚከብድ በዕድሜው ገብቶታል። በስምንት ዓመቱ የሞተችበት እናቱ ዛሬም ድረስ እየናፈቀችው ከእንቅልፉ ድንገት ይባንን፤ በጉንጩም ላይ ያቋረጠ ትኩስ እንባ ያገኛ ይሆናል። በልጅነቱ 'አንተ ልጥልጥ ባሪያ' ብለው የሰደቡት ሰዎች እምባገነንነቱ ላይ እጃቸው በሥውር የለበትም? እነዚያ ከንፈሮች ጠርተው ቢስሙኝ ብሎ አልተመኘም? እነዚያ ሰዎች በበደሉት እንድ ሰው ውስጥ ሺህ ሰዎችን አልበደሉም? እንደ ጀግና ኖር ኖር ሲያበቃ ይሄን ይሄን

ስሜቱንና ስብራቱን በአለቀ ሰዓት ለማን ይናገራል? ደካማ እያስመሰለውም? ወይስ ሲፈጠር ጀምሮ እንዲህ ዓይነት ሰዋዊ ስሜቶች የሉትም? ልቡ መጨከንን እንጂ ማዘንንና መጸጸትን እያውቅም?

○

እንዳንዶች ከምግባረ እኩይነት ጋር ሌሎች ደግሞ ከሠናይነት ጋር ይወለዳሉ? ከፋትና ደግነት እንደ ነፍስ ይከፈላሉ? ታዲያ በመሐል የ 'ነጻ ፈቃድ' ነገር ወደ የት ይወድቃል? ለመልካምነት ወይም ለክፉነት ተሳልፈን የተሰጠን ባሪያዎች ብንሆን ለድርጊታችን በምን ሒሳብ ኃላፊነትን እንወስዳለን? በእኛ ገላ ክፉና ደግ የሚሆነው በውስጣችን ያለው ሌላ ባዕድ 'እኛ' ከሆን... እኮ ማን ማንን ይኮንናል? ያወድሳልስ? በተፈጥሮው ክፉም ጥሩም የሚባል ሰው አለን? የምንበላሸው በገዛ ፈቃዳችንና ዙሪያችንን በከበበው የሰዎች ጥላ ጭምር እይደለምን? እሁን በያዝነው ባሕርይ ላይ ያዋጡ ሰዎች እልፍ ናቸው። ልቡና 'የነገሮች' ስብስብ ነው። የሕይወት ልምምድ በደግም በክፉም ይቀርጸናል። 'መ' በልጅነቱ የደረሰበት ምንድር ነው? ያየውን እይተን፣ የሰማውን ሰምተን፣ የደረሰበት ደርሶብን ከእርሱ የተሻለ ሰው ስለመሆንና ስለእለመሆናችን በምን እርግጠኛ ነን? ከአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች መካከል እስኪጨልምለት ድረስ ሰማይ ጠቅስ ቀንዱን የደበቀ ስንት የሰው ከብት አለ?

○

ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ ሰዎች የኮምዩኒዝምን አጭሩን ተረድተዋል። ለሶሻሊዝምም ደንታ ቢስ ሆነዋል። ነፃ ድግ በርእዮተ ዓለም ልዩነት ሳይሆን በእስተዳደር መንገድ ምርጫ ሰዎች ይጣላሉ። በእምናና በዘንድሮ መካከል ያለው ልዩነት ምንድር ነው? ኤቲኢክ ፈደራሊዝምን እንደ ግል አዳኛቸዉ የተቀበሉ ሰዎች ሌላ አማራጭ መንገድ ፈጽሞ እንደሌለ ለተከታዮቻቸው ይሰብካሉ። የእመጽ መንገዳቸው እልተቀየረም። ለዚህ እምነታቸው መሥዋዕትነት የሚከፍሉ ወጣቶችን ይመለምላሉ። ደም ከሚያፋስስ አብዮት ወደ ቃላት፣ አመክንዮ፣ ርእዮትና ውይይት አልተሻገሩም። ለድርጊቶቻቸው ኃላፊነትን አይወስዱም። በቀልን እንደ ውኃ ከፉኛ ይሰማሉ። በበደለኝነት ስሜት ይናጣሉ። ቃታ የሚያሳስቡ ትርክቶችን በዚህም በዚያም ያሉ ሰዎች ተግተው ይዘራሉ። ሁሉም ሰው ከመቶ ዓመት በፊት ተበደልኩ ለሚለው በደል የሥርየት በግ ይፈልጋል። ምኔ በግ ይመስላል?

○

ፈውዳል ነህ?

ቡርጂ ነህ?

እናርኪስት ነህ?

ኮምዩኒስት ነህ?

ፋሺስት ነህ?

ሊብራል ነህ?

ሶሻሊስት ነህ?

ፈደራሊስት ነህ?

ሥልጣን ሲፈትንህ ትደርስበታለህ። አምባገንን ከሆንክ? አምባገንን ነህ።

○

ባለኮፍያ ሹራብ የለበሰች አንዲት ሴት ፈገጠር ብላ ጉልበቷን አጥፋ ተቀምጣ ስልኳን ትነካካለች። የእግረኛውን ኮሪደር ይገር አልፋለሁ። በቆሙት ሦስት ወጣቶች ትይዩ ስደርስ ሁለቱ ልጆች እኩል ምራቃቸውን ወደ መሬት ተፉ። የምራቅ ዕጪያቸው አንድ ነው? የአገሬ ልጆች በአጠገባቸው ሳልፍ በዓይናቸው ቂጥ እየተገላመጡ! እከታ የሚተፉት ለማን ነው? ለእኔ ነው? ወይስ ለብሔሬ? ገረመኝ። አባቴ አባታቸውን በድሎ እንደሚያውቅ ይገምታሉ። ስለዚህም በደለኝነትን ይጠላሉ። ዘሩ ነኝና ሊያጠፉኝ ይፈልጋሉ። ሲያሳድዱኝ ግን አንድ አባት አይደለም የሌላ ሰው አባትን ቀርቶ የአብራኩን ክፋይ ሊበድል እንደሚችል ይዘነጋሉ። አባቴ የእኔም ጠላት ነው። አባቴን ለመግደል እኔን አትግደሉኝ አላልኳቸውም። ስለዚህም እኔን ሲገድሉ እንደ አባታቸው የተበደለን ሰው እንደሚገድሉ አያውቁም። ሞኝነታቸው ያሳዝነኛልም። ያስቀኖልምም። ከመተኮሳቸው በፊት ሚላግቸውን ቀረብ ብለው ለምን አያውቁትም? በፍትር እንዳይወድቁ

ነው? ...ምራቁ ወደ ተወነጨፈበት አቅጣጫ ሦራ ሳይ ዓይኖቻቸው ውስጥ ንጹሕ ጥላቻ ይንጸባረቃል። ምንም እንዳልተፈጠረ ወሬያቸውን ማውራት ቀጠሉ። ቢቻላቸው የጠሉትን ንኑሥ ለመግደል በቀበቷቸው ዘለበት የጊዜን ኧሮረት ይጠልፋሉ። ከመወለዳቸው በፊት ያለፉ ትውልዶችን ሲያሙ ቆጥሉ የሚመጣው ትውልድ የእነርሱን ጥሬ ሥጋ በተራው እንደሚዘለዝለው ይረሳሉ።

○

ስለአገሬ ሳስብ አጥንት የሚሰብር ድብርት ይሰማኛል። እርጥብ መሬቷ ላይ ቆሜ በኩራት መራመድን እፈራለሁ። ከሩቅ ልብ ብሎ የሚመለከተኝ የትኛውም ሰው አረማመዴ ውስጥ የተበደለ ኩራት እንዳለ አይጠፋውም። የአፍሪካ ቀንድ ሳይ መፈጠሬን መርሳት የምፈልግባቸው ጊዜያቶች አሉ። እነዚያ ወቅቶች ውበትም፣ እውቀትም እንደነጠፈባቸው ድንቁርናም እንደ ነገሠባቸው ጠራሪያ ተሲያት ያሉ ናቸው። እኮ አገሬ የቱ ጋር ናት? እሁን እሁን አገር የአባቶች ተረት ናት። ያለችው የድሮ ሙዚቃ ውስጥ ነው። ቅኝ ስላልተገዛን ያጣነው እውቀት ይኖር ይሆን? ከነጻነት ይልቅ ጭቆናን መጋራት ወደ ጠነከረ አንድነት ይወስደን ነበር? በዚህ ስሌት የባርነትን ቀንበር በጋራ ካልተሸከምን በስተቀር የምናውለበልበው አንድ ሰንደቅ አይኖረንም ማለት ነው? በጭንጋፍ ትውልድ ዓይን ይህቺ አገር ያለፈች ፋሽን ናት። በጠራራ ፀሐይ ግፍ በየቦታው ይፈጸማል። ሰዎች አረም ማረም ትተዋል። እያዩ እንዳላዩ መረን ያልፋሉ። እዚህ አገር ከፍተኛ

የምናገባኛቸውን ስሜት አለ። በምራመድባቸው ጎዳናዎች ላይ ሳዘግም እንደሚሰማኝ ባይተዋርነት ሥጋዬ በቁሙ ሊፈርስ ይደርሳል። ሥራዬ ብለው ድንቁርናን ለትውልድ በሚያከማቹ ሰዎች እበሽቃለሁ። አገሬ ላይ እስካለሁ ድረስ አደጋ ላይ እንዳለሁ እንዲሰማኝ የሚያደርጉኝን ዜናዎችን በየቀኑ እሰማለሁ። ወደ ተስፋ መቁረጥ እንደረደራለሁ።

○

ሰዎች እንዴት አገራቸውን ሊያጠፉ ዩኒቨርሲቲ ይገባሉ? ከመረራቸው ክላሺንኮቭ ታጥቀው ጫካ አይገቡም? ብዕር ጨብጠው ሰምን በጥራዝ ነጠቅ እውቀት ይነዳሉ ታዲያ? በፈጠራ መረጃ ጦርነት ያውጃሉ። ባላቸው ይቆምራሉ። የአገራቸውን አንድነት ለማስከበር ሲፋለሙ መሥዋዕትነትን በከፈሉላቸው የአርበኞች ደም ላይ ይቀልዳሉ። ልቡናዩ እውነቱን ይረዳል። ዘንድሮ ፖለቲካ ሳይንስ አይደለም። የነጠረ ሐሜት ነው። በቅኝ ቅኝ የሐሜት ወሬ ያለም፣ የሞተም እኩል ይብጠለጠላል። ትንተና ገደል ገብቷል። ምክንያታዊነት አፈር ደቼ በልቷል። እኚህ ልጅ እግሮች የሰነፍ ሰው ሥራና ምክር ውጤት ናቸው። በወንጭፍ ምላሶቻቸው፣ በድንጋይ ታሎቻቸው ያላረገፉት ማንን ነው? በወረወሩት ድንጋይ በሰማይ ያለችን ላም እግራቸው ሥር እያንከረባበቱ ጥለዋል። አሁን ወተቷን ብቻ ሳይሆን ላሚንም እያዩም። ለመጨረሻ ጊዜ ፍሥሐ ያደረጉት የመውደቅ ድምፅ ሲሰሙ ነው። የተሰበሰበው — ሲበተን፣ የተለቀመው — ሲዘረገፍ፣ የቆመው — ሲሰበር፣ የተራመደው — ሲያንከስ፣

የፈካው — ሲከስም፣ ቆጡ — ሲተረተር፣ ጠጣሩ — ሲጠረመስ፣ ግዘፍ የነሳው — ሲደረመስ ይደሰታሉ። ለእኔም ቀን እንደሚጠብቁልኝ አውቃለሁ። ከፎቅ ላይ የተገፈተሩ፣ በጩቤ የተወጉ፣ በድንጋይ የተቀወሩ፣ በዱላ የተነረቱ... ልጆች አሉ።

○

እናም ራሴን ላጠፋ በምችልበት አንድ ውብ ምሽት ከ 'ዲ' ጋር ተዋወቅኩኝ[23]። ከሞት ያስቆመኝ ብቸኛ ምክንያት —ያ ነበር።

[23] በቀጥታ አልተዋወቅኳትም። አየኋት እንጂ አላየችኝም።

[24]እጃቸውን ይዘን ከይሲ ያደረግናቸው ሰዎች ከሰይጣን ሊከፉብን ለምን እንደነግጣለን? በረኃብ የቀጣነው ውሻ የሚያድገው ወደ የት ነው? ወደ ተናካሽነት አይደለምን? ፍቅርና ምሕረትን፣ ፍትሕንና እውነትን ያጎደልንባቸው ሰዎችስ? 'የሰላም ሰው ነኝ። የሰው ልጆችን ሁሉ በሰብዓዊነት አፈቅራለሁ። በፍጹም ይቅርታ አምናለሁ። ለፍትሕም እታገላለሁ። ለእውነትም እሞታለሁ' እንላለን። ስለራሳችን የምንናገረውን የውሸት ትርክት እናምናለን። አሁን ወደ መነሻ እውነታችን መመለስ ከብዶናል። እውነቱን ብንናገር ከእንግዲህ ግን ያምነናል? በእውነትና በውሸት፣ በብርሃንና በጨለማ፣ በጽድቅና በኩነኔ፣ በነጭና በጥቊር... መካከል ያለው መሥመር ደብዝዟል። ሰው እንዴት በተመሳሳይ ሰዓት ሰይጣንም እግዜርም መሆን ይችላል?

○

የያዝነው

ያልተፈተነ ፍቅር

[24] ማቢያ 6

ያልተፈተነ እውነት

ያልተፈተነ ምሕረት

ያልተሆነ መሆን ነው።

'አኩኩሉ'[25]

'ሰልነጋም'

የሰምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ አስታውሳለሁ።

○

ማግሰኞ ቀን ነው። ከትምህርት ቤት ተመልሼ ዐጠዱን እንዳለፍኩ እናቴን ከሩቅ እየተንጎራደች አየኋት። በየመሐሉ ትቀመጣለች። ትነሣለች። እጆቿን ታናጥባለች። ቆዝማ በተቀመጠችበት ባትዎቿን በእጆቿ ትተመትማለች። አንገቷን ትደፋለች። ወደ ሰማይ ታንጋጥጣለች። መልሳ ታቀረቅራለች። የታጠቀችው ቀይ መቀነት ከአፍ እንደ ወጣ ምላስ ተዝለፍልፎ አቧራ ይልሳል። የፊቷ ላብ እንደ ጤዛ ወርዝቷል። የተንጨፈረረ ጸጕሯ ወይቧል። እየኋት።

[25] እነጀራ 7

የቀይ ዳማ መልኳ ተዳፍኗል። ክብ እንክብል ዓይኖቿ በልቅሶ ብዛት ቀልተዋል። እንደ ትላንት በኮረዳነት ዘመኗ እናቱን በሰባት ወንዶች ሕልም ውስጥ ከተሰበረ ማሠሮ ጋር ወድቃ አይቻታለሁ። የእኔ ሕልም ይሁን በትክክል የሌሎች ሰባት ሰዎች ሕልም ስብስብ እውነታውን አላወቅኩም። ግራ ተጋብቻለሁ።

‹እማይ ምን ሆነሻል?›

‹እዱ ልጂ ሰማይ ተደፋብኝ›

እያለች እጆቿን እንደ ተማረከ ሰው ወደ ላይ ዘረጋች። ጥፍሮቿ እፈር ቅመዋል። መዳፎቿ እቧራ ለብሰዋል።

‹ሰማይ?›

‹አዎ ሰማይ ተደፋብኝ› ቁና ቁና ትተነፍሳለች።

○

ምን እንደሆነ አላወቅኩኝም። እንዳች መጥፎ ነገር እንደ ተከሰተ ግን ልቤ ጠርጥሯል። እንደ ኤሊ እየተሳብኩኝ አጠገቧ በዝግታ ተቀመጥኩኝ። የያዝኳቸውን ደብተሮች ባቴ ላይ አደረግኳቸው። የምላት ጠፍቶኝ በዓይኖቿ ሰርቄ እያታለሁ። መዐት እንደ ወረደበት ሰው ተከዛለች። ሰውነቷ ይርዳል። እግሮቿ ያረግዳሉ። ዓይነ ውኃዋ ላይ ነገን ያለማወቅ ፍርሃት ይንከባለላል። እጇን ሰድጂ ገላጣ ከንዲ ላይ አሳረፍኩኝ። ደም ሥሮቿ እንደ መቆጣት ብለዋል። ጣቶቿ ይንቀጠቀጣሉ። ዞራ በዝምታ ትንፋሽ እስኪያጥረኝ ወደ ደረቷ አስጠግታኝ በስስት አቀፈችኝ። መልሼ እጥብቄ እቀፍኳት። ደብተሮቼ ከታፋዬ ላይ እየተንሸራተቱ መሬት ላይ ወደቁ። መተቃቀፋችን ከፍቅር በላይ ፍርሃት ነበረበት። በእናቴ እቅፍ እንዳለሁ የዓለም ምጽአት እንዲሆን ተመኘሁ — ግን አልሆነም።

‹አባትህን እያየሁት እምጥ ይግባ ስምጥ ሳላውቅ ዕልም አለ›

‹እ... ማለት?›

‹እዚያች ደፍ ላይ እንደ ቆመ ዳዊቱን እየደገመ ድንገት ከዓይኔ ተሠወረ›

ብዬ አባቱ ለጸሎት የሚቆምበትን የተለመደ ስፍራ ተመለከትኩ። እግሩ የሚረግጥበት ቦታ ላይ መሬቱ ትንሽ ተምሶ ጉድጉዷል። ከሠርጓው የወጣለት ጥቍር አፈርም እዚያው አካባቢ ተበትኗል።

‹እየር ውስጥ ሰረገ። እያየሁት ረቀቀብኝ። እብስ ብሎ ጠፋ። ሰውን ያህል ነገር ከተቀመጠበት ቦታ እንደ ዕታ አጣሁት ብል እኮ አሁን ማን ያምነኛል? እንደ ቀባጣሪ አልቆጠርም? የእኔን እውነት እንዳልናገረው የእኔው ብቻ ነው። እማኝ ካልጠራሁለት ሰሌላው ዓለም ትርጉም የለውም። በጊዜና በቦታ ለታሠረ ሰው የእኔ እውነት ምኑ ነው? የሰውስ ይሁን የእግዜሩ አልባሰም? ቆይ ትዕንግርት ሲያደርግ አያስጠነቅቅም? ለሁሉን ቻይነቱስ ልክ አይሰጥም? ለከሃሊነቱ ልጓም የለውም? ወሰን አይከልልም፣ ድንበር አያበጅም? ማለት እንዴት ያለ አበሳ ነው? ...ብችልም ‹ይሄን› ባላደርግ ጥሩ ነው። ሰዎች መሸከም አይችሉትም አይልም? ከራሱ ጋር አይነጋገርም? አይመክርም? አምላካዊ ጉዱን ለእኔ ለምስኪኗ ለምን ያከናንበኛል? አልደረስኩበት ለምን ይደርስብኛል? አላማረርኩት ለምን ያማርረኛል? ቆይ ለማን ምን ብዬ እነግራለሁ? እዚህ አገር ማን ነው ዘመዴ?› ጉንጯ ላይ እንደ ጠመለገ ቅጠል የረገፈ እንባዋን አበሰች። በድንገትም ግራ እጇን አፈፍ አድርጋ ያዘችኝ። ‹ግ› ዬ አንተ ማን ታምነኛለህ? ይሄን እውነት ትቀበለኛለህ አይደል?›

‹የቱን እውነት?›

‹የእኔን እውነት ልጄ›

‹እማይ አሁን እንድትረጋጊልኝ ብቻ ነው የምፈልገው›

‹ንገረኝ ታምነኛለህ?›

‹ለምን አላምንሽም እማ?›

‹ዝም ብለህ እንደምታምነኝ ብቻ ንገረኝ› በዓይኖቿ ተማጸነችኝ።

‹እምንሽለሁ እማ›

ይህን ያልኳት እናት እመነኝ ስትል እንደ ታሳ በዝምታ ስለምትታመን ነው። የትኛው ልጅ ነው እናቱ 'ታምነኛለህን' ስትለው 'ቅድሚያ ማስረጃ አምጪና' ብሎ የሚጠይቅ? ሳንሚንት ያለማስረጃ የምናምናቸው ሰዎች አሉ። የአባታችንን ወላጅ አባትነት ጠይቀን አልተቀበልንም። በስሙ የተጠራነው እንዲሁ በእምነት ነው። እናቱ ከአብራኳ ክፉይ አንደበት የወጣውን ቃል አልፈተነችውም። ምክንያቱም አንዱ ወገኛ ሲተርት 'ልጁን የማታምን እናት ራሷ ሌባ ናት' ብሏል። እንዳንጠይቅ በተረት ተሸብበናል። በቤተሰቡ ወንጀለኝነት ላይ የሚመሰክር ልጅ እናይም። 'ምንም ቢጠም መንገድ፣ ምን ቢከፋ ዘመድ። የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል።' የጨፍ ቅንጣት ከማያስገባ የእውነት ወገንተኝነት ይልቅ ዱቤ የሚያሰጥ ዝምድና ይመረጣል። በአፈ ጮሌ ሰው የተሸመነ ተረት ተረት አገር ይገዛል። የሐሳብ ሥርዓት ይፈጥራል።

○

የሰማችው ታል ለአፍታ ከጭንቀት ያረጋጋት መሰለች። ያን ምሽት ከተቀመጠችበት ሳትነሣ የአባቴን ትስብእት[26] በተስፋ እየተጠባበቀች ከደጅ አደረች። አጠገቧ ብቀመጥም ያፈጠጥኩት ትርጉሙ ያልገባኝ የረጋ ነፋስ ላይ ነበር። ለእኔ አባቴ በአካለ ሥጋም እያለ ሰውተ አልነበረውም። ከለባዊነቱ አላካፈለኝም። እንዲያውም እሳትነቴን ያጠፋ ቀዝቃዛ ውኃ ነበር። የእናቴን

[26] አካላዊ መገለጥ

መንከታተት ሳይ ግን እንጀቴ አረረ። ለአባቴ ያለኝ የጥላቻ እርኪም በእጥፍ ጨመረ። ልቤም እንደ መሬት ጉቃቃት ተሰነጣጠቀ። አባቴ ለእግዜር ቅዱስ ቢሆንም ለእኔ ግን እርኩስ ነው።

○

በሳምንቱ እንድ እንግዳ ሕልም አለምኩ። እዚያች አፈሯ የተማሰች ጎድጓዳ ቦታ ላይ ለምለም የሱፍ አበባ በቅላ ተመለከትኩ። ሕልሜ ውስጥ ዕራቁቴን ቆሜያለሁ። በጠባሳ የተወረረ ሰውነቴን አያለሁ። ጠባሳውን ከአባቴ እንዳገኘሁት አስባለሁ። እናደዳለሁ። ለምን እንዲህ አደረገኝ? እያልኩ አብስከሰካለሁ። የጽጌው የፈቱ ክበብ ወገግ እንዳለ ፀሐይ ወደ እኔ አቅጣጫ እያበራ ወደ ጫማዬ ያዘምማል። በሕልሜ በስተመጨረሻ ጀርባዬን ሰጥቼው እሮጣለሁ። አበባዋ እንዳልነበረች ትረግፋለች።

○

ይህን አስተርእዮ ለእናቴ አልነገርኳትም።

ጋይትር ለማለት የከበድዎት በደለኛ ሰው በሕይወትዎ የሉም እስኪ ፈለግ ፈለግ ያድርጉ ለመሆኑ ይህቺን አንገትዎ ላይ ያለ ጥሩር ጠባሳን አይተዋል? ምንንና ማንን ታስታውሰዎታለች መቼም መስታወት ፊት በቆሙ ቁጥር የምታስጨንቅዎት መረረ እውነት ይኖራል። እኮ ይንገሩን አይሩሩ። ነፍሬ የመዘዘብዎት ግን ነውን ሃሃ... እንዴት ይረሱታል? እሺ.... ይህቺ ደረትዎ ላይ ሰያፍ የተጋደመች ጠባሳስ የማን ስጦታ ናት? በሉ ይንገሩን እኮ የአባትዎ ገዳይ ስሙ ማን ነው? ያውቁት የለምን ጎንዎ ላይ ከዛ ያረፈው ሰምበርዎስ? እህ... ወንድ ልጅዎን በመኪና ገጭቶብዎ የተሠወረው ሰካራም ሹፌርስ? ልብዎን የነፈሰው የማይሽር ጠባሳስ ከየት ነው ያገኙት? እ...ሴት ልጅዎን ያባለገብዎት የትርፉ ዘመድዎስ? ይህቺ ጉልበትዎ ላይ እንደ ዝንብ ያረፈች ሞሪትስ የአደራ ገንዘብዎን በልቶ የካድዎት ታማኝ አገልጋይዎስ?

○

እስከ መቼ ድረስ ለበደለዎት ሰው ይቅርታ ሳያደርጉ ለመቀየስ አስበዋል?

[27] ማቢያ 7

አሳት ወይ አበባ[28]

ኧ

የፀደይ ተለማምጦ ቢራቢራዎች በነፋስ እየተገፉ ከፈኩ ጽጌያት ላይ በናፍቆት ሳይመረመሩ፣ ወፎች በሰማይ ላይ ነገሥቱውን እያማከሉ መስከረምን ስላመጣው የነፃምት ግለኝ ሳይዘምሩ፣ አበባዎች ከምድር ማጎፀን ያለምጥ ተወልደው መስከኩ ላይ ሳይነግሡ፣ ለመስቀል ወፍ መስከረም ጠብቶላት በመስቀል ሳትታይ፣ ሕፃናት ጅራፍ ሳያማቱ፣ እሸት ሳይሻተሉ፣ የበሄ መልሙል ሳይዘጋጅ፣ 'የአበባ አየሽ ወይ?' ከበሮ ሳይደምት፣ ረከቦት ሳይቀርብ፣ አራቲና ጠጅ ማር ሳይጎዘጎዝ፣ ኑግ ተለጥልጦ ከቂጣ ጋር ሳይቀርብ፣ ዕጣን ሳይጤስ፣ ሰንደል ሳይለኮስ፣ ፈጦ ተፈትፍቶ በባዶ ሆድ ሳይበላ፣ የደረቱ እናቶች ቅቤ ሳይቀቡ፣ ዶሮዎች ሳይታረዱ፣ ችቦ ከቋቱቱ፣ ከከሰና ከነጥከታ ሳይበሸጭ፣ ተለኩሶ ወደ ቤት ወደ ደጅ ሦስቱ ሳይገባ፣ ሳይወጣ፣ የገንፎ ምንቸት ወደ ማጀት የጎመን[29] ምንቸት

[28] እገሸራ 8
[29] ስንቆ

ወደ ደጅ ሳይባል፣ 'ኢዮሃ እበባዬ' ሳይዘምር፣ ተራቁቶና በወሐይ ተንገርግቦ የነበረው ገላጣ ሻርንጉርጉር ሜዳ አረንጓዴ ካባና ጌጥ ሳይለብስ፣ ጨለማ ሰማይ ላይ ጮራ ሳይፈነጥት፣ ምድር በብርሃን ዓይነ ርግቧ ሳይገለጥ፣ ገና ድርርርርሮ በእሳት አውታር ታጥሬ ሕዋው ላይ የምትንሳፈፍ እንዲት አደይ አበባ ነበረች።

○

የዚህ ቀን ትዝታው እሰኝ። እርሱ ከመደቡ ላይ በውድቅት ተነሥቶ ሸማውን አጣፍቶ ተከናንቦ ወጣ። ይመለሳል ብዬ ጋደም ብዬ ብጠብቅ፣ ብጠብቅ ድምፅ የለም። ከአልጋዬ ወርጄ ጋቢዬን ደረብኩኝ። በሩን ከፍቼ በረንዳ ላይ ቆሜ አማተርኩኝ። ቀዝቃዛ መንገደኛ አየር እያቷጨ በአጠገቤ ያልፋል። ምድሩ ድንግዝግዝ ጨለማ ነው። የወንዛወንዙና የቅጠላቅጠሉ ፀፀታ ዜማ፣ የውኖና የቡላል ጉርምሩምታ ይፈራረቃል። ጅቦች ይጮኃሉ። እየቆየ በየመሐሉ ሁሉ ነገር ለአፍታ ጸጥ ይላል። ተፈጥሮ ዝም ሲል ያስፈራል። በሆዱ ያሚረር ይመስላል።

○

ከምን ጊዜው በላይ ብቸኝነትን ፈራሁ። ሆዴ ተንቦጫቦጨ። እዚህ ሰብሳብ ላይ ልጄንና እርሱን እየጠበቅኩ ያሳለፍኳቸውን ወቅቶች አስታውሳለሁ። ከእናትነት አንጀቴ ተጨንቄ እልቅሻለሁ። ሕይወቴ ጥበቃ ነው። ሽፋሽፍቴ የዓይኔን ብሌን እንደሚጠብቁት ጆሮዎቼ የእርሱን ቃል ይጠብቃሉ። የልጄን ፈገግታ እንደ ምስል ከታቢ በሕሊናዬ ሰሌዳ ልስል በጉጉት እጠብቃለሁ።

እጨነቃለሁ። 'ሰለቸኝ' ብዬ ልቀመጥን አላውቅም። በረንዳው ላይ ተገትራ እቆማለሁ። አንድ ቀን የጠበቅኩት ቀርቶብኝ ተስፋ ባደረግኩበት ልክ እንዳልሰበር እሰጋለሁ።

○

ሰማዩ ከግራጫነት ወደ ደማቅ ብርሃናዊነት ፈግጓል። ከርቀት ነፋስ የሚያመጣውን የፈረስ ኮቴ ጆሮዬ ያደምጣል። ልቤ ያሰባል 'በዚህ ጽልመት የማን ፈረስ ነው ደግሞ?' እጠራጠራለሁ። 'መርዶ ነው? እኮ የማን?' ልጄ ተኝቷል። ጋላቢው ሲቀርብ እርሱ እንደሆነ አወቅኩኝ። ሸማው በሰማያዊ ብርሃን ተነክሯል። ገጹ ጸዳል ያበራል። ፈረስ ሲጋልብ አይቼው አላውቅም። ቀድሞ ነገር ፈረሱም የተገዛ ሳይሆን እግር ያመጣው ነው። በቍስል ተወርሮ፣ በዝንቦች ተከብቦ ደጃፋችን ላይ እንደ መጻዒ ተጥሎ ነው የተገኘው። እንደ ሰው አስታሞ ፈወሰው። ከገብሱ፣ ከእጃው፣ ከሲናሩ፣ ከእሞሌው ቀለበው። ካለዚያ ቀንም እልጋለበውም።

○

ይኼ ፈረስ በሆነ መንገድ እኔን ይመስለኛል። እርሱ ያገኘኝ በሰባት ወንዶች ተደፍሬ ከተጣልኩበት ማጥ ውስጥ ነው። የተደፈርኩት ተወልጄ ባደግኩበት ቀዬ ነው። ማን ማን እንደሆኑ አውቃለሁ። ሰባት የአገሬና የወንዜ ልጆች ናቸው። አብረን እየተጫወትን፣ ከብት እያገድን በጋራ አድገናል። ከአንድ ምንጭ ጠጥተናል። ልጆች ሳለን እንደ ወንድምና እኅት ነበርን። ከከፉ ነገር ጠብቀውኛል። ሳለቅስ አባብለውኛል። ስከፋ አስቀውኛል።

ከወደቅኩበት እንሥተውኛል። ሁሉ ነገር እንዴት ይቀየራል? ትዝታችንን መካድ እንችላለን? ስናድግ አንዳችን ለአንዳችን ባዕድ እንሆናለን? እንዲተውኝ የለመንኳቸው ስማቸውን እየጠራሁ አይደለ? የማውቀውን ሰው እንጂ የባዕድን ስም ከየት አመጣለሁ? በድንቁርና ታውረው ባይገባቸውም የደፈሩት እጎታቸውን ነው። የተደፈርኩት በወንድሞቼ ነው። በማይደገመው ሕይወት ውስጥ የተደፈረች ሴት ሆኜ እንዳልፍ ከጀርባዬ መክረውብኛል። በጊዜው ሥቃዩ ጸንቶብኝ የወደቅኩበት ግር ብሎኛል። የእናቴ እንስራ ተሰብሮ ተበታትኗል። ጭኔንና ወገቤን ነቆኛ ያመኛል። ከግሥሮው ጋር በጹላ የተመታሁበት ጀርባዬ ቆስሏል። ራሴ ይዞራል። ዓይኖቼ እንባን ይሞላሉ። ከሆዴ ፈንቅሎ የወጣ ምሬት ያስለቅሰኛል። የነቀነቁት የግቢያችንን አጥር አይደለም። በኃይል ገብተው ያሳደፉትና ያፈረሱት ጎጆዋችንን አይደለም። አጥር በአጥር ይተካል። ከቤትዎም ቢፈናቀሉ ተሰደው ሌላ ስፍራ አገንት ማስገቢያ ጎጆ ይቀልሳሉ። ሰውነትዎ ሲደፈር ከገዛ ገላዎ ወደ የት ይሸሻሉ?

○

ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ። ከክብሬ በተዋረድኩበት ምድር ካረከሱኝ ሰዎች ጋር እንጀራ መቁረስን አልፈልግም። መደፈሬ ሳያንስ ቀሪውን ዘመኔን በሀፍረት ተሸማቅቄ ለመግፋት ስገደድ ታይቶኝ ውስጤ ተንገፈገፈ። የበደሉኝ ቀና ብለው ሲሄዱ አገንቴን በምደፋበት ማኅበረሰብ ውስጥ መኖርን አልሻም። ለምን? እያልኩ በሚጠይቀኝ ክፉ ዕጣ እምርሬ እዘንኩ። ለመበደሌ ‹የእጅሽን

አገኘሽ› ሳይለኝ ድምጼን የሚሰማኝ ሰው ማን ነው? ካልጠፋ ሰው የገዛ ራሴ ውድቀት ላይ እንዴት እሚራለሁ? ሴትነት እንደ ወንድነት ሁሉ ከፈጣሪ የተሰጠኝ ስጦታ እንጂ በነፍሴ ክፉ ሥራ ሠርቼ የደረሰብኝ እንዳች መርገም አይደለም። ከእኔ ይልቅ እነርሱ ይታመናሉ። ሴትነቴ ውስጥ የብልግና እርሾ እንዳለ ሁሉ ያሽሟጥጡኛል። በሌሎች እጎቶቼ አይቼዋለሁ። በዚህ መንገድ ግለፍ አልፈልግም። ዓይኖቼን ወደ ሰማይ እንጋጠጥኩ። ሳምንህ ኖሬያለሁና እንዴ ታመንልኝ ብዬ ፈጣሪን በድፍረት ለመንኩት። ከዚህ መከራ የሚያወጣኝን ረዳት እንዲልክልኝ ጠየቅኩት። መኖር የምፈልገው ስም አጠራሬ ከማይታወቅበት ምድር እንደሆነ እምርሬ በእንባ ነገርኩት። ከዚያ ቀጥሎ የተፈጠረውን ነገር በውል አላስታውስም። ራሴን ልሳት የሰመመን እንቅልፍ ይውሰደኝ? እንጃ። የነቃሁት ከሁለት ቀናት በኋላ በእርሱ ቤት ውስጥ ነው። ከመራት በኋላ ማርገዜን ተረዳሁ። ልጄ ይሄን እውነታ አያውቅም። ከተመረቀ በኋላ ልነግረው እየጠበቅኩ ነው።

○

ፈረሱን ከጋጣው አሥሮት ወደ ቤት አቀና። እንዲት እንደ እሳት የምታበራ አደይ አበባ አውጥቶ በዝምታ ሰጥቶኝ ወደ ውስጥ ዘለቀ። እንባ ቀደመኝ። በጊዜው ያስደነገጠኝ ነገር የእርሱ የቀኝ እጅ በእሳት መለብለቡ ነበር። የለበሰው ሸማ ጫፍ ጫፉ እንደ ማሰሻ ጨርቅ ተታጥሏል። ያቺ የእሳት ነበልባል የጉረሰች አደይ አበባ እርጅና ሳያገኛት ዛሬም ሙዳዬ ውስጥ በምሥጢር እያበራች ተቀምጣለች።

እርሱ በተመወረ ከወሩ በአራተኛው ቀን ምስር ለትሚ ወደ ቤት ስገባ ምኝታ መደቡ ላይ በቢጫ ብርሃን የተኳለች አደይ አበባ በቅላ ተመለከትኩ። 'በስመአብ!' እጀቼን አመሳቅዬ አማተብኩ። መደቡ ሰሌን የተዘረጋበት የጭቃና የድንጋይ ድልድል ዝርግ ጣጋ ነው። በዚያ ላይ ወቅቱ የበጋ ወር አጋማሽ ነው። በእምስተኛው ቀን ከእንቅልፌ ስነቃ ሁለተኛዋ አበባ ብርቱካናማ ጸዳል ለብሳ እዚያው ጭንጫ ላይ በቂንጥ አብባለች። በስድስተኛውም፣ በሰባተኛውም፣ በስምንተኛውም... ቀን ሌላ አበባ።

○

ይህን አስተርእዮ ለልጄም አልተናገርኩም። ስወጣ ስገባ በሬን እከረችማለሁ። አደይ አበባዎቹ እንደ ዐሸን ይፈላሉ። ምሥጢሬን በዝምታዬ እሸብባለሁ። እስከ ዕድሜዬ መጨረሻ ድረስ በተስፋ እጠብቀዋለሁ። አንድ ቀን ይመጣ ይሆናል።

[30]የጠበቃችሁት ሰው በሰዓቱ ይመጣል? የተገባላችሁስ ቃል ሥጋ ይለብሳል? የአንዳንዱ ሰው ቃል እንደ ስንኩል መንፈስ ነው። ከአፍ ቢወጣም ምድር ላይ ሥራ አይሠራም። 'ይደረግልኛል' ያላችሁት ነገር በሐሳብ እንዳልነበር ሲቀር አላያችሁም? እንደ ጉም አልተበተነም? እንደ ሙት ቃል አልተዘረረም? በሌሎች ሰዎች ሕይወት ውስጥ እንደ ትርፍ ሰው አልተቆጠራችሁም? ይዞኝ ይሄዳል ያላችሁት ሰው ጥሏችሁ አልኮበለለም? እንድትታዩ በማትፈልጉበት ዓይን አልታያችሁም? ከሰጣችሁት ያነሰ አልተቀበላችሁም? ባልፈለጋችሁበት መንገድ አልተፈለጋችሁም? ስንቱን እንዳልዘከራችሁ ከነመፈጠራችሁ አልተዘነጋችሁም? እኮ ስትሰበሩ ማን ፈለጋችሁ? ማን እደመጣችሁ? ቸል ስትባሉ ማን ትኩረት ሰጣችሁ? ስትራቆቱ ማን ሸፈነላችሁ? ሲያስጠላባችሁ ማን ነው ያስዋባችሁ? በተጠጋችሁበት ልክ አልተገፋችሁም? በለመናችሁበት ልክ አልተጨከነባችሁም? ሰው ማመናችሁን ስሕተት ሆኖ አላገኛችሁትም? የዚያ ሰው አለመታመን የእናንተን በሰው ተስፋ ማድረግ እንድትረግሙ አላደረጋችሁም? እና ታዲያ ስለ ተስፋ ተጋንኖ የተሰበከ አይመስላችሁም?

[30] ማቢያ 8

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ[3132]

መንገዶችን

አራምባና ቆቦ ያሉ ሰዎች እንዴት ይገናኛሉ? ከሩቅ እያየኋት ወደ 'ዲ' መንገድ ተሻግሬ ለመሄድ አፈራ ነበር።

○

የምወዳት ሴት ያችያትና ወዲያ ማዶ። ለብቻዋ እንደበቀለች እንደ እንዲት አደይ አበባ እግሯን መሬት ላይ በቂንጥ ተክላ። እኔ ወዲህ ማዶ በሥውር ቆሜያለሁ። በነፋስ እንደ ተምላ ፊኛ ወደ ሕየ እንዳትነጠቅ በስስት እያታለሁ። በፍርሃት እጠብቃታለሁ፣ ያልተጠጋኋት አቅመ ቢስነት ይዞኝ አይደለም። ቀርቤ ልላት የምችለው ነገር ጠፍቶኝ ነው። ማለት ሰዎች እንዴት ብለው ነ

[31] እንጀራ 9

[32] ትዝታ —ማሕሙድ አሕመድ

ወደማያውቁት ሰው ዓለም የሚገቡት፣ 'ሃይ[33]' ብለው በእንዲት የሰላምታ ቃል ብቻ የትውውቅ በር ለመክፈት ቢሞክሩ እንደ ድፍረት፣ ዘው እንደ ማለት አይቆጠርባቸውም?

○

እንድ ውብ ምሽት 'ዲ' እኔ ከነበርኩበት ከ'ጃዝ' ካፌ' ወጥታ ወደ ግቢ መንገዴን ስታደርግ ተከተልኳት። 'ጃዝ' እኔም የምወደውና የማዘወትረው ካፌ ነው። ከቡና በወተታቸው ውጪ ከእነ ማይልስ ዴቪስ 'ሶ ዋት'፣ ከፍራንክ ሲናትራ 'ፍላይ ሚ ቱ ዘ ሙን'፣ የሬይ ቻርለስን 'ጆርጂያ እን ማይ ማይንድ'፣ የስታን ጌትዝንና የጆዋንዝ ቤርቶን 'ዘ ገርል ፍሮም ኤፓኔማ'ንና ሌሎችንም አድምጩ ያወቅኩበት ቤት ነው። በሳክስፎኒስት ጌታቸው መኩሪያ 'የገነት ሙዚቃ፣ እምባሰል፣ ትዝታ፣ ብቻዬን ተከገር፣ ዓይኖቼ ተራቡ...' እና በሙላቱ አስታጥቄ[34] 'የከርሞ ሰው፣ የግሌ ትዝታ፣ ካሳለፍኩት ሁሉ፣ ትዝታዬ አንቺ ልጅ..' የሙዚቃ መሣሪያ ዜማዎች እንደተመሰጥኩ የካፍካን፣ የጋብሬል ጋርሺያን፣ የጆርጅ ሉዊስ ቦርጌስን፣ የሚላን ኩንዴራን፣ የሙራካሚን፣ የጂ.ዲ ሳሊንገርን፣ የጸጋዬ ገ/መድኅንን፣ የገብረ ክርስቶስ ደስታን፣ የደበበ ሰይፉን፣ የሰለሞን ደሬሳን፣ የባለቅኔ ሙሉጌታ ተስፋዬን፣ የጸኖቸው ወርቁን፣ የጀርሶ ሞት ባይናር ኪሩቤልን፣ የስብሐት ገ/እግዚአብሔርንና የሌሎች ደራሲያንንና

[33] Hi

[34] ኢትዮጲክስ 4 — ኢትዮ ጃዝ

ገጣሚያን ሥራዎች እንድ፣ ሁለት እያልኩ ያነበብኩትም እዚሁ ካፌ ነበር። ጊዜ እንዴት ይበርራል?

○

ሐሳብ ከፍላ ስትወጣ ተከትያት ተነሣሁ። የመንገድ መብራቶች ደብዛዛ ብርሃናቸውን የምሽቱ ጨለማ ላይ ያርከፈክፉሉ። ሁሉ ነገር ድርና ውብ ይመስላል — ብላክ ኤንድ ዋይት። የጎዳናው ብቸኝነት መንፈስን ያቀረዝዛል። 'ዲ' ነጭ ሹራብ ለብሳለች። ጥቁር ቲሸርት አድርጌያለሁ። እየሩ ይበርዳል። እጆቼን የሱሪዬ ኪሶች ውስጥ ከትቼ በለዘብታ ከጀርባዋ እራመዳለሁ። 'ዲ' በእንድ ጆሮዋ የሙዚቃ ማዳመጫ አድርጋ ሙዚቃ ትሰማለች። የማንን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም። ግን እያደመጠች ነው። እንገቷ ወደ ቀኝና ወደ ግራ ትከሻዋ በስልት ይነቃነቃል። አብሪያት እየሰማች ያለችውን ዘፈን ለማድመጥ ባልታደል እንኳን ቢያንስ 'ያ' ሙዚቃ የማን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉቻለሁ። በድንገት በመንገድ ላይ የወደቀ ደረቅ ቅጠል ረግጬ ኮሽታውን ሰምታ ከመቅጽበት ዞረች — ደነገጥኩ። የሙዚቃ ማዳመጫዋን እውልታ በቅጥታ እየተራመደች ወደ እኔ እንደ ግዙፍ ጥላ መጣች። እየቀረበችኝና እየተጠጋችኝ በሄደች ቁጥር እያነስኩ ጠበቅኳት። ተጠግታኝ ቆመችና አየችኝ። እያደመጠች የነበረው ሙዚቃ የድምፁ መጠን ቢጻከምም በስሱ ይሰማኛል። የዶኖቫን 'ካች ዩ ሞንድ' ነበር።

○

'እየተከተልከኝ ነበር?'

ብላ ጠየቀችኝ። ድምፆ ያምራል፣ ያስፈራልም።

'እ.. እ?'

ተርበተበትኩ ሐሳቤ ዘፈኑ ላይ ነበር።

'እየተከተልከኝ ነበር ወይ?'

ደግማ ጠየቀችኝ።

'አረ አይደለም። መንገድሽ መንገዴ ስለነበር ነው'

ብዬ ዋሸኋት።

○

በዚያን ምሽት ፊቱ ላይ ምን እንዳየች አላውቅም — ሳቀች። አብራያት ፈገግ አልኩኝ። ምን አልባት ውሸት ላይ ጎበዝ አይደለሁም። እስከዚያች ዕለት ድረስ ሰዎችን የምዋሸበት ምክንያት አልነበረኝም። የዚያን ምሽት ግን በትክክል ዋሸሁ። ‹ዲ›ም ለመጀመሪያ ጊዜ እንድ ሕፃን ለመዋሸት ሲሞክር ያየች ያህል በሹፈት ሳቀች። ሳቋም የሚወደድ እንጂ የሚጠላ አልነበረም።

○

‹ካፈው ውስጥ ስታየኝ አይቼሃለው›

አለችኝ።

‹እ..›

የምላት አልነበረኝም። የከንፈሯን እንቅስቃሴ፣ በፈገግታ የተነከረ የአወራሯን ስልት እያለሁ። በዚህ ቅርበት ተጠጋግተን አናውቅም። አልተጨባበጥንም። አልተሳሳምንም። እጅ ለእጅ አልተያያዝንም። ገላችን አልተነካካም። አሁን ግን እጅግ ተቀራርበናል። ይህ ርቀት ለእኔ እንደ ትልቅ ቅርበት ነው። አጠገቧ ነበርኩኝ። እየቀዘቀዘች የምትሞቅ፣ እየደበዘዘች የምትደምቅ፣ እየከሰመች የምትፈካ፣

ከሙዚቃ ኖታነት ሥጋ ወደ ለበሰ ሰውነት የመጣች ትዕንግርተኛ ልጅ ናት። በመካከላችን ካለው ቅርርብ በላይ ሌላ ተአምር አልነበረም። ትላንት አራምባና ቆቦ ነበርን። ዛሬ በአንድ ክንድ ርቀት ፊት ለፊት ቆመናል። መደነባበሬና መፋዘዜ ሲበዛባት...

‹ዲ እባላለሁ› ብላ እጁን ለሰላምታ ዘረጋች። ስሜን ነግሬያት ተጨባበጥን።

○

እንዲህ ነበር ወደ አንድ መሥመር የመጣነው። ዓለማቶቻችን እንደ ቡና በወተት የተካለሱት። ለብቻዬ ስሆን ልቤ ላይ የጣለችውን የትዝታ ክብደት እመዝናለሁ። ‹ካች ዘ ዊንድ› ን ፈልጌ አደምጣለሁ። ፈገግ እላለሁ። ‹ዲ› በዘፈኑ ግጥሞች መካከል ዶኖቫን ስሟን ስለሚጠራ በተለየ መንገድ እንደምትወደው ነግራኛለች።

○

Diddy di dee dee diddy

Diddy diddy diddy dee dee dee

ጀርባዋ የረሾም ጊዜ ትዝታዬ ነበር።

[35]ኮቴያችን በድን መሬት ላይ ያርፋል። ዳናችን በነፋስ እየተጠረገ ከዓይን ይሠወራል። መንገዱን አቋርጠን እንዳልመጣን ያሳረፍነው አሻራ በዋዛ ይጠፋል። ጊዜ አልፎ እኛም እዚህ መንገድ ላይ እንድ ሰሞን ነበርን ብንል ማን ያምነናል? ጎዳናው ላይ ከነበርን ያሳረፍናቸው ዳናዎቻችን የታሉ? ከሌለንስ ‘ያንን መንገድ’ ሳናቋርጥ በምን ተአምር እዚህ እንዴት ደረስን? በምድር ላይ የማይጠፋ አሻራ ማሳረፍ ከባድ ነው። ተልከን ከሄድንበት ስንመጣ ከላኩን ሰዎች አፍ መሬት ላይ የተተፉት ምራቆች ደርቀው ይጠብቁናል። የምናገኘው ሽልማት የለም። ከመኖር የምናተርፈው ትዝታ ብቻ ነው። መንገዳችን እንደ ትዝታ ነው። አንዴ ብናልፈውም አንረሳውም። በትውስታዎቻችን ምሪት ደጋግመን እንመላለስበታለን።

[35] ማቢያ 9

ልብ የላትም[36]

ምን እንዲህ ያደርጋታል?

‘ዲ’ መልኳ ውኃ ውስጥ እንደ ወደቀ መሐልቅ[37] ነው። ታምራለች፣ ታጓጓለች — ግን ደግሞ ቀዝቃዛ ናት። ሁሌም በሁለት ነገሮች አማሃይ እንደዋለለች ነው። በመጥፎና በጥሩ፣ በጎዘንና በደስታ፣ በማስታወስና በመርሳት፣ በመወሰንና በአለመወሰን። ሙሉ ሆና አታውቅም። ሳቋም እንባዋም የተገመሰ ነው። በወጣት ገላዋ ውስጥ መሮጥ እየቻለች፣ የሚያንከረፍፉት፣ መሳቅ እየቻለች የሚያስተክዛት ማንም የማያውቀው ያረጀ ሰው

[36] እንጀራ 10

[37] የብር፣ የናስ ክብ ሳንቲም

ነፍስ አላት። አዕምሮዋ ለመብረር ሲሞክሩ እርስ በእርሳቸው በሚጋጩ ቢራቢሮ ሐሳቦች የተሞላ ነው።

○

የዐረፋ ኳሶች፣ የዛፍና የአበባ ቅጠሎች መዋቲነትን፣ የሙዚቃ ቅምሻንና የቡና ጣዕምን፣ ቡና ለሰለ ተደርጎ ሲቆላ ያለውን ድምፀት፣ ዕድሜ ጠገብ ሙዚየሞችንና ሐውልቶችን፣ የጎብስት ዳቦ ስስነትንና ልመት፣ የተለያየ ቀለም ያላቸው የጫማ ክሮችን ርዝመትና ልፍስፍስነት፣ የአፉዬ ገላን ለስላሳነትና ኢምንትነት፣ የሲዲን ቀስተ ደመናዊ ከበብንና የካሴት ተጠንጣኝነትን፣ የቢጫ ቀለማም ሹራብ ፍካትን፣ የሰማያዊ ጅንስ ጃኬት ስክነትና ውበትን፣ የቡኒና ጥቁር ከፋይ ቡትስ ጫማዎቿን ክብደት፣ የረዣዥም ካልሲዎቿን ሙቀትና አስቂኝነት፣ የጥቁር ድመቷን ተጠጊነትና ዝምተኝነት. . . ትወዳለች።

○

በቀን ውሎዋ የተጨማደዱ የአሮጊትና የሽማግሌ ቆዳዎች፣ ስፌታቸው ተተልትሎ ሲሳብ የተሸበሸቡ ሰደርያዎች፣ ሹራቦች፣ ቀሚሶች፣ ሱሪዎች፣ የሸረሪት ድሮች... ያየችበት አጋጣሚ ካለ ሌሊት በእንቅልፏ መሐል ትረሰሻለች። ተጋጭተው የተጨረማመቱ መኪናዎች፣ የተሸራረፉ የብርጭ ከናፍር ደርዞች፣ በጊዜ ሂደት የተሰነጣጠቁ፣ ዝገት የሚያገፉ ሕንጻዎች፣ የእንጀራ ሽህ ዓይኖች ...ትውስታ እረፍት ያሳጧታል። ሌላው

በማታውቀው ምክንያት ከልጅነቷ ጀምሮ የጥሩምባ ድምፅ ስትሰማ ልቧ ይርድባት ነበር።

○

ጥሩምባ ትፈራለች። ሰው ሲሞት የሚነፋ ነገር እንደሆነ ሳታውቅ በፊት ድምፁን ስትሰማ እየጮኸች አልቅሳለች። ጨዋታዋን አቋርጣ 'እሪሪ' እያለች ወደ ቤት ገስግሳለች። ተኝታ በእንቅልፏ መሐል ብትሆንም ጥሩምባ ሲለፈፍ እያለቀሰች ትነቃለች። ይህን ባሕርይዋን የሚረዱ የሰፈር ሰዎች 'ምን አውቃ ነው አሁን?' እያሉ ያዝኑላት፣ ይስቁባት ነበር። እንግዳ ነገር ነው የጥሩምባ ድምፅ ስትሰማ የምትገባበትና የምትወጣበት ጨንቋት የምትራወጥ ልጅ ማየት። ልቅሶዋ ሲሰማ አካባቢው ጸጥ ይላል። ጥሩምባ ለፋፊው የልቅሶው መነሻ ምክንያት እርሱ እንደሆነ ሲገባው ደንግጦ ያቆማል። መልእክቱን በቃል አሰምቶ ይሄዳል። ዛሬ ዛሬ ይሄ ፍርሃቷ እንደ ድሮ ጠንካራ አይደለም። አያስለቅሳትም። አያስጮሃትም። ብቻ አንዳንድ ጊዜ ሰውነቷ በስሱ እንደ መንቀጥቀጥ ይልባታል። ሌሊት ከሆነ በዝምታ ትነቃለች። የጠፋባትን እንቅልፍ ፍለጋ አልጋዋ ላይ ትገላበጣለች። ከተደራራቢ አልጋዋ ላይ ኢንተርኔት ስትጠቀም የምታድር 'ሊ' የምትባል የዶርሟ ልጅ ድምፆን ሰምታ ትጠይቃታለች።

'ሕልም ነው?'

‹እም ተራ ሕልም ነው።›

‹ዲ› ሕልሞቿን ተራ ብላ ብትፈርጃቸውም ፍጹም ተራ አልነበሩም። ተኝታ በለመመን ‹ልጅነቴ አልፏል? ...ቆዳዬ ተሸብሽቧል› የሚሉ ቃላቶችን ታነበንባለች። ይሀን ስትል ‹ሊ› በተደጋጋሚ ሰምታት እዚህ ዓለም ላይ እንደሌለ ሰው ሆና በዝምታ አልፋታለች።

‹ሊ እንቺስ ለምን አልተኛሽም?›

‹ዛሬ መንገድ ላይ ያጋጠመኝ አንድ ሰው ነበር›

‹ምን ዓይነት ሰው?›

‹ራሴን ገደልኩት እያለ የሚጮህ ሰው›[38]

[38] በሕይወት እያሉ ጎልውነትን መካድ ቢሥነ ልቡናው የጥናት ዘርፍ 'Cotard delusion' በመባል ይጠራል። በዚህ የአዕምሮ ሕመም የተጠቁ ግለሰቦች የጋዛ ራሳቸውን ጎልዮት፣ የእገድ ሰውነት ክፍላቸውን ወይም የገላቸውን ከራስ ጎልዮት በቁም ይከጻሉ። ይህም ጠባይ 'Cotard's syndrome' በመባል ይታወቃል።

‹እብድ መሆን አለበት›

‹ምናልባት ይሆናል›

‹ታዲያ እንዴት ራሱን ከገደለ በኋላ በሕይወት ሊኖር ይችላል?›

‹እኔም ይሄ ጥያቄ ነው ያልተመለሰልኝ›

○

ንግግራቸው ከዚህ አይገፋም። ጸጥታ ይነግሣል። የ‹ዲ› ገባር ሕልሞች ያለማቋረጥ ወደ አንድ ሰፊ የሕልም ባሕር ይጠልቃሉ።

[39]ጋሼ. . . ጋሼ ማንን እየጠበቁ ነው?
ጋሼ. . . ጋሼ ማንን እየፈለጉ ነው?
ማን ነው የቀረብዎት?

○

ልጄ. . . ልጄ የቆምኩትስ እኔኑ ጥበቃ ነው።
ልጄ. . . ልጄ የወጣሁትስ እኔኑ ፍለጋ ነው።
የቀረብኝስ ሌላም ሰው አይደለ — እኔው ራሴው ነኝ።

○

ጋሼ በስተርጅና ራስዎን ፍለጋ?
ዛሬም ራስዎን ጥበቃ?
እውንም ራስዎ ራስዎ ላይ ቁሩ?
ኧረ መቼ ይሆን ከ'ቱ የሚገናኙ?
ኧረ መቼ ይሆን እርስዎ ከእርስዎ የሚገጥሙ?
ኧረ መቼ ይሆን እንደ መንገደኛ 'ላኔ' ከሚሉት ጋር ድንገት
'ሚገናኙ?

[39] ማቡያ 10

○

ኧረ ልጄ ልጄ
ዕለቱን አላውቀውም።
ኧረ ልጄ ልጄ
ሰዓቱን አላውቀውም።
ብቻ እንዲያው በእንተው አፍላ ዕድሜ
ብቻ እንዲያው በእንተው ለጋ ወጣትነት — መጥፋቱን
አውቃለሁ።

ሳስታውስ ከንፈሩ፣ ትንፋሱ ይሻተት የነበረው ጂን ጂን ነው። ፊት ለፊት ካለ ሶፋ ላይ ሄዶ ያቀመጣል።

○

የእናቱን የልብ ትርታ እንደ ሰሞነ ሕማማት በገና አደምጣለሁ። ልቧ ውስጥ የዓለሙ አጋ በገና ነው ያለው? ነፍሷን እንዘረው። እኔን በማቀፍ፣ የተመሳቀለ ያረጀ ተስፋዬ ጎልጎታ ያለው ይመስለኛል። በእንቅልፍ ተዘርፌ እንባ እንባ ይለኛል። ድምፆ ባር ባር ካለ ሆዴ እየተገፋ ሳግ እገሰሱ ይወጣል። ከማሪያምነቿን በታች ያለንን ሕመም ማን ያውቃል? የእናቴን ሕመም ለማስቆም ከገባሁበት እንቅልፍ መንቃት ብፈልግም እውነተኛውን ዓለም ግን መጋፈጥ ፈርቼያለሁ። የሕልሙን ዓለም መርጬሠያለሁ። እናትና አባቴ የሚለያዩበት ዓለም ላይ መንቃት ምን ያደርግልኛል? አስፈሪ ትዝታ እደሆንም? ሕልሜም ማርና ወተት አይሰጠኝም። ያለኝን እፈት ነው መልሶ የሚማተኝ።

(ሞንሶ ፈ —

ዕ

ሳብ፣ እባብለሶ ሾፈ፣ ልናጉና ሾጸ፣ ባለዚት ነገ በለሶን ሰዓት ቅፃፈ እሾፈረስ ኦሎሶ በከባድ ፈለና ስጄት ሙነኮ ሊያበኩኩ ኦሎሶ በለንድ ሚኒሮ ሾኒ ለኮንን ቀረነውን ለልሶኢሳርንሾ

መለያየት[40]

እኮ ልብን እንዴት ይገሰፁልን?[41]

የሰምንት ዓመት ልጅ እያለሁ የእናቴ የ 'ሰ' ክንዶች ላይ አርፈ እንቅልፍ ይመስደኛል። ዕለተ ቀኑ ዓርብ ነበር አስታውሳለሁ። ጸጉሬን የሚያሻሹኝ ጣቶች እጅግ ለስላሳ ነበሩ።

○

እኔና እናቴ በእንቅልፍ እያናወዘን ከተቀመጥንበት ሶፋ በስተጀርባ የሚሰማ ሰዓት ተሰትሏል። ከሦስቱ አፉት ሰዓት ተኩል አልፏል። ኮቤሙ የከበደ ሰሙ ቢታችን ይጥባል። የእናቴን ሚንባር ለመሳም ይጠጋል። ትሸሸዋለች። ክንዱ ላይ በተኛሁበት አንገቱ ጉንፈኑን ይለመኛል። 'ያኔ' የሸተተኝ ጠረን ነበር። አድጉ

[40] እንዲሁ ፲፲
[41] ለራስ ዮሐንስ ፪ በዛብህ ... በዚህ ዕቅዱ ሁሉንም ተጨባጭ ነገሮች ...

የሚያመው 'ና' ነው። የምንለያይበት ቦታ ላይ እንደ ደረሰን እኔም እርሱም እናውቃለን። 'ቻው ቻው' ለመባባል ግን ተፈራርተናል። በእንድ አልጋ ላይ የምንተኛው በፅንጨት መነካት እንደ ሴሰበት ቱሰል ለንዳችን ከለንዳችን ተራርቀን ነው። ሴላ ሴት ጋር ደኺል። ጠልቶናል። እስከ አሁን በአቶ አላለውም። ድርጊቱ ግን ንላቡ ብቻ ሳይሆን ከንላቡ የሚወጣው ድምፄም እንዳረጀበት ከነገረኝ ቆይቷል። እንደ ድሮ ቀናቶቹ እንዴት እንዳለቁ አይጠይቀኝም። ከነጉድለቱ ላወራው ሰምክር አልቸልም። ቱና መልስ አይለጠኝም። ከባድ ቀን አሳልፎ ይሆናል ብዬ ዝምታን እመርጣለሁ። ግን ከሴላ ሰው ጋር እንደ ልጅ ሲሰቅ ሲጫወት አየዋለሁ። ቆይ ይህን ያህል ምን አድርጌዋለሁ? በመካከላችን ያለው ንደል በግልጽ እየሰፋ ነው። መጨረሻችን እንዳይከፋ በተቻለ መጠን እንድንነጋገር መንገድ አከፍትለታለሁ። የሚዘጋበት መንገድ አያማም። ስለነበረን ትሳንት ብዬ አለቅሳለሁ። የእንባ ብዛት ግን ያዘመመ ትዳራችንን ከመፍረስ አይመልሰውም።

○

በቸልተኝነቱ ደካማ እንደሆንኩ እንዲሰማኝ ያደርጋል። ንግግሬን የቋጨችበት መልክ ይለጠዋል። በለፉ የአርጊትን መልክ ያስይዘኛል። ያጣተለኛል። በእርሱ የተነሣ ጠንቅቄ የማውቀውን የገፃ ዕድሜዬን አሳምንም። ልብሴን በቀየርኩ ቁጥር ገላዬን መመልከት እፈራለሁ። ድንገት ተሸብሽቦ ባገኘውስ? ምናልባት አርጅቼ ቢሆንስ? መስታወቴ የሚያሳየኝን እውነት እጠራጠራለሁ። በትክክል የማየውን ነው? ወይስ 'ቢሆን' ብዬ

የምመኘውን የልጅነቴን መልክ ነው የምመለከተው? ፊት ለፊቴ ሊቀመጥ እስከዚ ንገረኝ እውነት ልጅነቴ ላልፎለል? ቆዳዬስ ተሸብሽቧል? ብዙ ለጠይቀው እዳዳለሁ። እርሱ እስከሚነሳኝ ድረስ ወጣት ነበርኩ። በላዩ ላይም ሴላ ቤት እስኪመርጥ ድረስ ቆንጆ ነበርኩ። በ'ዘ' ዓይን ሴላ ቤት የሚደረብባት ዓይነት ቤት ሆኛለሁ። እንዴት ነው እንደዚያ መሆን የሚቻለው? ሳላውቀው ንድያለሁ? ወይስ እንዲሁ በተፈጥሮ ለለንድ ወንድ በቂ ያልሆንች ሴት ለለች?

○

በልጃችን በ'ዲ' ፊት እንድናወራ አይፈልግም። ብቻችንን ቤት ውስጥ ስንቀር ወጥቶ ይሄዳል። መኝታ ክፍል ገብቶ ይተኛል። ወይ መጽሐፍ ያነባል። ትኩረቱን ቴሌቪዥን ላይ ያደርጋል። ውስጤ ይበግናል። ወደ ደጅ ከወጣ በቶሱ አይመለስም። ሲለውም በዚያው ማደር ጀምሯል። ቁጭ ብለን ምሽቱን እየጠበቅነው ይዘገይብናል። 'ዲ'ዬ የለባቷን ዓይናች ካላየች እንቅልፍ አይወስዳትም። በእርሷ ፊት እንድናወራ ሳይፈልግ ሲቀር ድርጊታችን የሕይወቷን መሥመር የሚቀይለው አይመስለውም። የመሸው እርሱን እየጠበቀችው ነው። ትሳንት ደጅ አደረ። ቀን ከሥራ እንደ ወጣ ወደ ቤት አልመጣም። ቢያንስ ድምውን እንዲያሰማት ብደውልለት አያነሣም። አሁንም ከንዱ ላይ የጣላት ፕይት አይደለም። አባቷን ፕበቃ ነው። ይህቺን ልጅን ብሎ ለቢቱ አሳደረም። እንደ ነጋም በጊዜ አልመጣም። ቢያስብበትስ በትልበድ ዳዴ ብሳ የቆመችበት ቤት እየፈረሰ መሆኑን ብታውቅ

መጀ ትተኛ ነበር? እኛ ባናወራም ሰምኛ ያወራሉ። ሰምኛ ባያወሩም መለመሱ ይገባኛል። አብረን የምናረጅ ይመስለኝ ነበር። አሁን ግን ወደ ወጣትነት ሲመለስ በግልጽ እያየሁት ነው። ሩዲሮን ወልደናል። ዳግም ወጣት ከሆንም በእሷ ገላ ሙሰጥ ብቻ የማደግ ፊድል እንደምናገኝ አጠብቅ ነበር። እርሱ ግን ጥሎኝ ሌላ መንገድ ፍለጋ ወጥቷል። ከእኔም ከልጁም ሌላ ሴት መርጧል። መጠየቅ እፈልጋለሁ። እኔና ልጁን ትቶላት የሄደላት ሴት የወጣትነት መንገድ ሰጠችው ወይ?'

○

በእንቅልፍና በተሰፋ ክንዴ ላይ የተዘለሰች ልጀን ጸጉር ከመዳበስ አርፋለሁ። ለእፍታ አውጠነጥናለሁ። እንባ ያረገዙ ዓይኖቹን እጠርጋለሁ። በሕመም ያሳለፍኳቸውን ሴሊቶችም አስታውሳለሁ። ሥቃዩን የምተነፍስበትን ቃል የባሌ ዓይኖች ላይ እፈልጋለሁ። አልጋ ላይ ተኝተን አስባለሁ። እንደ ተለመደው ጀርባውን ይሰጠኛል። ይረሳኛል። እያረፈብኝ ያለው የፍቅር ኮርፊያ ይሁን የጥላቻ በትር ለይቼ ለማወቅ እቸገራለሁ። መኝታችን ቅዱስ ነበር። እዚያ ፍራሽ ላይ በገዱሕ ናፍቆትና ፍቅር ያሳለፍናቸው ምሽቶች እገሰላዎቻችን ላይ አሻራዎቻቸውን ትተዋል። በጨለማ ውስጥ አቆላምጠናል። ሰሚ እንደዚያ የሚያምር አይመስለኝም ነበር። በዚያ ልክ እየተቆላመጥኩ አላደግኩም። ቃሉቹ ልቤ ውስጥ እንደሚውለበለብ የብርሃን ሰንደቅ ከፍ ከፍ ብለዋል። የምለው ጠፍቶኝ እጅቹን አጥብቄ ሰስም እንባዬ በጉንጩ ፈሰሰል። ይኼ ሁሉ ቃሉን በማመኔ ነው። ዛሬ ፍራሹ ይቆጠቁጠኛል። አንሰላው

የቆሸሸ ይመስለኛል። ትላንት እነ አጥቢዋለሁ። ምን ሆኜ ነው? ብርድ ልብሱን ንፋስ ሳስመታው እሙላለሁ። ልነ ያልሆንው ነገር ምንድን ነው?

○

በልብሶቹ ይዞት የሚመጣው የሴላ ሴት ጠረን በዚቱ ይላመላል። ነገ በአካል ይደት እንደማይመጣ በምን አውቃለሁ? 'ያ' ያለምመኛል። ልብሶቹን ሳጥብ እተነዛለሁ። ማን ፈት ነው ያወለቃቸው? ብቻዬን በሌለበት እናደዳለሁ። ቢፈቅድልኝ እንደ ሕፃን ላጥበው እዳዳለሁ። በገላው ላይ ማዘዝ አቁሚያለሁ። መልሺ ላንጻው እንዴት እችላለሁ? ባልሽ ለው ነው መልእክተ ቢሉኝ ሳለው ነው ብዬ እመልሳለሁ። ከእንትና ጋር ሲወድቅ አየነው ብለው ይነግሩኛል። በለው ወሬ አላምንም። መረጃም ግን አልንቅም። ተደብቄ ያንኑ መውደቁን ላይ ለው መሆኑን ይበልጥ እረዳለሁ። መውደቁን በማስረጃ አይቼ አልሸሸሁትም። እስከሚነሣ ጠብቄዋለሁ። መነሣት ያለመቻሉ ግን ትርጉሙ ምንድን ነው? እንደ ተመቸው? እንደ ሞቀው? እንደ ደላው? ለውም መልእክተም እንዳልሆነ ነው ትርጉሙ? ማለት አልገባኝም። የቱ ጋር ነው የተጣጣነው? መለያየት የጀመርነው? ለውቀው አልነበረም?

○

እርሱን ማጣት አልፈልግም። የእምነቴ መጀመሪያ ነው። እርሱን ካጣሁት በማን አምናለሁ? እያልኩ ሴሊት ላይ ከነጥፋቱ

እንዲያትረኝ እጠብቀዋለሁ። እጅቹ አይዘረጉምም። ታሉም መደ እኔ ለይመጣም። ሹክሹክታውንም አልሰማም። በመሰኩት ደኅ፡ ሥር እየተሸሉሰሉ የሚገቡ ራሳቸውን የበረዳቸው ነፋሰት በመሳከላችን 'ለገጅ ሆዬ[42]ን ያዘማሉ። ድምፃቸው ተዝረክረክ ግጥግቸውም መለያየት ነው። ቅኝቱን ሳደምጥ አድራለሁ። እንባ አምጣለሁ። የደስታ ሳይሆን የኀዘን— የመቻል ሳይሆን የመቁረጥ በእነዚያ ምሽቶች ጥልቅ እንቅልፍ ይጥለኛል። ስለማያትረኝ አያውቅም እገጂ በላብ አሰጥግለሁ። ያለምኒቸው ሕልምት ስለለንድ የሚርጥ ልጅ ናቸው። የመለድነው ወንድ ልጅ መለሱኝ ጹካውን ይገር እከተለየለሁ። ግን ከእናቱ የሚሸሽ ልጅ ምን ዓይነት ነው? ...ፊቱን በውልብታ ሳይ ባሌን ይመስለኛል። ትርጉሙ አይገባኝም። ደካማ የሆንኩት ለፍቅር ነው። ልቤን መገለጽ አልችልም። ገላውን ብንጠቅም ልቡ ግን የእኔ እንደሆነ አምናለሁ። የቆየሁትም ልቡ የእኔ ነው በሚል እምነት ነው። ምናልባት ምኝ ነኝ። እምነቴ ትከከል አይደለም። የለው ልጅ ብዙ ትከከል ባልሆኑ ነገሮች ያምናል። ልቡ የእኔ ነው ወይስ የሌላ? ዝምታውን እንዲሰብር እፈልጋለሁ። እገባዬ እንደ ሐምሌ ዝናብ ይወርዳል።

○

[42] "እገጂ ሆዬ ቅኝት ከሌሎች ቅኝቶች ለየት ያለ ፀባይ አለው ይላሉ መረጃ ሰጪዎቸ በጀመረበት የሚደጨርስ በጨረሰበት የማይጀምር "አወናባጅ" ቅኝት ነው ይሉታል። ሌሎች ቅኝቶች ግን በጀመሩት የሚጨርሱ፣ በጨረሱበት የሚጀምሩ ናቸው።" ሀለቱር መሃ ቀስታዩኒና አወቃ በወሎ አዝማሪዎች የነሮና የዘፈን ልምድ፣ ገጽ 127፣ መጋቢት 2007 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

ቿ

ነው' እባላለሁ። የ'ሰ' ባልና የ'ዲ' አባት ነኝ። ለትዳሬ መፍረስ ተጠያቂው እኔ ነኝ። ይህን የምለው እየኮራሁም እያፈርኩም አይደለም። በርግጥ አገናለሁ። ግለት ከድርጊቱ ይልቅ በዝምታዬ የቆለለችው ሥሰል ከፉኛ እንዳደማት ይገባኛል። ልቤ ቢቆርጥም በእሬ የደረስኩበትን ውሳኔ ለመናገር ጊዜ ወስጃለሁ። ሳልሞከር ቀርቼ አይደለም። 'እ...' እልና ግራ ተጋብቼ የጀመርኩትን 'እእ'ታ ለመጨረስ ከራሴ ጋር እታገላለሁ። የውድቀቴን ታሪክ ከምን መጀመር እንዳለብኝ አላውቅም። ነገር ግን 'ሰ'ን ተራርቀን በነበረ ጊዜ ይበልጥ እወዳት እንደ ነበር አስታውሳለሁ። ሳላውታት አረቅራት ነበር። አይገርም? በከንዴ ሳትገባ ትናፍቀኝ ነበር። ድምፆ ብርቄ ሳለ ልሰማት እጓጓ ነበር። እያወራሁት ያለሁት ስለመርታትና ስለመረታት አይደለም። አሁን ተቀራርበናል። ተጠጋግተናል። በአንድ ጣሪያ ሥር አድረናል። እጅግ በጣም ተሳምደናል። ለገላዋ አዲስ አይደለሁም። ውሎዋ እንዴት እንዳለፈ አውቃለሁ። ከማን ጋር ምሳ እንደ በላች፣ እነርሱ መሥሪያ ቢት ግን ወረኛ፣ ግን ጉረኛ፣ ግን ጅል፣ ግን ሰቆንጃና እንደሆነ አውቃለሁ። የማልጠይቃትም ለዚያ ነው። ግለት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተቀራረብን ቁጥር ስንራራቅ ይታየኛል። በፊት የነበረው የፍቅር እሳት አሁን በርዷል። እወዳታለሁ። ግን ዛሬም እርቧን ስለማፍቀሬ በልቤ እጠራጠራለሁ። ያረጀብኝ ገላዋ ሳይሆን እኔ ለእሷ ያለኝ ፍቅር ነው። መለልቸት በውስጤ እንደ ጉድ

ይናገልል። ከዚያ መሰልቸት ውስጥ እንደ አርን የሚወጣኝ ወሩራዎ ድብርት ብቻ ነው።

○

የተነሣንበትን የፍቅር እውነተኝነት ጥያቄ ውስጥ እከታለሁ። የምረዳው ከዚህ ትዳር ልጅ እንጂ አዲስ ነገር መፍጠር እንደማንችል ነው። በርግጥ እንምክራለን። ግን አይሠራም። የምንደርስበት ሃቅ 'ያ' ነው። እኔ ልብ ውስጥ ትዳራችንን የሚያስቀጥለው እሳት ጠፍቷል። እያስመሰልኩ መቀጠል አልፈልግም። በማስመሰልስ ምን ያህል መንገድ መጓዝ እችላለሁ? ምርጫ እንደ አማ ሰው ተቀብዬ በትዳሬ ብገፋ ሰሕተተኛ ነኝ። 'ሰ'ንም 'ዲ'ንም ተጨማሪ ሴላ በደል እንደ መበደል ይቆጠርብኛል። ይህን ማስብ የነበረብኝ ቀድሞ እንደ ነበር አውቃለሁ። ነገር ግን ሴላ እውነታ ላይ እስከምደርስ ድረስ የእኔና 'ሰ' ፍቅር የነበረና እውነተኛ ነበር። በቃኝ እጅ የያዝኩትን እውነታ የሚፈትን ሴላ ተጻራሪ እውነታ ግራ እጅ ላይ ሳገኝ ምን ላድርግ? የተረዳሁት ፍቅር የመሰለኝ ነገር እንደ አሞኘኝ ነው። አሁን ለ'ሰ' ሲሰማኝ የነበረው የፍጹም ፍቅር ስሜት አብሮኝ አይደለም። ልቤ ውስጥ ሲቀጣጠል አይሰማኝም። እና ወደ ተገናኘንበት መደዚያኝ የመጀመሪያ ዕለት ፊቴን በሐሳብ ጉ። እመልሳለሁ። ያን ሰዓት በዚያ ቦታ በ'ሰ' ፈንታ ሴላ ሴት ተገናኝቼ ቢሆን ኖሮ አልፋት ነበር? ባላገኘኋትና በአገኘኋት ሴት መካከል ያለው ልዩነትስ ምንድን ነው?

○

የተለየ ነገር አላደረግሁም። የትኛውም የትዳር ሕይወት ውስጥ ያለ ሰው ቢያጋስ እንዴ የገባበት ትዳር ውስጥ ስለመረጠው አጋር ትክክለኛነት ቀለበት አድርጎም ራሱን ይጠይቃል። መልሱ ከጠበቀው ወይም እንዲሆን ከሚመኘው ተቃራኒው ቢሆንም ለዚያ ሰው ለውጥ የለውም። ምክንያቱም ቀለበት ጣቱ ላይ አጥልቋል። ለንዴውት ተጋብቷል። ልጅም ወልዷል። አብዛኛው ትዳር ከእውነተኛ ፍቅር የተነሣ ሳይሆን ከጎብረተሰብ የሚመጣ የመዋረድ ሰሜት በመፍራት የቆመ ነው። እና ራሴን ስለ'ሰ' እና ስለእኔ ትዳር ስጠይት ያገኘሁት መልስ አለ። ከመልሱ መሸሽ አልችልም። ቸል ብለውም እሰከ ሞት ይከተለኛል።

○

እ... አሁን እወዳታለሁ እንጂ አላፈቅራትም። ይህን ለመናገር የደደብ ሰው ድፍረትና የአረመኔ ሰው ጭካኔን ይጠይቃል። መጠጣት የጀመርኩት ያን ድድብናና ጭካኔ በጥቂቱ ከአልኮል ውስጥ ባገኘው ብዬ ነው። አርፍጀ የምመጣው በዚያው እንደወጣሁ እንዳልቀር ስለምፈራ ነው። ፍርሃቴ ያስረፍደኛል። ጊዜ ብሰጠው በዚያው ያስቀረኛል። መጥቼ በር ላይ ስደርስ ወደ ቤቴ እንደ ምን መግባት እንዳለብኝ ግራ ይገባኛል። እንደ ባል! እንደ አባት! እንደ ከሃዲ ወይስ እንደ ለንድ እንግዳ ሰው ነው በሩን አልፈ የምገባው? ይሄን እያሰብኩ አመሻለሁ። ደጅም አድራለሁ። አሁን ግን እውነቱ ምንም ያህል ቢጎዳትም በግልጽ

ተናገረው ለጾድ እንደሚገባኝ አምናለሁ። ግን 'ሰ' በአውነቱ ፍቅር እንደምታረኝ አውቃለሁ። ለእኔ ያላትንስ ፍቅር ምን ለደርገዋለሁ? ከልቧ ለምታፈቅረኝ፣ ልጅንም ለሰጠችኝ ሴት እንዴት እንደዚህ ዓይነት ነገርን በቀላሉ ዘርግፈ መናገር እችላለሁ? በእርሷ ላይ፣ በልጂና በትዳሬ ላይ እንደ መቀለድ አይሆንም? እንደ ረፈደ አውቃለሁ። ግን የእኔንና የ'ሰ'ን መገናኘት ላስተካከለው የምችለው በመለያየት ነው። 'ሰው ምን ይለኛል?' በሚል ስሜት መታሠር አልፈልግም። ለእኔ ያላትን ፍቅርና 'ዲ'ዩን እንደ ካቴና መመልከት አልችልም።

○

እውነታውን የነገርኳት ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ልቧን የሰጠችውን ሰው ማንነት ጠንቅቃ እንደማታውቀው ዓይነት ባለ አሰተያየት ተመለከተችኝ።[43] እንዲህ አይታኝ አታውቅም። ይህም መረዳት በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ያፈቀረችው፣ ዕርቃኗን በፊቱ የቆመችለት፣ ልጅንም የወለደችለት ሰው 'እኔ' መሆኔን ማወቋ

[43] "How many of us known someone for years when suddenly, One day something happens, and we see him for the first time as a "real person." His personality has become alive and full of meaning in a way which has nothing to do with his appearance or his attitude. Our two minds has nothing to be looking directly at one another. We feel we have a real cotact with that person." The Philosophy of Aristotle, Monarch Notes. "ምነ ያሀሎቻችን ነን ለዓመታት ያወቅነውን አንድ ሰው በድንገት አንድ ቀን በተፈጠረ ከስተት ለመጀመሪያ ጊዜ "እውነተኛ ማንነቱን" ያየነው። የዚያ ሰው ማንነት. ከአቋሙና ከአመለካከቱ ጋር ባልተናኘ መንገድ ወደ ሕያውነትና ትርጉም እዘልነት ይመጣል። ሁለቱ አዕምሯችን እንዳቸው እንደኛቸውን በቀጥታ የሚመለከቱበት ምንም ነገር የለም። ከዚያ ሰው ጋር እውነተኛ ግንኙነት እንዳደረግን ይሰማናል።"

ወደ ድንጋጤ መራት። ወዲያው ደነገጥ። እያየሁዋት ጠመለኝች። ቀድሞ በምታውቀኝና አሁን በተገለጥኩላት ሰው ማንነት አዕምሮዋ የተምታታ መሰለች። ሄጂ ልደግፋት ፈለግሁ። ግን እንደምኗ ሆኜ ነው የምደግፋት? ግራ ገብቶኛል። አሰተያየቷ ላይ 'እውን አንተ ነህ?' ዓይነት ትዝብት ይነበባል። ሰለ እኔ ያላት አዲሱ ምስል የድሮውን ምስል፣ የድሮውም ምስል በአዲሱ እንደተጠፋፋባት ታስታውቃለች። ልትናገር ብላ ወደ ጣሪያው ቀና አለች። ሰግቦን ጋርዷታል። ከንዷ ላይ ወደ አሰተኛቻት ልጃችን አገላቷን ደፋች። 'ዲ'ዬ ሽፋሎጇ ተከድነዋል። የድካም እንቅልፍ ወስዷታል። አልፎ አልፎ ድምፃችን ከፍ ሲልባት ትነቃነቃለች። ለመመን ይዟታል። 'ሰ' የሚፋረዳት ዳኛ ፈልጋ እንዳጣች ተበዳይ ቀና ብላ አየቾኝ። በምላሹ አገላቷን ደፋሁ። የቀራት ጥያቄ 'በማን ነው የለወጥከኝ?' የሚል ነበር።

○

በሥራ አጋጣሚ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ የማውቃትን ልጅ አገኘኋት። 'ኤል' ትባላለች። በልጅነት አፈቅራት ነበር። ሻይ ቡና ተባባልን። በጨዋታ በጨዋታ ሰናወራ 'ያኔ' የጻፍኩላት ደብዳቤዎች ዛሬም በቤቷ እንዳሉ ነገረችኝ። አልረሳችኝም። በእሷም ትላንትና ዛሬ ውስጥ ዋጋ እንደተሰጠኝ በክብር አለሁ። የተጠፋፋነው ድንገት ነበር። አልፎ አልፎ ያሰፈ ሕይወቴን በትዝታ ሰበረብር ትላንቴ ውስጥ ያልተመለሰች ጥያቄ ሆና የማገኛት እሷን ነው። 'ያ' ያላለቀ ፍቅር ይከነክነኝ ነበር። እና ጊዜ አልፎ 'ኤል'ን በአካል ሳገኛት 'አሁኔን' ጥያቄ ውስጥ

ከተተከሉ ትላንቱ ውስጥ የነበረች አንዲት ትዝታ የተረጋጋ ሣሬዱን ትረትነኖለች ብዙ አልጠበቅኩም ነበር። የጀመርኩት ግን ያልጨረስኩት የልጅነት ፍቅር ይጠራናል። እንዴት ብዙ ድምፁን ችል ማለት ለቻላለሁ? እንዴትስ ብዙ ልቤን መገሰጽ እችላለሁ? 'ኤል' ምኖቴ ነበረች። ምኖቴን የመናር ዕድል ሲገጥመኝ እንዴት ረግጬ አልፋለሁ?)

○

ነግቶ ከእንቅልፌ ስነቃ እናትና አባቴ ተለያይተዋል። በየቅል መንገድ ሲሄዱ ተላልፌ የተሰጠሁት ለሴት አያቴ ነበር። የተመሳቀለ የእናቴ ከንድ ላይ እንቅልፍ ወስዶኝ ከተነሣሁበት ቀን እንሥቶ ቀኖቹ ልክ አይደሉም። ሕይወቴና ስሜቴ ተቀይሯል። የማያቋርጥ ቅዠት ውስጥ ያለሁ ይመስለኛል።

[44]እንድ ሰሞን ያፈቅርዎት የነበረ ሰው፣ ዛሬ ዛሬ ስምዎት ሲጠራበት ይዘገንነው ይሆናል። ለመውደድ ጊዜ እንዳገኘው ሁሉ ለመጥላትም ጊዜ ያገኛል። እርስዎም ከወደድዎ ወደ አልወደድዎ፣ ከጠላዎት ወደ አልጠላዎት — ይገለባበጣሉ። ጊዜ ኃያል ነው። የሰዎችን ስሜትና ማንነት ይለዋውጣል። በነበሩበት አይቀሩም። የማይገነዘቡት ለውጥ አካል ነዎት። ቢገደሩም ፈቀቅ ይላሉ። የሰውን እጅ ባያዩም የጊዜን ጠምዛዥ እጆች አንጋጠው ያያሉ። ስፍራ ያልለቅቆታል። ግራ ዘመሞች ቀኝ ይዘምማሉ፣ ቀኝ ዘመሞች ግራ ይዘምማሉ። ጊዜ መስታወት ነው። ሁሉን ያላይዎታል። መሐል ሰፋሪዎች የእግዜርም የሰይጣንም ናቸው።

[44] ማቡያ 11

የእሳት እራት[45]

እና

መብራት

፩

ፀሐይ ለስላሳ ብርሃኗን እንደ ሐበሻ ቀሚስ የነሰነሰችበት የሴት ወይዘሮ ቅዳሜ ጠዋት ነበር።

○

አያቴ ውስጥ ልብሷን ለብሳ ባለሶስት እግር ድንክ በርጩማ ላይ ተቀምጣለች። ጀርባዋ ላይ ወርቃማ ጥለት ያለው ስስ ነጠላ ጣል አድርጋለች። ከመቀመጫ ክበቡ ተነሥቶ የወረደ እርጅና ሠራሽ ስንጥቅ የኋለኛውን እግር እንዳልጠገገ ቍስል ገልጥጦታል።

[45] እንጀራ 12

ከበስተኋላዋ ቆሜ የጥጥ ፍልቃቂ የመሰለ ነጭ ሽበታም ጸጉሯን በቀስታ በሚዶ እልጋለሁ። ግድግዳውን የብረት ከራንጀ ተደግፎት ቆሟል።

‹እቫንጉሊትሽ አደረግሽኝ አይደል? ኧረ ቀስ ነጪሺኝ›

እስቃለሁ።

‹የዛሬን እያድርገውና ምን የመሰለ ዘንፋላ ሥጣ ጸጉር ነበረኝ መሰለሽ?›

‹እና የት ሄደ ዛሬ?›

‹ሂሂሂ እርጅናማ ያን ጸጉር ከእኔ ወሰዶ ለእንቺ አወረሰሽ። ድሮስ ከዚህ በላይ ምን እፈልጋለሁ? ምንስ ያደርግልኛል? ደግሞስ ሲናፍቀኝ ዓይኖቼ ሥር አይደለሽ? ሂሂሂ... ጠርቼ መዳበስ ነው። ወጣትነት ይተላለፋል እንጂ አያልፍም። የእኔን ብቻ አይደለም የእናትሽንም ውብ ልጅነት እንቺ ውስጥ እየዋለሁ። እርጅና ነው ጠራርጉ የማይወስደው የሌለው። ይሽው እግር እምቢ ካለን ቆይቷል። ዓይንም በሞራ ተጋርዷል። አሁንማ መቼ አጥሮት ያያል? ሂሂሂ... እንጠናበራለን እንጂ መቼ እናያለን? አናይም

እኮ እርጅና ብቻውን አይመጣ፡ ግሳንግሱ መዐት ነው። ሳነ፡
በደጉ ጊዜ ከሰው እስከ መልአክ አይተንበታል ይብታል።'

'መ..ል..አ...ክ?'

'አዎን፡ ሊያውም መልአክ ሞት ነዋ።'

'ምን ያመስላል?'

'ያየሁት ሰው ሊወስድ ግቢዬ መጥቶ ነው። ሴሊት ነው እንደ
ጉድ ያጠንብልሻል። እኔ ደግሞ ሂሂሂ... ጣሪያው እያፈሰሰብኝ
ግስታጠቢያ ደሞኜ ወለሉን እወለውላለሁ። ይንጠባጠባል።
አምፖሉም ደብዛዛ ነው። ከተቀየረ የቆየ። ሻማዬን አብርቼ
ተቀምጬያለሁ። በመሐል የውጪው በር ከፉኛ ሲጋጭ
እሰግለሁ። ነፍሱን ይማረውና 'ያ' ተከራዬ በሩን አሠሪው ሲለኝ
ነበር። እኔ ደግሞ ዘንግቼዋለሁ። ያው ከቤትም አልወጣ። ነገር
ልብ አልልም። ወድቄ የተሰበርኩበት ጊዜ ነው። የሚያስፈልገኝን
እናትሽ ናት የምታመላልስልኝ። እና የመስኮቱን መጋረጃ ገለጥ
እድርጌ ከፈትኩት። ወደ ውጪ ብመለከት እንድ ነገር የግቢዬ
መሐል ላይ ተገትሮ ቆሟል። ደንግጬ ተረሁ። የከፈትኩት

መስኮት በነፋስ እየተወዛወዘ ከልቢ ጋር ይመታል። የተገተረው
መልአክ ነበር። ጨለማ ከንፎቹ አየር ላይ ከፍ ብለው
ይርገበገባሉ። በአንድ እጁ ሰይፍ በሌላው ደግሞ ስልቻ ይዟል።'

'ምን የሚያደርግበት ነው?'

'ሂሂሂ... ምን አውቃለሁ ብለሽ ነው? ያው 'ሰይፉ' ሰይፍ ነው።
ይህቺኑን አንዲት ሕይወት ይነጥቅበታል። በ 'ስልቻው' ደግሞ
ሙት ነፍሳትን ያጭቅበታል። ተይኝ ተይዘው ይጮሃሉ። 'ያ'
ይሰማኛል። ጆሮዬ ላይ ጭውው ይልብኛል። ፈዝዤ የሚሆነውን
በድንግዝግዝታ እመለከታለሁ። በዚያ ላይ ስገባ ነፍሴም
ፈርቼያለሁ። ሂሂሂ... ነጎድጓዱም ይሽጐደጉዳል። እያየሁት
የተዘጋ ተከራዬን ቤት ከፍቶ ገባ። መቼም በጽልመተ መላእክት
ሥራ አልገባ ነገር... ዝም። ጠዋት ታንቆ ልክ ከእናቱ ማኅፀን
ወጥቶ እንደ ተወለደ ሰው ዕርቃኑን ተገኘ። ሰቅሶ ላይ እንዳንዱ
ተገድሎ ነው ይላል። ሴላው ተዘርፎ ነው ይላል። እኔ ግን በግቢዬ
ያየሁትን አውቃለሁ። ግን ለማን ምን ብዬ እናገራለሁ?
በስተእርጅና መሳቂያ ልሆን? ፖሊሶች 'ያየሽውና የሰማሽው ነገር
እሉ ወይ?' ብለው ቢጠይቁኝ... ዝም፣ ዝም።'

‹እዩ?›

‹ወዬ የእኔ እቶዩ ገላ›

‹እ...› ያሰብኩትን ከመጠየቅ ወደ ኋላ አልኩኝ።

‹በይ ንገሪኝ። ምንድን ነው እሱ?›

‹ሰዎች የሚለያዩት ለምንድን ነው?›

‹ሰዎች የሚለያዩት?› ያልጠበቀችው ጥያቄ ነበር።

‹እ?› አልኳትና ባታየኝም ራሴን በአዎንታ ነቀነቅኩኝ።

‹ፍቅር ሲያልቅ ነው›

‹ፍቅር ያልቃል?›

‹እም› ብላ የተመጠነ ምላሽ እንዴት እንደምትሰጠኝ እፍታ ወስዳ የሐሳብ ጉርሻ በሕሊናዋ ጠቀለለች። ‹እንደ ናና ከረሜላ እንከብል፣ በመዳፍ ላይም እንደ ፈሰሰ የሱካር ስፍር ተልሶና ተመጥጦ ሳይታሰብ ያልቃል።›

‹እ... እማዬና አባዬ የተለያዩት በእኔ ምክንያት ነው?›

‹ማን ነው እንደዚያ ያለሽ?›

‹ማንም›

‹በይ ደግመሽ እንደዚህ ስትዪ እንዳልሰማሽ። እነርሱ በራሳቸው ምክንያት ነው የተለያዩት። ፍቅር ሲነጥፍ ምን ይደረጋል? ቤት ካለ ፍቅር አይቆም?› ብላ በልጇ የትዳር ዕጣ እንደ መተከዝ አለች።

'እማሩን እባዱ ንድቷል?'

'እንዴት እንደዚህ ልትይ ቻልሽ'

'ሕልሜ ውስጥ ስታለቅስ አይቻታለሁ'

'እባትሽ ሳይሆን አፈቃቀሯ ነው የጎዳት። እየሽ እባትሽን በጣም ነበር የምትወደው።'

'ፍቅር ይጎዳል?'

'አፈቃቀሩን ካላወቁበት አዎ።' የእሳት እራት ታውቂያለሽ?''

'ማታ ማታ አምፖል የሚዞሩት?'

'እዎ። 'የእሳት እራት ፍቅር' የሚባል የፍቅር ዓይነት አለ። ልክ በስማቸው ሂሂሂ። የእሳት እራት የብርሃን ግለትን ትወዳለች። ሥጋ ተፈጥሮዋ ወደ ብርሃን እንድትሳብ ያስገድዳታል። እንደ ምልኪ በዙሪያው እያንገዋበበች ትሄድና ትሳተሙዋለች። በትኩስነቱ ይፈሽታል። አትተወውም። ልነፍጎችው ነች። ትጠጋዋለች። አሱም አይምራትም። ደጎና አድርጎ ይልጣታል። ሂሂሂ ያቺም ገላ ሆና ልትበርር ክንፍ አውጥታ ነው እንግዲህ። በስተመጨረሻ የምትሞተው ተንበልብላ ነው። ተቃጥላና እንደ አመድ በና። እየሽ የእኔ እቶዱ ገላ ...የእሳት እራት ሞቷ የሚጀምረው ለብርሃን ካላት ፍቅር ነው። አንድን ሰው በስብእናው ብርሃናዊነት በማም ልትወጂው እንደምትችይ ሲገባሽ ያኔ መፍራት አለብሽ። ህልውናሽ ራስሽን በማፍቀር ላይ ሳይሆን ሌላን ሰው በፍጹም ልብ ከመውደድ ከተነሣ አደገኛ ነው። እየሽ... ቢያጠፋም ብርሃን — ብርሃን ነው። አምርረሽ መጥላት አትችይም። ካለ እርሱ ሕይወትሽ ጨለማ እንደሆነ እንዲሰማሽ የማድረግ ትልት አትም አለው። ሂሂሂ... ብርሃንን መጥላት መቼ የዋዛ ሆኖ፣ እንደማፍቀሩ አይቀልም። ከባድ ሥራ ነው። ልብሽን ከመክፈትሽ በፊት ቅድሚያ ራስሽን ማፍቀር መማር አለብሽ። ያለበለዚያ ቢቁኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ ሆነሽ ቁጭ ነው። ሲበድሱሽ ለራስሽ አትቆሚም። 'እሺ' እንጂ 'አይ' አትዪም። ምርጫዎችሽና ሕልሞችሽ ይጨልማሉ። ብርሃንን ስለተጠጋሽ ብርሃንን አትሆኚም። በሌላ ሰው ማንነት አትደምቂም። የራስሽን ጌጥነት መፈለግ አለብሽ። ሂሂሂ... ደግሞ ውስጥሽ አለ።' ንግግሯን ገትታ ዙራ ተመለከተችኝ። በእሳት እራቷ ዕጣ ፈንታ እዝናለሁ። 'እየሽ

የእኔ እቶዬ ገላ... እኛም እንዲሁ ነን። እንዳንኤ በምንጠራቸው ነገሮች እንጠፋለን። ሰዎች በጨለማ ውስጥ ብቻ አይደለም። ቀኑን ብርሃንም ይሠወራሉ። በጠሉትና በተጠራጠሩት ሳይሆን በመወደዱትና በእመኑት ይጎዳሉ። ይከዳሉ። እናትሽ የእሳት እራት ፍትር ውስጥ ነበረች። አባትሽ ጥሩ ሰው ነው። ግንኮ የሚወደው ዓይነት ሰው ነው። ነገር ግን ያጠፋል። ይሳሳታል። ታግሳለች። ሞክራለች። ሳይሆንላት ሲቀር 'አይ' ብላለች። መለያየትን መርጣለች። እየሽ እኛ ሰዎች የእሳት እራቶች አይደለንም። ያለመታጠል ምርጫን መምረጥ እንችላለን። ሂሂሂ... አሁን ያልኳቸው ነገሮች ስሜት እንደማይሰጡሽ አውቃለሁ። ወጣትነት ቆላ አይደለም ያለው ቅርብ ነው ይመጣል። ትደርሽበታለሽ።'

○

አልተዋጠልኝም።

[46]ክራሳችን በላይ ሌላውን ስንወድድ ራሳችንን እንበድላለን። በሕይወታችን ውስጥ ላሉ ሌሎች ሰዎች ከትንሿ ልባችን ላይ ቆራርሰን የሰጠነው ስፍራ ብዙ ነው። ስለዚህም በእኛ ዓለም ውስጥ ለእኛ የሚሆን ቦታ አጥተናል። በልባችን የወደድነው ሌላውን ሰው ብቻ እንጂ የገዛ ራሳችንን አይደለም። የገዛ ራሳችንን እንዴት መውደድ እንዳለብን አናውቅም። አልተማርንምና።

○

ከሌሎች በላይ ራሳችንን አስበልጠን ስንወድድ ሌላውን እንበድላለን። ራሳችንን ስንወድ ለሌላ ሰው የሚሆን ቦታ በልባችን እንተውም። ስለዚህም በእኛ ዓለም ውስጥ ሌሎች ሰዎች ስፍራ ያጣሉ። በልባችን አብዝተን የወደድነው ራሳችንን ብቻ እንጂ በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ሞምር አይደለም። ሌሎችን ሰዎች እንዴት መውደድ እንዳለብን አናውቅም። አልተማርንምና።

[46] ማቢያ 12

የአገር ቤት መንገደኞች[47]

ወደ ምንም የሚወሰዱ

የጨለመ ዶርሜ ውስጥ እንደተጋደምኩኝ ስልኬን ከፍቼ ጋለሪዬን አገላብጣለሁ። በካሜራዬ ያነሣኋቸውን የወዳደቁ ቢሜ ቅጠሎችንና የሣር ዘለላ ፎቶግራፎች በጣቴ እያሳለፍኩ አያለሁ። ወድቀው የተገኙበትን ስፍራና ሰዓት ለማስታወስ እሞክራለሁ። በድንገት እንባዬም፣ ንቃቴም ይከስማል። እንቅልፍ ጥሎኝ ይሄዳል። በንጋታው የዓይኔ ቅላት እስኪበርድልኝ ድረስ ጥቁር፣ ቡኒ፣ ሰማያዊ... መነጽሮችን አድርጌ እንቀሳቀሳለሁ።

○

[47] እነጀራ 13

ቡና እወዳለሁ። የወጣልኝ የሴት አያቴ ብቸኛ አጣሁ ነበርኩ። ደም ሥሬ ቢቆረጥ አቦል፣ ቶና፣ በረካ ይፈስሰኛል። ደነሞኝ ሳናውዝ ስለቡና ውትያኖስ አልግለሁ። ቢጠግኝ በእጄ እየጨለፍኩ ፉት ስለምለው፣ ጸጉሬን ለትቂ ሂጂ ስሰምነክርበት፣ ልብሴን አወላልቱ ዕርቃኔን ሰለምዋኝበት፣ ገላዬን ሰለምለቃለቅበት፣ ሰለተንገረገገ የቡና ፍንጃል አስባለሁ። ሐሳቡ ብቻውን ያነቃኛል። የግቢ ልጆች የሚያውቁኝ እንደ ምንጭ በጠራው ሳቂ፣ ጸጉሬን በማስይዝበት የወይነ ጠጅ የሚግ ክሬ፣ ከላይ በማደርጋቸው ሰፋፊ ቢጫ የዳንቴል ሹራቦቼ፣ ቢራቢሮ በተፈተለባቸው የጂንስ ጃኬቶቼ፣ በሚኒስከርቴ፣ በቀያይ ባቶቼ፣ በከፋይ ቡትሰ ጫማዎቼ፣ በረዣዥም ቡኒ ካልሲዎቼ — ነው። ብዙ ጊዜ ከራሴ ወይ ከሙዚቃዬ ጋር ነኝ። ሙዚቃዬን ከፍቼ አልጋዬ ላይ ተጋድሜ፣ ደረጃ ላይ ተቀምጬ በቁዘማ ኮሌክሽን እደምጣለሁ። ጆሮዬ ውስጥ ስንትና ስንት የሙዚቃ ግጥሞች እየተጥመለመሉ እንደ ጉርሻ ወደቁ? በብሉስ፣ በካንትሪ፣ በፈንክ፣ በጃዝ፣ በፖፕ፣ በፎልክ፣ በሶውል፣ በአፕራ፣ በእኩሰቲክ፣ በኢንስትሩመንታል... ደረቅ ተሲያቶቼን ገፍቻለሁ። የቴፕ ክር የመሰለ ጸጉሬን ታጥቤ፣ ከተፍረከረኩት ዛላዎቼ ላይ ጤዛዎቼን ሳራግፍ የወረደኝን የጠል ናዳ ማን አየ? ...አረጋገፉቸው፣ ከመሬት ሲጋጩ የሚያወጡት ድምፅ እንዳልተሰማ፣ እንደ አዲስ የሙዚቃ ዘውግ ነው።

○

የመንገድ ዳር አግዳሚ ላይ ተቀምጬ ወደየቢታቸው፣ ወደየቀጠሮዎቻቸው ለመሄድ ታክሲ የሚጠብቁ ሰዎችን፣ መኪናዎቻቸውን የተወለጋገደ ሰልፍ አስይዘው ከላነሰኦቻቸውን የሚያስሙሁ ቹፌሮችን፣ ፍራፍሬ የሚሸጡ ባለጋሪዎችን፣ አልፎ ሂያጅ ሰዎችን... የድንች ጥብስ እየበላሁ እንደ ተንቀሳቃሽ ምስል እከታተላቸዋለሁ። ማንም ይታዘበኛል ሳይሉ ኑሮዋቸውን ይኖራሉ። ንፍጣቸውን ይናፈጣሉ። ምራታቸውን ይተፋሉ። ከንፈሮቻቸውን፣ ሪዞቻቸውን ይጠርጋሉ። ጆሮዎቻቸውን በጣታቸው ያጠነጥናሉ። ጸጉራቸውን ይዳብሳሉ። ያክካሉ። የሸሚዞቻቸውን፣ የሹራቦቻቸውን እጅጌ ይሰበስባሉ። የሱሪዎቻቸውን፣ የቦርሳዎቻቸውን ዚፖች፣ የስልኮቻቸውን ስክሪን ይነካካሉ። የእግርጌያቸውን አቧራ ያራግፋሉ። የተፈቱ፣ የላሉ የጫማ ከሮቻቸውን ያሥራሉ። አዛውንቶች የከዘራዎቻቸውን እጀታ ያዝ፣ ለቀቅ፣ ጠበቅ ያደርጋሉ። የዛሉ እጆቻቸውን ያንቋቋሉ። ዓይኖቻቸው ሰውነታቸውን ትተው ይሄዳሉ። ሩቅ፣ ሩቅ ያማትራሉ። ሥጋ እንደ ለበሱ ሮቦቶች እንቅስቃሴዎቻቸው ተመሳሳይ ናቸው። ታሪኮቻቸው እንዴት ተለያዩ፣ ሕይወታቸው...

○

በሽታ መቼ ያማል

ደዌስ መቼ ይገድላል?

የሚያመው መኖር ነው

የሚያመው ሕይወት ነው

○

የሚል ስንኝ አገሏል። በተገጣጠበ የኮረኮንቹ እግረኛ መንገድ ላይ ጠያይም ጠጠሮች እንደ ኮከብ ፈስሰዋል። ከሳምንት በፊት በዚህ መንገድ ሰማያዊ ዩኒፎርም ለብሰው፣ ዚፑ ተበላሽቶ በመርፌ ቁልፍ የተጠቀመ ቦርሳ አገለለው፣ ከቱፕርዋራቸው ላይ የጸጉር ቅባት እንደ ላብ እየተንጠባጠበ ወደ ትምህርት ቤት ያለፉ ልጆች ለቅልልቦሽ ጨዋታ አምስት አምስት[48] ለስላሳ ጠጠሮች መርጠው አንሥተው ወስደዋል። አርፍደው ሲደርሱ እንደ መሰንቆ ደጋን ከጀርባው በጎበጠ ክፉ ዘበኛ ተገርፈዋል። የተገረፉት ስለአረፈዱ ነው? ወይስ እንደ ዕድሜያቸው ልጅ ለመሆን ሲሞክሩ ነው? ያልጠና የእጅ መዳፎቻቸው ላይ ያረፈው ልምጭ ቀይ ሰምሰም ሰንበር ሠርቷል። ከመንገድ ፖል ባውዛዎች፣ ከመኪና መብራቶች እንደ ውኃ የሚፈስሰው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ብርሃን ጠጠሮቹን ያረሰርሳል።

○

ልጆቹ የለቀሙት ጠጠር ከሀያ ዓመት በኋላ የት እንደገባ ቢጠየቁ በትዝታ ምልሰት አይደርሱበትም። ዛሬ ለእኛ የቀረቡት ነገሮች ነገ ይርቃሉ። የገዘፉት ይኮሰምናሉ። ካረጁ የማይበጁት፣ ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ የሚሰብረው፣ ያረጀ አንበሳ የዝንብ መጫወቻ

[48] ሰባትም የለቀሙ አሉ

የሚሆነው፤ መነሪና ጉም እያደር የሚቀለው፤ ቀን የጎደለበት ጠገራ አይጥ የሚበላው፤ ወልደው ሳያበቁ በሰው ልጅ የማይስቁት፤ ተቀምጠው የሰቀሉት ቆሞ ለማውረድ የሚከብደው... በጊዜ ርትውነት ነው። በእጃችን የነበሩት ጠጠሮች ሳናውቀው ነባር ዋጋቸውን ያጣሉ[49]። እንዳልተገረፍንባቸው ተንሸራተው እንደ ዋዛ ይጠፋሉ። መዝግበን ስላልያዝናቸው በቀላሉ መልሰን አናገኛቸውም። በወደቁበት ይዘነጋሉ። ስለራሳችን ትላንት በረሳንበት ልክ የዛሬ እኛነታችንን አናውቀውም። በብላቴናነት ጠፍጣፋ መሬት ላይ የሰየምናቸው ጠጠሮቻችንና ጢባጢቤዎቻችን፤ 'ላይ፤ ባንከረባብት' የተባባልንባቸው ብዮቻችን፤ ከየሱቁ ደጅ አጎንብሰን ለቅመን 'ደስቶ ፈንገር' የተጫወትንባቸው የማስቲካ ልጣጮቻችን፤ የሽበ እሽኩሌታዎቻችን፤ የበረኪናና የሴራፋም ካርቱን መኪናዎቻችን፤ እልፍ ድርድር ቆርኪ ያጨድንባቸው አኪራም ድንጋዮቻችን፤ ዲሞና ቱዘር ያፈጋንባቸው የወተት ላስቲክ ኳሶቻችንን፤ ተረረም ያደረግናቸው የኮባ ሽጉጦቻችን፤ የወረቀት መርከቦቻችንና እሽክርክሮሾቻችን፤ የጨሌና የአካት ቀለበቶቻችን ዛሬ በአካል የት ነው ያሉት? ...ምር[50] ደፍነን እንደ ፈረስ ባጎነበሱ የጓደኞቻችን ምቹ ጀርባዎች ላይ ተቀምጠን አሻግረን ስናይ የመርሳት እገሩ እንዲህ ቅርብ ነበር? ዕቃቃዎቻችን የከበሩት ባዶ ትዝታዎቻችን

[49] "Time is that by which at every moment all things become as nothing in our hands, and thereby lose all their true value." (Arthur Schopenhauer, The emptiness of Existence) "በእያንዳንዱ የጊዜ ቅጽበት ሁሉም ነገሮች በእጆቻችን ላይ ወደ ምንምነት ይመጣሉ። በዚህም ያላቸውን እጣናዊ ዋጋ ያጣሉ።"

[50] ሚዳ ላይ የተሠመረ መሥመር

ውስጥ ብቻ ነው። በእውኑ ዓለም በቅጡ እንኳን አልተሰናበትናቸውም። በማላውቀው ነገዱ ውስጥ እንደ ተራ ዕቃቃ የመረሳት ዕጣ ፈንታ አሳድዶ እንዳያገኘኝ እፈራለሁ። እና ሊሞኔ 'ኤቭሪ ቲንግ መስት ቼንጅ' እያለች ታግደረድረኛለች።

ከተቀመጥኩበት የሚያስነሣኝ በሌሎች ሰዎች እይታ ውስጥ የመውደቅ ስሜት ነው። የሆነ ሰው እያየኝ ቢሆንስ? ራሴን ሌላ ጥያቄ እጠይቃለሁ። እዚህ ምን እያደረግኩ ነው? የማይመጣ መርከብ፤ የማይመጣን ነገ እየጠበቅኩ ነው? ቫይቭሬት ያደረገ ስልኬን ከኪሴ አውጥቼ እመለከታለሁ። አንድ ቲክስት ሚሴጅ ከ 'ሊ'[51] "የት ነሽ?"

[51] የዶርሚተሪዋ ልጅ

[52]የሕያውት እስትንፋስ ለሰው ልጅ የተሰጠ ታላቅ ቸንበር ነበር። ሲዘምንና በምክንያት ሲሸመን ያግረ፣ ያጌጠ፣ የተዋበ መሰለ። እነዚያን መንገደኞች ያያሉ? እስኪ ለአፍታ ይመልከቷቸው። ምን ዓይነት የሕያውት ቀለም አየልኝ? ሲንገዳገዱ ተመልከቱዋቸው። የመልካቸው አጠያየም፣ የሴቶቻቸው ግድያት-ያም ገጽ፣ የወንዶቻቸው ሙጀሌያም እግር፣ የልጆቻቸው ፎርፎርና ቅጫም፣ በመንገዳቸው እንደ ሞታ ምርግ የተከመረው አዳሪያቸው፣ የሕልሞቻቸውና የቅዠቶቻቸው ሚትቅት፣ የሣር ጎጆዎቻቸው ክሣድ የተደፋ ግራጫ ነው። ሕይወትን የሚነባቸው ፈጣሪ፣ ኑሮንስ ያከበደባቸው መንግሥት የቱ ነው?

○

ድርሳኖቻቸው ላይ ከከብቶቻቸው ጋር ሣር እንደተሻሙ ተጽፏል። በረኃብ ሲቆሉ ከብቶቻቸውን ላለማረድ ተግደርድረዋል። ከከብቶቻቸው እርድ በኋላ በቸነፈር ያለፉ የሙት ልጆቻቸውን ሥጋ እያለቱሱ፣ ጨነራቸው እየተፋፋ፣ ድቅ እያላቸው በሉ። የተረፈውን እነሉ አፈር ምሰው ከከርሰ ምድር ቀበሩ። የጣት ጥፍሮቻቸው ውስጥ የደረቀ ደምና አፈር አለ። ሰማይን እያዩ

[52] ማቢያ 13

ተፈጥሮን የሚቆጣጠረው ማን ነው? ብለው ጠየቁ። መልሰም አላገኙ። ከሰሱ፣ ረገሙ፣ እንባ ረጩ። ወጥመድ ገላቸውን ገላልጠው ያለ ርኅራኄ ደቡ፣ ሴቶቹ ሹርባቸውን፣ ወንዶቹ የራስ ጠጕራቸውንና ጽህማቸውን ሞልጪው ተላጩ፣ ግቅ ዝተት ለበሱ። ገመድን ታጠቁ። መንግሥትን የሚሾም ማን ነው? ብረት ምጣድ ላይ ዐረሩ የሚያምስ አብዮትስ ድግሱ ምንድር ነው? መሞት መቹ ከበደን? ለሞት ለሞትማ ሺህ መንገዶች አሉን። ለሕይወት ነው መንገድ ያጣነው ሲሉ ጮኹ። ሙሾ አዘነቡ። እንባ እያወረዱ፣ በባዶ እግሮቻቸው አረገዱ። ሃይማኖተኛ ሕዝቦች ናቸውና በአማልክቶች መኖር ያምናሉ። ሆኖም ግብረ ገብነት እይታይባቸውም። በልጓምነት አልገራቸውም። ድብቅ ፍላጎቶቻቸውና የሌሊት ሕልሞቻቸው ያስደነግጣሉ። በቪህም እብደታቸው የተነሣ አማልክቶቻቸው በመጀመሪያ እኛ ሰማይንና ምድርን አልፈጠርንም። ጠያይም ሰዎችን ከጠይም አፈር ከጠይም አስትንፋስም ያስገኘን —እኛ አይደለንም ሲሉ ይክዳሉ።

ለነብት መቼ ያልቀል?

Starry Night [53] [54]

'ግ' ን በነዋነብታማ የምሽት ስማዮች አስታውሰዋለሁ።

○

ትዝታው ከራዲዮ ላይ ሲተላለፍ በካሴት እንደ ቀጻሁት የድሮ ሙዚቃ ከነእሽሽታው ይመጣብኛል። በፊቱ እንደ ተሣለ ሥዕል ነበርኩ። አይቶኝ አይጠግብም። 'ዓይኖችሽ እንደ ከዋክብት ናቸው' ይለኛል። ቫን ጎኽ ስለሚባል አብድ ሠዓሊ ያወራኛል። ስለቢጫና ስለስግያዊ ቀለማት፣ ስለሱፍ አበባዎችና ስለጥድ ዛፎች፣ ጉም ስለለበሱ ቀናትና ስለሻራታም ከዋክብትማ ምሽቶች፣ በዘላለማዊነት በር ላይ ስለሚተክዘም ሽማግሌ። ቫን

[53] እገጀራ 14
[54] ሥዕል — በሺንሰንት ቫን ጎኽ

ጎሽ 'ሞት ወደ ከዋክብት የምንነጠትበት ሠረገላ[55]' እንደሆነ ያምን እንደ ነበር ይነግረኛል። ያቅፈኝና በሹክሹክታ 'ወደ ክኛክብት ተጠግቼያለሁ' ይለኛል። ምናልባት ከልቡ ነው። አጠገቢ ሆኖ የሌለባቸው፣ ደረቱን ዳስሼ የልብ ምቱን ያጣሁባቸው ቀናቶች አብሩ። ዓይኖቹን ሳይ ሩቅ የሄደ ይመስለኛል። ስጠራው በዝምታ ይመልስልኛል። ብሌኖቹ ውስጥ ጭጋግ እያለሁ። 'በርዶሃል የኔ ጌታ' አለዋለሁ። በታል አይመልስልኝም። በጸጥታ ያቅፈኛል። ጡቶቹን ይስማል። ከንፈሮቹ አንገቴ ዙሪያ 'ቨፍቲንግ ጊርስ' ጎ[56] ይርበተበታሉ። የጸጉሬን ቅንጣቶች በትንፋሹ እፍታ እየገፋ ፊቴ ላይ እንደ ቀጤማ ይነሰንሳቸዋል።

'Because of color lack

I shall paint your loving face

In colourless breath' [57]

○

[55] "Just as we take the train to go to Tarascon or Rouen, we take death to go to a star." Letter to brother, Theo van Gogh, 10 July 1888
[56] "Shifting Gears" — Sololmon Deressa (ያተኮጨበ)
[57] በቀለም ዕጦት
በቀለም አልባ እስትንፋስ
አፍቃሪ መልክሽን ልሥል እወዳለሁ

ከእሱ ጋር እንድ ነፍል ማለት ትርጉሙ ብዙ ነበር። ለእኔ 'ነ በመለኮት እንደገባ ግራጫ ደመና ነው። ሳትፈጠሩና ራሱን እየደባበስኩ ስለመው እንደ ተሰበረ ሰማያዊ ሰማይ ይሳጠሳል። መና በልቶ እንዳደገ ሰው ምንምነቱ ይጣፍጠኛል። ጉያዬ ውስጣ ገብቶ እካልነቱ አይገዝፍብኝም። ክርኔ ላይ ይንሳፈፋል። እንደ ማይጠገብ ጎብስት ስሙ አፈ ውስጥ ይልማል። ነፍሴ ከረብታ ላይ ትወጣለች። ስለቢጫ ቀለማት፣ ስለሱፍ አበባዎችም እያወረኝ ይበርደኛል። ነፍሴን ለለስ ያለ እስክስታ ያስመታታል። 'ነ ከመለከረም እስከ ጷግሜ አንዱን ወር ቢሆን — ሐምሌን ወይ ነሐሴን ነው። እሱን ላገኝ ከዶርም በወጣሁበት ቀን ያኔ ከረምት ይውላል። ይበርደኛል። እንዲያቅፈኝ አፈልጋለሁ። ድምፁ ውስጥ ያለውን ትዝታዬ እወደዋለሁ። 'እትት[58]' ን አዜምለታለሁ። በራድነትን አንጎራጉርለታለሁ። 'ገ' በማንም ልብ ውስጥ ያልተደረሰ ለብቻዬ የሰማሁት ዜማና ግጥሜ ነው።

○

ሰዎችን ሳይ አሻግሮ ያየኝ ነበረ። እኔ የሰዎች ጓላ ሳለሁ እሱ ጓላዬ ነበረ። ሰዎች የማያቸው ህያው ሥዕሎቼ ሳሉ፤ የሚያዩኝ ህያው ሥዕሉ ነበርኩ። እንደ አሞራ በዙሪያዬ ያንጎገብብ ነበር። የጥላውን እንጂ የአካሉን አመጣጥ አላየሁም። ከጓላዬ ሰው ነበር። ስታይ ነበር። ኮቴውን ሰምቼ ዞሬ አየሁት። የእግሮቹ አጣጣል እንደ 'ነ

[58] እትት —አስቴር አወቀ

ሆኖለስ ዋንደረር[59]' ጥታዎች ነበሩ። አድሜው አሰብኩት። ተጠግቼ ቀረብኩት። ልቤን ከናቹ አጠትኩት። ነፍሴን ዋዬ ወደድኩት። እንደ ቡና ካፈይን አምሮቱ ነበር። ልቤንም እንደሚለልብ መዚታ። ጠጣሁት። ሰማሁት። ልክፍተኛው ሆንኩኝ። ብቻዬን ቁሞ ብዬ የተመለደበትን ገጠር አስብ ነበር።

○

ያያቸውን ተራራዎችና ኗኗቴዎች። የቆጠራቸውን ሆኔታ ጭምር በምናቤ አደምጣለሁ። ብቻነቱን የተጋሩትን ግልገሎች በሕሊናዬ እስላለሁ። ወደ ውጪ የተመለከተባቸውን መስኮቶችና ጠራሪያ ተሊያቶች ልጋራው ድሮውን እናፍቃለሁ። ከእናቱ ጋር አህያ እየነዳ እህል ሊሸጡ የኳተኑዋቸውን ጠጠራማ መንገዶች በሐሳብ ፈለግ እከተለዋለሁ። በገበያዎች ውስጥ የተገኘራቱ ባተሌ ሳይናቹን አያለሁ። ከዚያ ገጠር ማምለጥ ይፈልግ ነበር። በረገጭዎም ዛፎች ሥር የተሰማውን ትንሽነት ላስረሳው እፈልጋለሁ። ግን አልችልም። እሞክራለሁ እንጂ ድሮው እንደ ባቡር እምልጦኝ ሄዷል። አልደርስበትም። ሳውቀው ዘግይቻለሁ። እንደሚከተለኝ ያወቅኩት አርፍጄ ነው። አሁን ከታመመበት ሕመም ላድነው አልችልም። እርሱ የተሠራው ከሕመም ነበር። ስወደው ከነአረፈበት ጠባሳ ጭምር ነበር። እኮ 'ነ' ያለጠባሳዎቹ ምን ነበር?

[59] The homeless wanderer —Emahoy Tesegue-Maryam Guebrou

○

አያቴን ሳስታውሳት እገረማለሁ። ለረዥም ጊዜ የእሳት እራት በሕልሜ አልም ነበር። አምፖሉ ውስጥ ሰንጥቃ ለመግባት ስትታገል አይቼ እነቃለሁ። እንዴት አልተቃጠለችም? አልረገፈችም? የ'ግ' ልብ ውስጥ መግባት እፈልግ ነበር። ሳቡ ግን በቦታው የለም። ዘወትር እንግዳ ስሜት ይሰማኛል። የማልነቃበት እንቅልፍ የወለደኝ ያህል እደነግጣለሁ። ከ'ግ' የያዘኝ ፍቅር ቢታጠቡት ከቆዳ ላይ እንደ ማይለት የመነቹከ ቀለም ነው። 'ያ' ቀለም በየስፍራው ይከተለኛል። በየጎዳናው እንደማፈቅረው ተጽፏል። በመኪና ጩኸቶች መካከል እሱን ማፍቀሬ ሳይደፈርስ በእርጋታ ተቀምጧል። አልጋዬ ሥር ስለእርሱ የታገሯቸው ቅኖቶች እንደአወለቅኳቸው ሚማዎች ተከማችተዋል። ልብሴን ለብሼ በ'ግ' ፊት ዕራቁትነት ይሰማኝ ነበር። በእርሱ ዘንድ ሰውነቴም ሕልሜም እንደ ተገለጠ ምንባብ ነው። 'ግ' ልጠነቀቀው የሚገባኝ የብርሃን ብርጭቆ ነበር። ነገር ግን ሳገኘው የሚጮህ ብርሃን አላየሁበትም። የተመለከትኩት ገዘም ያለ ጨለማ ነው። ግራ እጋባለሁ። እጠጋዋለሁ። የማያታዋል ጥሎር ብርሃን ነው። ሳሳገኘው በፊት ተነጥቄዋለሁ። የእኔ ሳይሆን በፊት ተወስዶብኛል። የነጠቀኝን አላውቅም። ግን እርግጠኛ ነበርኩ።

○

'ያኔ' ግቢ ሲረበሽ። እንደ ሌላው ጊዜ ነበር የቆጠረኩት፣ ተማሪዎች መንግሥት ላይ ያምጹ። ክፍል የሚጎባበትኝ

ማይገባበትን ቀን ይመስናሉ። የርጎብ አደግ ይመታሉ። ይፈራሉ። ከእንድም ሦስቱ 'ግ' በእነዚሁ ተማሪዎች በተከለከለ ቀን ክፍል ሲገባ ታይቷል። ለብቻው ካፈ የተመገበበትም ጊዜ አለ። እንድ ምሽት ወደ ላውንጅ ሲሄድ ጠብቀው የደበደቡት ልጆች ነበሩ። ማንነታቸውን ቢያውቅም አላልፎ ሰመስጠት ግድ አልነበረውም። በተደጋጋሚ ጥርስ የነከሱበት ልጆች እንዳሉ እሰማለሁ። አስቆጥቷቸዋል።

○

ከዶርሚተሪዬ ሆኜ የአድማ መበተኛ አስለታሽ ሞስ እያለሁ። ተማሪዎች እየተጫጫሁ ይተራመሳሉ። ፌደራል ፖሊሶች ግቢ ውስጥ በእግርና በፓትሮል ይንቀሳቀሳሉ። የጦር ሜዳ እንጂ ትምህርት ቤት አይመስልም። ስልኩ ላይ ደወልኩለት። እያነሣም። በተደጋጋሚ ይጠራል። አያነሣም። ልቤ ፈራ። ከዶርሜ ወጥቼ መውረድ ፈለግሁ። አጥወለወለኝ። የዶርም ልጆች እንደ እብድ ቆጥረው ያዙኝ። ተረጋግቶ ደጅ ስንወጣ፣ ከቆሰሉ ልጆች ውጪ ተገድሎ የሞተ አንድ ተማሪ እንደ ተገኘ ሰማን። ዓለም ሊከዳኝ፣ የቆምኩበት መሬት ሊንሸራተት ታወቀኝ። 'ግ' መሆኑን ሳታረጋግጪ ብላ 'ሊ' ልታረጋጋኝ ሞከረች። እርሱ ስለመሆኑ ልቤ እርግጠኛ ነበር። አንጀቴ ሲበጠስና ሲቆስል ሰምቻለሁ። የዶርሙ ልጆች ደውለውልኝ የተፈጠረውን ነገሩኝ። በጩቤ ተወግቶ፣ ዛፍ ሥር እንደ ተበጠሰ ቅጠል ተጥሎ መገኘቱን አረዱኝ። ፀሐይን በማንኪያ የዋጥኳት ያህል ውስጤ ተንበለበለ። ከንፎቼ ረገፉ። እንባዬ ከቁጥጥሬ ውጪ ይወድቃል። በረንዳ ላይ

የሚጠብቀትን እናቱን አስባለሁ። ይሆርብኛል። እንደ ብርሌ ስለበር ይሰማኛል። እንደ አረጀ ሕንፃ ስሰነጣጠቅ። እንደ ጣሪ ስረግፍ።

○

ዛሬም ድረስ ከዚያ የተረገመ ግቢ ወጥቼም የሎርድ ሐሮንን 'ዘ ናይት ዊ ሚት'ን ከፕሰይሊስቱ ላይ ሳደምጥ የምታጠልበትን ዩኑ እሳት ስሰበሰብ እንደናርኩ ይገባኛል። ስለ 'ገ' ስብሰሰሰል ከፉን ቡና እጠማለሁ። በማግስለው የቡና ማግ ውስጥ የነገን ነኝ ከዋክብታግ ሰማይ ይታየኛል። ሦስት ማንኪያ ስኳር አድርጊበት ይመረኛል። የስኳሮቹ እንክብሎች ከእርጥብ እንባዬ ደርቀዉ የተሠሩ ያህል የምወደው ቡናዬ ላይ ያንገሸግሹኛል። ውስጪ ረት ይናጣል። ስደበር ሙዚቃ ያምረኛል። ለወትሮ ከገባሁበት ግዜ ያወጣኝ ነበር። አሁን ግን ሙዚቃም ሌላ ሕመም ነው። የምሰማቸው ዘፈናች ሁሉ ስለእኔና ስለእርሱ የተዘጩ ይመስሉኛል። ግጥግቸው ደስ የማይል ትርጉም ይሰጠኛል። ጨለግ ይውጠኛል። እንቅልፍ አልጋዬ ላይ ይጥለኛል። ከድሜ ጋር ታጥፌ እተኛለሁ።

○

'ገ' ን ከማገኘቱ በፊት አልጋዬ ላይ በእንቅልፍ መውደቅ እደሰ ነበር። የምተኛው ከራሴ ጋር ታግዬ ነው። በድካም ስረታ ራሰን ከትራሴ በታች ቀብሬ ወደ ማላውቀው መቀመቅ እወርዳለሁ። እውነተኛውን ዓለም ተሰናብቼ በሕልሜ ዓለም ውስጥ ድንነት

እነታለሁ። ራሴን በእናቴና በአባቴ መካከል ቆሚ አገኘዋለሁ። የሁለቱንም እጆች አጥብቴ ይገርያለሁ። ጎይለ ቃላትን ይለዋወጣሉ። እንዲያዩኝ ብፈልግም አያዩኝም። እጃቸውን ይዤ ቡተጣጽኖ እጎትታለሁ። አጎንብሰው አያዩኝም። ድምፂን አይሰሙም። ሳይግባቡ ሲቀሩ ወደ ተለያየ መንገድ ጀርባ ተሰጣጥተው ይሄዳሉ። እጃቸው ስላለቀቅኩኝ እርምጃ በጪመሩ ቁጥር እንደ ታኘነ ማስቲካ ወደ ሁለት አቅጣጫ እለጠጣለሁ። ልበጠስ ስለምደርስ መለያየታቸው ያመኛል። 'ገ' ን ካገኘሁ በኋላ አስፈሪ ሕልሞቼ ጠፍተዋል። ሌሊቶቼም ሰላማዊ ነበሩ። ከሞቱ በኋላ ግን እነዚያ ሕልሞቼ ከምሽጋቸው ወጥተዋል። አሁን አሁን ሊመሽ እንቅልፍ እንዳይጥለኝ እፈራለሁ።

○

መስኩት ላይ፣ ስከፍትና ስዘጋ አስታውሰዋለሁ። መስኩት ለምን እንደሚወድ አሁን ድረስ አይገባኝም። ቤተሳፈርንባቸው ታክሲዎች ውስጥ በመስኩቱ በኩል ተቀምጦ ወደ ውጪ የሚያይበት መንገድ አንጀቴን ይበላዋል። ከመስኩቱ ወዲያ ለእኔ የማይታየኝ ሌላ አገር አለ? የመጣነው መንገድ ይሄን ያህል ረዥም ነበር? እያልኩ እገረማለሁ። ከኖርኩት ያልኖርኩት ሕይወት አይበልጥም? ከ'ገ' ጋር ያሳለፍኩት ጊዜ እንደ አንድ ልብ እንደሚሰልብ የሙዚቃ ርዝማኔ ነው። ምናልባት 05 ደቂቃ ከ44 ሴኮንድ ነው። ከዚያ የቀረኝን መንገድ ስለማላውቅ የመጣሁት መንገድ ይገዝፍብኛል። ናፍቆቱ እልወጣም ይለኛል። ብቸኝነት ዙሪያዬን ይከበኛል። የሚያዘናጋኝ ሰው እፈልጋለሁ። ሊያቅፈኝ

ጉያው የሚሞቀኝ፣ እና ደግሞ ዝም ማለት የሚችል። እቅፍ የሚተወኝ፣ ረዥሙ ብለሙ እንዳለ የሚያስረሳኝ። ማን ነበር ከድሙቱ ጋር ብንኖር ነኝ።

○

ድብርት ሊገድለኝ ይደርሳል። በቅዠማ አትም ሳጣ ከጎኑ ጋር የተገናኘንበትን ምሽት እረግማለሁ። በሞተ ሰው አነሰሳለሁ። እናደዳለሁ። በሃገም እሳት የማይሞት ትዝታዬ ያመረኛል። ልቢ ላይ ካፊያ ይጥላል። ብርድ ልብስ እደራርባለሁ። መሥራያ ቤት ደውዬ ሰበብ ሰጣቸ ለሳምንታት እተራለሁ። በጎመት እንደ መደ ሁለቱ ናፍቆት እንደ አሙስ ነፋስ ያመታኛል። በምን ዓይነት ሥነታዩ ውስጥ እንደማልኖ ማንም ሰው አያውቅም። እንደ መናኛ ከተማ ምስቅልቅሌ ይመጣል። እንደበቱ ይዘጋል። ስልኪን እጠፋለሁ። አፈ ዝም ቢለውም ሆዴ ይረግመዋል። በዘናጭ ያልተላመ ገላ የለኝም። ዓይኖቼን ከድኜ የምራገመው እያንዳንዱን መላም ነው። የቆዳዬ ገበር እንደ መጽሐፍ ገጽ ቢገለጥ የጠይም ከንፈሩ ዳና በስሱ ታትሚል።

○

ኑቱውን ሰምቼ የሠርክበትን ቅጽበት እጠላለሁ። ወድቃ የረገጣትን ቅጠል እረግማታለሁ። የተመላለስንባቸውን እውራ ጎዳናዎችና ጠባብ ጥምዝምዝ መንገዶች ዓይናችሁ ይፍለስ እላለሁ። እኮ የትኛው መንገድ ነው የመለደውን ሰው ሲመልስ ያያችሁት? እኔ መንገድ ሲወለድ እንኺ ሲመልስ አላየሁም። ለራሴ የማይገቡኝን

ነገሮች አደርጋለሁ። ለምሳሌ ‘ኀ’ የሚመሯቸውን ጓደሬን ከመሬት ተገምቼ በመቀስ እጉመዳለሁ። ምንም አያስማኝም። በሞትም እንዲኖያድ እጠብቃለሁ። ምስለ ያለው ሕሊናዬ ውስጥ ነው። ፎቶግራፍ አልተነሣንም። ስንላላ የምንተያጠ፣ የምናቃጥለው ማስታወሻ አልተወልኝም። ትዝታው ያረብሸኛል። ቅውስታ የሚሰረዝ ነገር ቢሆን ስለ’ኀ’ ያለኝን ትዝታ ሰብስቢ አሰርዝ ነበር። ቶና ብዬ ለማይን በሙሉ ዓይኖቼ ለማየት እፈራለሁ። ሕየው ላይ ልረሳው የምፈልገው ጠባሳ ተጋድሟል። በፈን ከናቼ ከተማ የምመጣው እንደ ወሐይ እያበራሁ ነው። የነዘኑን ጥልቀት ለሰዎች ብናገር ሙኖና ምነበር እንኺ መቼ ከነብብ ያመርዱልኛል?

ሥበሕሙምና በሥቃይ ውስጥ እናልፋለን። እኔም ያመጠኝ ጊዜ ለለገድ ወዳጄ ደውዬለት ነበር። ያን ምሽት ለረዥም ሰዓታት አወራን። ስለጠባሳዎቹ እንሥቹ ሥቃይ ምን ያህል እንደ ሰለቸኝ ነገርኩት። በድምፄ ውስጥ የመከራዬን ክብደት አሳየሁት። በትዕግሥት አድምጦኝ ከጨረሰ በኋላ ዛሬም ድረስ የማልረሳውን አንድ ጥያቄ ጠየቀኝ። 'ካለጠባሳዎችህ ምንድር ነህ?' ብሎ። ካለጠባሳዎቹ ምንም አልነበርኩም። ጠባሳዎቹ ቢጠፉ የምናገረው ታሪክ የሌለኝ ሰው ነኝ።

○

ሕይወት አልጋ በአልጋ አይደለችም። የተወለድነው በጣዕርና በሥቃይ ውስጥ ነው። እናቶቻችን ሲወልዱን 'ምጡን እርሺው ልጁን እንሺው' የተባሉ ናቸው። ተጽፈው ያነበብናቸው፤ የወደድናቸው መጻሕፍትና ገጸ ባሕርያን ሳይቀሩ በጽኑ መከራ ውስጥ ተፈትነው ያለፉ ናቸው። ምናልባት እያንዳንዳችን በየእርምጃዎቻችንና በየውሳኔዎቻችን ልክ እየተጻፉ ያሉ ጅምር መጽሐፍቶች ነን። እያዘጋጀን ላለነው ግለ ታሪክ ጸሐፊውም ኖና

[80] ማቢያ 14

ገጸ ባሕርይውም እኛ ነን። በምን መልኩ ታሪካችንን መዝጋት እንፈልጋለን?

ሁለት ዓለም[61]

የት ትኖሪያለሽ?

ኢንተርኔት ሊዘጋ የምትሆነው ይጠፋታል። የምትኖረው ምናባዊ ዓለም ውስጥ ነው። ስልኳን እንደ ሁለተኛ ልቧ ታየዋለች። ካለ ሶሻል ሚዲያ መኖር እንደማትችል ይሰማታል። 'አትወርኩ እንደ ተጻረጠ ቢቀርስ?' የሚለው ሐሳብ ብቻውን አጥንቷ ድረስ ያስደብራታል፤ ነርቭስ ያደርጋታል። ስትቀመጥ፤ ስትነሣ፤ ስትበላ፤ ስትጠጣ፤ ስትማር፤ ስትጋደም፤ ትራንስፖርት ስትጠቀም፤ ሽንት ቤት ስትገባ፤ ስታጠና... ስልኳ እጇ ላይ ነው — እንላይን ነች።

[61] እነጀራ 15

○

የአሮጌ ባሶችን ቀለምና መሳፈሪያ ትኬቶች፤ የውጻቂ ማስቲካ ልጣጮችና የአሻንጉሊት ሥዕሎች፤ የካፈ ቢሶችና ሰጉርሻ የተተዉ ሳንቲሞች፤ የሻማ ብርሃንን ደካማነት፤ ታጥበው ከተሰጡ የልብሶች አንደበት የሚወጣውን የውኃ ነጠብጣብ፤ የቴሌቪዥንን ምስል አልባ እሽታን፤ የረኀቦኛም ዛፎችን መለሉ ቁመትና የግንዳቸውን ያረጀ ቅርፊት፤ በመኪናዎች ላይ የረበበን የዝናም ጉምና ጠል፤ የምሥጢር ኪሶችን፤ ተወርዋሪ ኮከቦችን፤ የቻት ላይ ታይፒንግ... ምልክትን፤ የቴሌ ኦፕሬተሮች አመራር፤ ጠረጴዛ ላይ የብርጭቆ መቀመጫ የሚሠራውን ርጥብ ክበብ፤ የማታውታቸውን ሰዎች የድሮ ፎቶ፤ የመኪና መንገድ ላይ በዝናብ ወቅት ቀስተ ደመናነትን የሚያሸ ዘይታማ ውኃ. . . ይመስጢታል። ያዝናኑዋታል። የገዛ ራሷን ፎቶዎች፤ በመስታወትና በውኃ ላይ ያለን የመልኳን ነጸብራቅ፤ ዴኅቡ፤ ምላሽ ያላገኙላቸውን ጥያቄዎች ትጠላለች።

○

ከመኝታዋ ስትነሣ በሙሉ ልቧ አትነቃም፤ አትታጠብም፤ አትለብስም፤ አትራመድም፤ አትማርም፤ አትበላም፤ አትጠጣም፤ አትጸዳዳም፤ አትተኛም። በአጠገቧ ስለሚደረጉት ነገሮች ሐሳቡ የላትም። ግድም አይሰጣትም። በዚህ ቸልታዋ ኢንተርኔት እየተጠቀመች መንገድ ስትሻገር ከመኪና ልትጋጭ፤ ከፖል ልትላተም፤ ከደረጃ ልትወድቅ፤ ከጉድጓድ ልትገባ

የነበረችበት ጊዜ ብዙ ነው። ግለኝተኝነት ስለምታበሳ ጓደኞች የሏትም። ሰው ቀርቦ መግባባት ይከብዳታል። በአነስል ሊቀርባት በምከሩት ሰዎች የሚቀርብላት ጥያቄ ተመሳሳይ ነው። 'ለምን ለልክሽን ትተሽ ከእኛ ጋር አታወሪም?' ይሄ ጥያቄ ቢተሰበቸ ጋር ለእረፍት ስትሄድ ይጠነክራል።

○

'እስኪ ለልክሽን ትተሽ ከእኛ ጋር ተጫወቺ... ተይ እያልኩሽ እኔ ነው! ....እንቺ ሊ ምን ይዘጋሻል? ወይ ንቀት!' እናቷ ል።

'ኧረ ውጪና ከሰው ተቀላቀይ... የሆንሽው ነገር አለ? ለምንድን ነው የማታወሪው? ...የእኔ ሽጋ ተይ ዝም አትበይ። ትንሽ እንኳን አውሪ... ወጥተሽ የምታገኚው ሰው ካለ ንገሪኝ ብር እንድሰጥሽ' አባቷ ቸ።

○

ስልኳን ኪሷ ውስጥ ትከተዋለች። ሜሴጆች ይገባሉ፣ ኖትፊኬሽኖች ይደረደራሉ። እንግን እንደሆኑ ትገምታለች። አብሮ አደጎቿን፣ የኤለመንተሪና የሃይስኩል ትምህርት ቤት ጓደኞቿን ተደዋውላ አትገናኝም። ከካምፓስ ወደ ቤት የምትመጣውም በእናቷ ቀጭን ትዕዛዝ ነው። ያደገችበትን ግቢ፣ ዓለም ምን እንደሚመስል ያየችባቸውን ጎዳናዎች ትጠላለች። የተረበሳትን

ጥያቄ እንዴት ማስተናገድ እንዳለባት ግራ ይገባታል። መልስ ለመስጠት ትምክራለች።

○

ድምፅ አውጥታ ያወራች፣ መልስ የሰጠች ይመስላታል። ነገር ግን ሕሊናዋ ውስጥ የተፈጠሩ ድምፅ አልባ ዝብርቅርቅ ቃላት ብቻ እንደ ነበሩ የምትረዳው ፊት ለፊቷ ተቀምጠው ጥያቄውን ያቀረቡላት እናትና አባቷ ዓይኖቻቸውን በተግጽኖ ሲያንከራትቱ ስታይ ነው።

'እ...' ትልና ዝም ትላለች።

ሶበምንጠቀማቸው የታላት ልክ ብንደበርስ? ማለት ብዙ ታላት ስንጠቀም በብዙ ብንደበር? ጥቂት ታላት ስጠቀም ደግሞ በጥቂቱ ብንደበር? አያስፈራም? ሁለቱ ቦታ ቢታረኑስ? ምን ለውጥ ይኖረዋል? ጥቂት ስንናገር ብዙ ብንደበር፣ ብዙ ስንናገር ጥቂት ብንደበር? ከታላት ጋር ያለን የስሜት መዛመድ ያው መደበር አይደለምን?

○

ዝም ብንል ውጤቱ ይለወጣል? ዝምታ በሁለት ሆሂያት መካከል ያለ ክፍተት ወይም ኖኀት ቢሆንስ? ዝምታችን በምን ቀዳሚ ሆኗና በምን ተከታይ ሆኗ መካከል ያለ ክፍት ቦታ ሊሆን ይችላል? ልዋሟ ብንስጠው በሁለት አታካች ነገረኛ ሰዎች አማሃይ የቆምን ዝምተኞች መሆናችን አይደለም ወይ? ሁለቱ ጀሮዎቻችን በእጆቻችን ጠርንፈን ይዘንም የድምፃቸው ጥን ግዝፈት ታምቡራችንን ቢያላጋው? ያው ዝምታ ብንሆንም የተረበሸ፣ የደረረሰ ዝምታ መሆናችን አይደለም ወይ? ደግሞስ የዝምታ ከብደትና ቅለቱ ምን ያህል ነው? ከንግግራችን ይልቅ ዝምታችን እያመራምርም?

○

ዝምታ በጥልቅ የመደበር ምልክት ቢሆንስ? 'ዝም ያለ ሁሉ የሚናገረው ነገር የሉለው ነው' ግን አለ? 'ቢያውቅም' በለቶ አልፎ አልፎ ዝም የሚልበት ሊት አናውቅም? ለመድኃኒት አንሂን? ...ዝምታ ከንግግር በፊት ያለ ሐሳብ ማዋቀሪያ ፋታ ቢሆንስ? እንዲህ ዓይነቱ ዝምታ 'ዝምታ' ሊባል ይችላል? ሌላም ከፈፍ አለው። ለምሳሌ ዝም የምንለው የምንናገረው ነገር ስለሌለን ወይም መናገር ሳንፈልግ ቀርቶን ላይሆን ይችላል። መናገር እየፈለግን ነገር ግን ታል አውጥቶ የመናገር ድርጊት አሰልቺነት እና አቅም ጠያቂነት ቢሰማንስ?

እ...

...ብለን ጀምረን ቀሪውን ብንተወው? ዝምታ ብናደርገው? ...ከተናገርናት አንዲት 'እ' በላይ ያልተናገርናቸው 'እ...እ'ዎች ለአድማጭ አይከነክኑም? በልዋጩ የአንድን ሴት ቁመና ሸራ ላይ ስለን ስለን፣ ልክ የፈት ገጽታዋ ላይ ስንደርስ ቀለም ነክረን በብሩሻችን የመለረዝ ያህል ብናጣፋው? ተደራሲያኖቻችን ካዙት ግልጽ ቁመና በላይ የተሰረዘ፣ የጎደሰ መልኩን ያለማወቃቸው ነገር እይገጻቸውም? እያቁነጠንጣቸውም?

እ? »

ጥላቻና መውደድ[63]

ቅርብና ሩቅ

የማውቃቸውን ሰዎች እጠላለሁ። መልከ መልካም እናቴ ካልጠፋ ወንድ ፉንጋ አባቴን መርጣ አገባች። ስወለድ የአባቴን መልክ ይዤ ወጣሁ። ታናሽ ወንድሜ 'ዮዮ' አሥር ዓመቱ ነው። የእናቴን ዓይን፣ አፍንጫ፣ ከንፈር፣ ጥርስ፣ መልከ ቀይነትን ይዟል። አንደበቱ ይጣፍጣል። አዕምሮው ብሩህ ነው። ጥሩ ውጤት ያመጣል። አስተማሪዎቹ ይወዱታል። ከግቢ ውጪ ያየው ሰፈርተኛ ጠርቶ ይስመዋል። ከትምህርት ቤት ሲመለስ ቤቱንና ግቢውን ያምሳል። ደጅ ከጓደኞቹ ጋር ወጥቶ ይጫወታል።

○

[63] እገጀራ 16

አቶ እንደዚህ ዓይነት የልጅነት ጊዜ አልነበረኝም። ጉንጯን አልተሳምኩም። በዕቃቃ ጨዋታ ላይ ለሚስትነት አልታጨሁም። በሸመዶቹ ሰርግ ላይ እበባ በታኝ አልተደረግኩም። ኤሰመጉተሪና ሃይስኩል እየተማርኩ መልሱን የማውቀውን ጥያቄ እጇን አውጥቼ ለመመለስ እፈራ ነበር። ፕረዘንቴሽን ሲባል ከፍል አልገባም። 'ለመመኝ' ብዬ ቤት እቀራለሁ። እባቴ ምኔን እንዳመመኝ ይጠይቀኛል። 'ሐኪም ቤት እንሂድ?' ይለኛል። ጥያቄው ያናድደኛል። እልህ በደም ሥሬ ይመላለሳል። የፈተና ውጤቴን በመድፈን ላካክሰው እሞክራለሁ። ውርደት ይሰማኛል። የማጠናው ለበቀል ነው። ከፍል ውስጥ አልሳተፍም። የምቀመጠው መጨረሻና ጥግ ላይ ነበር።

○

የከፍል ሥራዎችን ከማንም ተማሪ ቀድሜ ሠርቼ እጨርሳለሁ። ይሰኬን ለቅቄ እስተማሪው ያለበት ፊት ድረስ ሄጄ ማሳረም ግን ይከብደኛል። እየዘረ የሚከታተል ከሆነ ሲመጣ ጠብቄ እሳያለሁ። የውጤት ቀን የፈተና ወረቀቶቼን ስቀበል መምህራኖቼ አያምኑኝም። የኮረጅኩ ይመስላቸዋል። ትምህርት ቤት በሌሊት ተነሥቼ እሄዳለሁ። ጥቅር ሰሌዳው ላይ በቢት ሥራነት የተሰጡ ጥያቄዎችን በወዳደቁ ቁርጥራጭ ጠመኔዎች ተደብቄ መሥራት ያስደስተኛል። እንደ መምህር እየተንጎራደድኩ የምቀመጥበትን ዴስክ ከተለያዩ አንግሎች ከርቀት እየዋለሁ። አንገቴን ደብተሬ ላይ ደፍቼ እዚያ ወንበር ላይ ነበርኩ። ማንም አላየኝም። እግዜርም ከላይ ሆኖ የማያየው ሰው ይኖር ይሆን እንዴ? አጠገቤ

የሚቀመጠው ትልልቅ ቢጋሮች ያሉት መነጽር የሚያደርግ ቁጭ ረዥም ልጅ ነው። አቶ ይቸታል። ጥርሶቹ ቢጫኒና የተወለጋገዱ ናቸው። የተያየነው ከእርሱ ጋር ነው። የጥያቄዎችን መልስ ከሚደብተር ይገለብጣል። የመነጽሩ መስታወት ላይ የራሲን ነጸብረቅ አዘውትሬ አይ ነበር። ለረዥም ጊዜ በመነጽር መስታወት ውስጥ ያለች ትኝሽዩ ሪፍሌክሽን ብቻ እንደሆንኩ ይሰማኝ ነበር።

○

እናቴን በመራጭነቷ አምርሬ እረግማታለሁ። በአባቴ ተመራጭነት እዝንበታለሁ። በወንድሜ ውበት እቀናበታለሁ። ለምን ቆንጆ ሆነ? ...የሚመርጠኝ አላገኘሁም። የተለየሁ ብሆን፣ ነገሮችን መቆጣጠር ብችል፣ ሰዎች ልብ ቢሉኝ እወድ ነበር። የሚያምር ገላ እንዲኖረኝ እየተመኘሁ ነው ያደግኩት። የለየልኝ አኩሪነት ወጣኝ። ኮፍያ ያለው ሹራብ ለባሽ ሆኜ ቀረሁ። ኢንተርኔት ከዚህ ዓለም ያመለጥኩበት መስኮት ነበር። የማያውቁኝ ሰዎች እዚህ ሰው የመሆንን ዕድል አይሰጡኝም። ሶሻል ሚዲያ ላይ ለመሆን የወሰንኩትን ነኝ። ስሜን፣ ጾታዬን፣ የተወለድኩበትን ቦታና ጊዜ፣ የተማርኩበትን ትምህርት ቤት... ቀይሬ አካውንት መክፈት እችላለሁ። ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር የተሰማኝን ሜሴንጀር ላይ በቲክስት አወራለሁ። ማንም አይዳኘኝም። በትላንቱ አይሰፍረኝም። ከሰዎች ጋር ለመግባባት በሥጋ መገለጥ አይጠበቅብኝም። ጊዜው ሰዎች በዓይን ካላዩት ሰው በፍቅር የሚወድቁበት ነው። ከማያውቁኝ ከማላውቀው ሰው ጋር ረዥም ርቀት አወራለሁ። በአካል ቢርቁም በመንፈስ ቅርብ የሆኑ ሰዎች

አሉ። ቴክኖሎጂ ድንበር አልባ ዓለም ፈጥሯል። እዚህ ሆኜ እዚያ ነኝ ‘ያ’ በሁሉ ቦታ የመገኘትን አምላካዊ ስሜት ያላብሰኛል። በቦቶት ወደ ሕይወቱ አዳዲስ ሰዎች ይገባሉ። ቅርብ ያሉት ይርቃሉ። ሩቅ ያሉት ይቀርባሉ። ስሌቱ ምንድር ነው?

○

ኢንተርኔት እየተጠቀምኩ ባይሆንም አላወራም። ሳሎን ሶፉ ላይ ተቃምጬ የቴሌቪዥን ቻናሎችን እቀያይራለሁ። የማየው አርት ፖለቲካይዝድ እንደሆነ ነው። ሾው፣ ሙዚቃው፣ ድራማው፣ ኢንተርቪው፣ ዶክመንተሪው... ፕሮፖጋንዳ ነው። ብሰላችም ወደ ደጅ አልወጣም። ‘እሽሽሽ’ የሚል ወይም ስርጭት ያልጀመረ ቀስቶ ደመናማ ቀለሞችን የሚያሳይ ጣቢያ ላይ አድርጌው እቀመጣለሁ። ሲደክመኝ ቴሌቪዥኑን እጥፍቼ የተዘጋ ክፍሌ ውስጥ በዝምታ አሳልፋለሁ። ነጭ ኖራ የተቀባ ኮርኒሴ ላይ ሳይናቼን እተክላለሁ። ተጋድሜ ሰመለከተው ለስላሳ ኖራ ነው። ርቃቱ ግምቴን እንድጠራጠረው ያደርገኛል። ተነሥቼ አልጋዬ ላይ ቆሜ እንጠራራለሁ። እጆቼ አይደርሱልኝም። ትራሴን አመቻችቼ እቆምበታለሁ። ጣቶቼ የኮርኒሱን ገላ ይረማመዱበታል። ኮርኒሱ ከሩቅ እንዳየሁት ለስላሳ አይደለም። ችፍርግርግ ደቃቃ ዐተር መላይ ፍንጥርጣሪዎቹ ይሸከካሉ።

[64]እንዳንዴ ለእኛ ከቀረቡት ሰዎች ይልቅ የራቁን ሰዎች አላምረው ያውቁናል። ከአንድ እናት ተወልደው በአንድ ጣሪያ ሥር ከአደጉ ወንድምና እኅት በላይ አራምባና ቆቦ ያሉ ሰዎች ይላላባሉ። ልብ ለልብ ይግባባሉ። እንጀራ ጠቅልለን የምናጎርሰውን ሰው ሆድ እናውቅም። እንዳችን የአንዳችንን ልብስ ለብሰን ስንሰነብት የምንተዋወቅ እንመስላለን። እንደ ወንድምና እኅት የወረስናቸው ዓይኖችና ጆሮዎች ተመሳሳይ ናቸው። እርስ በእርስ ግን እንተያይም። አንሰማማም። ዓይኖቻችን የሩቅ ሰው ያያሉ። ጆሮዎቻችን ባይተዋሩን ያደምጣሉ። በሥጋ እንጂ በመንፈስ አልተዛመድንም።

[64] ማቢያ 16

መሸኛ[65]

ደግሞም መመለሻ

ምሽት ነው በቤታችን ጣሪያ ላይ ተቀምጬ ስለ ትላንት አስባለሁ።

○

መቼ ዕለት ላፕቶፔን ስበረብር የ'ዲ'ንና የ'ግ'ን እንድ ፎቶግራፍ አገኘሁ። በትዝታ ወደ ኋላ ተመለስኩ። ተመርቀን ከዚያ ግቢ ከወጣን ሁለት ዓመት አልፎናል። ጊዜ እንዴት ይበርራል? ...ከ'ዲ' ጋር ተደዋውለንም ሆነ አጋጣሚዎች አገናኝተውን አያውቁም። ሕይወት በተለያየ መንገድ ወስዳ ለያይታናለች። ኢንተርኔት ላይ ሥራዬ ብዙ ፈለግኳት። አከቲቭ ከሆነች ዓመታት አልፈዋታል። ቴክስት ሜሊጅ እንዳልጽፍላት

[65] እንጀራ 17

ምን ብዬ እንደምልከላት ሳስብ ግራ ተጋባሁ። ነዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ 'ተጠፋፋን እኮ' ብላት አያስትምን? ይሄን ሳሚላት ትንሽ አልዘገየሽም? እስከ ዛሬ የት ነበርሽ ባነሽ ብትለኝስ? ...እንድን ሰበስብኩ።

○

ፎቶውን ያነሣችው ሳያውቁ ነበር። 'ዲ' ወጪ ወራጁን የምታይበት ፌርማታ ላይ ከ 'ግ' ጋር ተቀምጣለች። ያንን ወንበር ከማንም ሰው ጋር ተጋርታው አይቻት አላውቅም። በፎቶው ላይ ሐምራዊ ሚኒስከርት ለብሳለች። ጸጉሯ ተጎንጉኗል። ከላይ ቢጫ ቲሸርትና ሰማያዊ ጃኬት አድርጋለች። እርሱ ጥቁር ጂንስ ሱሪ በጥቁር ሹራብ ለብሷል። አንገቱን እንደ መድፉት ብሎ መሬቱን ያያል። እርሷ በስስት ሰርቃ ታየዋለች። ሁኔታዋ ተስፋ በቆረጠ ሰው ተስፋ ያደረገች አስመስሏታል። በጊዜው እንደ መገነደኛ ከሩቅ አቅርቤ አንሥቻቸው አለፍኩ።

○

ፎቶውን በወቅቱ በተለየ ፍቅር እወደው ነበር። ለረዥም ጊዜ ደጋግሜ አይቼዋለሁ። ያልገቡኝ ስሜቶች መልኮቻቸው ላይ ተጽፈውበታል። ሳየው ይከፋኛል። በጥልቅም እደበራለሁ። አነድ ላይ ተቀምጠው አንድ ላይ አይመስሉም። አጠገብ ለአጠገብ ሆው ተራርቀዋል። ተለያይተው አንድ ላይ ናቸው። ከእነርሱ ጀ የሚያገናኘኝ ነገር ባይኖርም የተከገዘኩትን መተከገ አስታውሳለሁ፡ 'ግ'ን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት የግቢ ልጆች ሊዘብቱበት ሰዎ

ላን ነው ብዬ ከተቀመጥኩበት ተና ስል ነው። ሲራመድ ፊቱይወትም ለምትም ግድ ያለው ሰው አይመስልም። ከትከሻው ቃገበር እንደ ተሸከመ ሰው ተደፍቶ ያዘግግል። ከጊዜያት በኋላ ከ'ዲ' ጋር የፍቅር ግንኙነት እንደ ጀመሩ ደረስኩበት። በሂደት አብሬያቸው ቡና መጠጣት ጀመርኩ። ያን ያህል ቀረቢታ በይኖረንም ጥቂት ታሳቶችን ተለዋውጠናል።

○

ተገድሎ የተገኘው ከአንድ የዋርካ ዛፍ ሥር ነው። ከሳምንታት በኋላ እርሱ የተገደለበት ስፍራ ላይ አንድ ባለቢቱ በውል ያልታወቀ ቡላ ፈረስ ቆሞ ተገኘ። እኔ ራሱ በዓይኖቼ አይቼዋለሁ። የፈረሱ ገጽ ላይ የሚነበበው ጥልቅ ጎዘንና ድብርት ነበር። የግቢው ጠኞች በበር ሲገባ አላዩትም። ከቀናት በኋላም በየት በኩል እንደ ወጣ ሳይታወቅ ተሠውሮ ቀረ። 'ግ' ን በጨረሻዎቹ የሕይወቱ ደቂቃዎች ላይ ያዩት ጓደኞቹና ሌሎች የግቢው ሰዎች ሲናገሩ ገጹ ላይ ልብን የሚነካ እንግዳ ፈገግታ ነበረው። የሞተ ሰው ይስቃል? ልቡ ላይ ጩቤ የተሰቀሰቀበት ሰው ተንጋሎ ደም እየፈሰሰው፤ ቅጠላት እየረገፉበት ሰማይ ሰማዩን እያየ ይፈግጋል? የሞት መልእክ ካሚራ ይዞ ይዞራል? ታዲያ ለምን ፊቱ በብርሃን ወገገ ይሄን እያሰብኩ ቀና ብዬ ሰማዩን ተመለከትኩ። ድንገት ኧራታም ብርሃን ያለው ተወርዋሪ ኮከብ እየተምዘገዘገ መጥቶ መጥቶ በቅርብ ርቀት ካለ የሰፈራችን ጫካ ውስጥ ከንፉን እንደ ተመታ ርግብ ወደቀ። በዚህ ርቀት ኮከብ ሊወድቅ አይቼ አላውቅም። ሄጄ ማየት ፈልጌ ከተቀመጥኩበት ብድግ አልኩኝ።

ግን ምሽቱን ፈርቼ መልሼ ተቀመጥኩኝ። ማሰጣ
ተንቀጠቀጠብኝ። ነገ በጠዋት ተነሥቼ የወይዘሪትን ቤታ ፈልጌ
ስለማየት እስባለሁ። ልቤ በሐሳብ ተከፍሏል። የዛሬው ምሽት ማታ
ይነጋል?

ድሕረ ቃል

በዮናስ ኣ. ጥሩነህ (ዶ/ር)

ድሕረ ቃል | ትዝታሽን ለኣኒ፣ ትዝታዩ ለኣነኚ

በዮናስ ኣ. ጥሩነህ (ዶ/ር)

እንደ መግቢያ፡

በጽሕፈት ደረጃ ኣገራችን ዘመናትን የተሻገረ ታሪክ ቢኖራትም በኣሁኑ ወቅት ሥነ ጽሑፋችን ኣዚህ ግባ የሚባልበት ደረጃ ላይ ኣይደለም። በኣህጉርም ሆነ በዓለም ኣቀፍ ደረጃ ስማቸው ጎልቶው የወጡ የኣገራችን ደራስያን ቁጥር ከኣንድ እጅ ጣቶች ያንሳሉ። እንደሌሎች ኣገራት ኣያንጸንጹ ዜጋ በቀን የሚያነበው ፊደል ብዛት ተጠንቶ ባናይም ኣውነታው ግን የተሠወረ ኣይደለም።

ሥነ ጽሑፍ ትልቁን ማኅበራዊ ኣዕምሮ (societal consciousness) በሙቅጽ ረገድ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። እንድ ማኅበረሰብ የደረሰበት የማሰብ (intellect) ደረጃ የሚገመገመውም በሥነ ጽሑፍ እድገቱ መጠን ነው ብዬ ኣምናለሁ። ሥነ ጽሑፍ ብዙ ዘርፎች ያሉት ሲሆን ልብወለድ ድርሰት ደግሞ ኣንዱና ዋነኛው ነው።

የልብወለድ ድርሰት መጻፍ ማለት ኣዲስ የሆነ ዓለም መፍጠር ማለት ነው።[66] ይህ ኣዲስ ዓይነት ዓለም በኣውን ኣንጻለውና ኣንደምንኖርበት ዓለም ሁሉ ታሪካቸው በሚተረክላቸው፣ ሕይወት ያላቸውና ሕይወት ኣልባ በሆኑ፣ በተለያየ ቅርጽና ኣቀራረብ በሚከሰቱ ገጸ ባሕርያትና ድርጊቶች የተሞላ ነው። ይህ የገጸ ባሕርያት ዓለም በመጽሐፍ ገጾች

[66] "Writing fiction – any fiction, no matter if it is realist, modernist, or postmodernist – is, by definition, an act of creating a world." ***The Cambridge University Introduction to Postmodern fiction***, *Bran Nicol, 2009*

የሚተረክ የተቀነበበ ነውና የተረክ ፍጥነቱና የድርጊት ሩጫው የተጣጣፈና ከእውኑ ዓለምም በበለጠ ድራማ የሚበዛበት ነው።[67]

በእሱባለው አበራ ንጉሤ የተጻፈው ይህ ትዝታ/ሽን ለእኔ፡ ትዝታዊ ለለንጅየተገለ የልብ ወለድ ድርሰት የደራሲው የመጀመሪያ ሥራ ሲሆን በርከት ያሉ አዳዲስ ነገሮች የተካተቱበት እና የተደከመበት ሥራ ነው።

የድርሰት ሥራው የድሕረ ዘመናዊ አጻጻፍን የተከተለ ሥነ ጽሑፍ ነው። ድሕረ ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ሲነሣ አብሮ ስማቸው የሚነሡት ፈረንሳዊው ፈላስፋ Jacques Derrida፣ አየርላንዳዊው ታዋቂ ጸሐፊ ተውኔት Samuel Beckett፣ አሜሪካዊው William S. Burroughs ወዘተ ናቸው። ይህ የሥነ ጽሑፍ ቤት ድንጋጌ ያለው፣ ትርጉም የመጣለት እስተምሀር ባይሆንም የራሱ የሆኑ ባሕርያት ያሉት ነው። በቪሆም ከተለመዱት የRealism፣ Romantism ወይም Modernism የሥነ ጽሑፍ ቤቶች የሚለዩት የራሱ ባሕርያት ያሉት ነው። ይህ ሥነ ጽሑፍ እንደ James Joyce እና Virginia Wolf የመሳሰሉ ታላላቅ የዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ደራሲያን ግለኛ በኋላ ከ1940ዎቹ ጀምሮ ብቅ ግለት የጀመረ ቢሆንም በአገራችን ሥነ ጽሑፍ እምብዛም የሚታይ አይደለም።

ድሕረ ዘመናዊ የድርሰት ሥራ ማንበብ እንደሌላ መጽሐፍ ቀላል አይደለም። በተቆጠቡና ጉልበት ባላቸው ዓረፍተ ነገሮች መልዕ መሠረታዊ ጥያቄዎችን እንድናቀርብና ራሳችንን እንድንጠይቅ የሚያስገድድ ስለሆነ በሽምጠጣ ተነቦ የሚቀመጥ ጥራዝ አይደለም። ይህም ሥነ ጽሑፉ እንዲወደድና ዕድሜ እንዲኖረው ያደርገዋል።[68]

[67] "Fictional worlds, then, are more complex than realist texts acknowledge. So is narrative." *Ibid, p xiv*

[68] "Postmodern fiction presents its readers with a challenge: instead of enjoying it passively, they have to work to understand it, to question their own responses, and to examine their views about what fiction is. Yet accepting this challenge is what makes postmodern writing so pleasurable to read and rewarding to study." *ibid p xii*

ሕልውና (existence) በዋናነት፡ በመሠረታዊነት የሚበለት ግብዓት ነው።[69]

ትዝታ/ሽን ለእኔ፣ ትዝታዩ ለለንጅ እንደዚህ ዓይነት ድርሰት ነው። የዘመኑን መንፈስ የሚያንጸባርቅ (zeitigist) እና በዚህ ወቅት ያለውን የለጠቃላዩ የሰው ልጅ ሁኔታ (The Human condition) የሚተርክ ሥራ ነው። ይህም በአገራችን ሥነ ጽሑፍ የራሱ ቦታ እንዲይዝ ያደርገዋል። በሥነ ጽሑፍ ዘርፎቻችንም ላይ መልካም ቀለም ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

እንደመግቢያ ይሄን ያህል ካልን ከዚህ በታች ደግሞ ጎልተው የወጡ ነጥቦችን እያነሣን እንዳስሳለን።

ሀ. ስም (Proper Name) :

"What's in the name?"

Asked the poet.

"Everything",

Said the Magician.[70]

[69] "To read postmodern fiction is to be invited to ask: what *is* fiction? What does reading it involve? Why do we read? Why, for that matter, do novelists write? Why do they create innovative, experimental forms rather than just stick to traditional ones?" *ibid, p xii*

[70] ***What Is it In a name? An inquiry into the semantics and***

ወለንድ ድርሰት ውስጥ የገጸ ባሕርያት አሰያየም ከነአተኮ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፣ ይሄ ጀግሪ ደራስያን ልብ የማይሉት ነገር ይመስለኛል። ስም እንድ ገጸባሕርይ የሚገለጽበት መጠሪያ ቃል ነው፣ ቃሉ ብቻውን ትርጉም ያለው እንኳን ባይሆን ያን ገጸባሕርይ ያለበጭ ግሰብ ግን አገችልም፣ ለምሳሌ Goethe እንዲህ ይላል:

"A man's name is not like a cloak that merely hangs around him, that may be loosened and tightened at will. It's a perfectly fitting garment. It grows over him like his skin. One cannot scrape and scratch at it without injuring the man himself."[1]

ለም እንድን ግለሰብ፡ ቁስ ወይም ቦታን ይገልጻል። ለምሳሌ ለንደን ብል ለለንድ ከተማ እያወራሁ እንደሆን ይታወቃል። በእውተት ለሌላ እኳል ወተቶ የሆነ እንደሆን ነው እንጂ ይሄ ስም ሲነግ በቲምስ ወንዝ ላይ ለለተገነባችዋ የሃገረ እንግሊዝ ከተማ ነው የምናስበው፣ ወአሥርአላችን ውስጥም ስለ ለንደን አንዳች ምስል ይከሰታል።

ወእገሪችን ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር አያይዞ ለሰዎች ስም ግውጣት የተለመደ ቢሆንም ሰያሚው ቀጥተኛ ትርጉሙን ሳይመከል ይችላል፣ ለምሳሌ 'ለማ' የተባለ ሰው በቀጥታ ከጎሠን ስሚት ጋር የተገናኘ ነው ግለት አይደለም።

የተለያዩ ፈላስፎች በስያሚ ምልክትነት ዙሪያ የተለያየ አቋም አላቸው፣ ለምሳሌ እንደ J. Stuart Mill ዓይነት ፈላስፎች ሰዎች ትርጉም የሌላቸው ምልክቶች እንደሆን ጽፈዋል። በአንፃሩ ደግሞ እንደ F. Gottlob Frege ዓይነት ፈላስፎች ስሞች በራሳቸው ትርጉም ያላቸው

---

pragmatics of proper names, Farhang Zabeeh, 1968

[1] Dichtung und wahrheit

ምልክቶች መሆናቸውን ያበከራሉ።[2] በዚህ እገባብ ትርጉም (meaning) ማለት እንድን ነገር ከሌላ ነገር የሚለይ ቃል፣ ስሚት ወይም አረዳድ እንደሆነ የተረዳ ነገር ነው። [3]

ይህንና ስሞች በተለያሚው ሥነ ልቡና ላይ ከፍተኛ ተጽዕና ማደራቸው እሌ የማይባል ሃቅ ነው። ስማችን ይቀርጸናል፣ ስማችንን ወደግከለ እናድጋለን ወይ ደግሞ ስማችን በተለምዶ የሚወከለውን ትርጉም እንላበሳለን። ይህ ሐሳብ ሁልጊዜ ነው ማለት እንኳን ቢከብድ ኛ እንደሚጻብር የክርክር ሐሳብ መውለድ ግን ይቻላል። ለምሳሌ ለንፉሃው የተባለን ጎረምሳ ብናስብ እቋቋሙን፣ ባሕርዩውን፣ አስተሳሰቡን ወዘተ በደብዛዛውም እንኳን ቢሆን መገመታችን አይተርምና በደሀ ስም የተሰየመ ገጸባሕርይ በስያሚው ምክንያት በውስጣችን በምንስለው ምስል ተጽዕና ሥር መውደቁ አይቀርም።

ይሥን ጽሑፍ ውስጥ በተለይም በልብወለድ ድርሰት ውስጥ ያሉ የገጸባሕርያት ስሞች ሙሉ በሙሉ ለእንባቢ እሊቢ (Imagination) የሚተው ስለሆኑ እንባቢ ከእሁን ቀደም በግላዊ ገጠመኝ በሚያውቃቸው የስያሚዎች እንድምታ ምክንያት የገጸባሕርያቱ ምስል በከፍተኛ ሁኔታ ተጽዕና ይደርስበታል። ምክንያቱም አስቀድመን የግናውቃውን ነገር በስም እንረጻም። ከዚህ አልፎ ተርፎም እንደበርትራንድ ረስል ያሉ

---

[2] Farhang Zabeeh

[3] "...Meaning in language is just a matter of difference. 'Cat' is 'cat' because it is not 'cap' or 'bat'. . . Meaning is the spin-off of a potentially endless play of signifiers, rather than a concept tied firmly to the tail of a particular signifier. . . Meaning, if you like, is scattered or dispersed along a whole chain of signifiers; it can't be easily nailed down, it never fully present in any one sign...", *Literary theory, An Introduction, Terry Eagleton, 2003 p110-111*

ፈላስፎች አስቀድመን የማንተዋወቀውን ነገርም አንሰይምም የሚል ሐሳብ ያንሣሉ።[74]

በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ውስጥ ደራሲው ሆን ብሎ ገጸ ባሕርያቱ በስሞቻቸው መነሻ ፊደላት (Initials) ብቻ እንዲጠሩ አድርጓል። [ገ፣ ሂ ገጽ 71 'ደ'፣ 'ኃ'፣ 'መ' ገጽ 58 መሠረት] በአንዱችን ሰውን በስሙ የመጀመሪያ ፊደል መጥራት የተለመደ ስላልሆነ ይሆናል በሌሎች የአማርኛ ልብ ወለድ ድርሰቶች ውስጥ ይሄ አይታይም።

በሌሊሳ ግርማ "እሰቲ ሙዚቃ" ውስጥ ከአነበብነው 'ኤሰ' ውጪ በሌላ ሥራ ይሄን ቴክኒክ ማየቱን አላስታውስም።

እንባቢው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ገጸባሕርያት በሙሉ ስም ስላልተገለጡ ስሞቻቸው እስቀድመው በአዕምሮ በሚከስታቸው ነባር ምስሎች ሳይጨቆኑ እውነተኛ መልካቸውን እንዲያይና እንዲረዳ ይረዳዋል። ይኼ ደራሲው ፈልጎ የፈጠረው ቴክኒክ ለእንባቢ አዕምሮ የፈጠራ ዕድልን ያጋራል። ጨርሶ የበሰለ ነገርን ከሚመገብ በምግብ ዝግጅቱ ላይ የራሱን አስተዋጽዖ እንዲያበረክትና የእጁን ጣዕም አብሮ እንዲተምስ ያደርገዋል ማለት ነው በሌላ አማርኛ። ይህም እንባቢ በተረኩ ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፍ ያደርጋል። በእንጻሩ ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ በሕዕናዊነት (Intertextuality) የተረቡ እውናዊ የሰው ሰሞች [ደሸኝ 'ሳ'፣ ፀዳ 'ቱ'፣ ፈታውራሪ 'ገ'፣ ጀንራል'ና' ገጽ 55, 56 እንዲሁም 'መ'፣ 'ኃ' 'ደ' ገጽ 58] በእውን የምናውቃቸው ሰዎች በመሆናቸው በስሞቻቸው መጀመሪያ ግጠየቅ አስፈላጊነቱ እምብዛም ነው።

[74] "A name in a narrow logical sense of a word whose meaning is of a particular, can only be applied to a particular [being] with which the speaker is acquainted. because you cannot name anything you are not acquainted with.". *The philosophy of Logical Atomism, B. Russell*

ለ. የሕዋ - ጊዜ ኮንቲነም /The Space - Time Continuum:

አንድ ልብወለድ ድርሰት ተረኩ የሚያርፍበት ጊዜ እና ጊዜው የሚፈስበት ቦታ (space) ያስፈልገዋል። የሕዋ - ጊዜ ኮንቲነም (The space - time continuum) በፊዚክስ ዘርፍ የአንድን ቁስ በሕዋ ውስጥ ያለ መገኛ ለመግለጽ የሚያገለግል ጊዜ፣ ቦታና ቁስ አካል የሚሰናሰሱበት ባለአራት ስፍረት (diamension) ፅንሰ ሐሳብ ነው።

የልብወለዱንም ዓለም በዚህ ስፍረት ሰፍረን ለመረዳት እንሞክራለን። ጊዜ ብቻውን ትርጉም የማይሰጥ ቃል ነው። ጊዜ ያለሚያርፍበት ቦታ (space) ለብቻው አሐድ መሆን አይችልም። እንደዚሁም ቦታ ያለጊዜ ለኬት ትርጉም አይሰጥም። በተሳሉ ለመረዳት፣ ወርድ ወይም ስፋት ወይም ቁመት ብቻ ያለው ያለውን ሳጥን ማሰብ እንችልም። እንድ ሳጥን ሳጥን እንዲሆን ወርድም፣ ቁመትም፣ ስፋትም ያስፈልጉታል። እያንዳንዳቸው በራሳቸው ትርጉም ያሳቸው ቃላት ቢሆኑም እንዳቸው በሌላቸው ካልተሰናሰሉ ትርጉም ያለው ነገር አናገኝም። ጊዜና ቦታም ያላቸው ግንኙነት ከሞላ ጎደል ይሄው ነው።

በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ በአብዛኛው የተለመደው ጊዜ ቀጥተኛ ጊዜ (linear time) ነው። ይህም ማለት ከ— እስከ ተብሎ ከአንድ መነሻ ሰዓት እስከሌላ መድረሻ ሰዓት ድረስ፣ ተከታታይ ሁነቶችን በቀጥታ ያለመተጣጠፍ የሚተረክ ጊዜ ነው። በድሕረ ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ጊዜ ይኼንን የጊዜን ቀጥተኛነት ወደጎን የመተውና የተረክ ኩነቶችን እንዳሻን፣ እንደተመቸን ወደትፍንጭ ቅንጣቶች በመበታተን በዘፈቀደና በተረባበሸ (chaotic) በሆነ መንገድ መተረክ ይታያል።[75]

[75] "The terms of significance have obviously changed in postmodern fiction: linearity, linear causality, and qualitative difference lose much of their impact (as far as that is possible

ቃኤሶደን ብለነ፣ ቃጀቶዶ ለለንድ በአሥራ ስድስት ሰዎች እንደራሶችና በአሥራ አምስት ማህያሎች የተረበ የሚሳክተ ሴማ ነው። በመነሀ ላይ የተነባበረው እያንዳንዱ እንጂራ የራሱን ሚሎ የተለያየ ግደነት ማህያ ቀርቢሏል። ማህያሎቹ በየእንጂራዎቹ ላይ ያለ እንጂ መረቱ ከላይ እስከታች እየሰረገ ሁሉም እንጂራዎች ላይ ያተመ ተጭኮተዋል። ስንበላ ይማፍጣል። ጣቶቻችን ላይ፣ ቅርጥሙን ካለሙ ያረቱ የመረት ወለላዎች በምላስ ይላላሉ። ከዛ ለይንከ ብለን እንመርቅ እሚን።

መጽሐፉን ስናነብ ባለአዲስ ቅርጽነቱ ባያጠያይቀንም አስቀድመን ካነበብናቸው ሥራዎች ጋር እያስተያየን ማቀራረባችን አይቀርም፡ አጠቃላይ ቅርጹና የምዕራፍ አስተነባበሩ በግርድፉ የአሚሪካዊ ጸሚኒካዊውን ደራሲ ዩኖት ዲያዝን (Junot Diaz) ሥሪ ያስታውሰኛል።[78]

አሁላው አበራ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀመባቸውንና ነልተቃ የወጡ ቴክኒኮችን ለመዳሰስ እንሞክር።

1. Metafiction:

ሚታፈክሽን ማለት ደራሲው በድርሰቱ ውስጥ ስላለ ልላ ድርሰት የሚናገርበት/ የሚገልጽበት አጻጻፍ ነው።[79]ይህ

[78] *This Is How You Lose Her, Junot Diaz, 2012*

[79] "Metafiction is the main technical device used in postmodern fiction. It may be defined as 'fiction about fiction' – fiction, that is, which is about itself or about fiction rather than anything else." *The Cambridge Introduction to Postmodern fiction*

የአጻጻፍ ቴክኒክ በደ/ሕረ ዘመናዊው ሥነ ጽሑፍ የተለመደ ቴክኒክ ነው። ደራሲው የተረኑ (Narration) የሚተረክበት መቃን (frame) ትኩረት እንዲያገኝለት ሲፈልግ በቴክስት መሐል እየተከሰተ ስለልብመለዱ ሌላ ልብመለድ በልብመለዱ ውስጥ ይጽፋል።[79]

ለምሳሌ፣ *". . . ከጠብታም ጋር ስንወርድ የምናገኘው የሁቶኒያ መሰነ ላይ በጀርባው የተንጋለለውን– ሳ'ን ነው . . ."* [ገጽ 7] ካለን በኋላ ይዛን ተረክ እንደመደገሬያ አስመርኩዞን ወደ ግርጌ ማስታዎሻ ይወን ይገባል። በግርጌ ማስታዎሻ ላይ የተጠቀሰው ተረክ የተለየ ተረክ ነው። በዋናነት የዚህ ተረክ አንባብ በዋናው ተረክ ላይ የክበረንን ለዘብተኛ አረዳድና ስለላ እንድናጠናክር ነው።

ይህ ዓይነት ቴክኒክ በእውን ያሉ ዋቢ ተረኮችን በማስገባት ወይም ደግሞ ከላይ እንዳየነው ተጨማሪ ልቦለዳዊ ተረኮችን በማስገባት ሊደረግ ይችላል። አልፎ ተርፎም አንባቢንም

Bran Nicol, 2009, p35

[79] "The metafictional staging of a clash between real and represented worlds encourages us to pursue the implications to their logical conclusion: fiction is fictional, but no more so than reality.When it collapses the distinction between fiction and reality by causing the 'outside world' to seep into the world of the novel, metafiction is more subtly demonstrating that the obverse also happens, the fictional world intrudes into the real world. This might seem far-fetched until we consider the effect of having real historical personages feature in awork of fiction as they frequently do in postmodern writing." *Ibid, p39*

ቺሞር በግወናበድ በእውን የሌሉ ደራሲያንንና ግጣትን መጽሐፍትን መጥቀስም ሊሆን ይችላል። በዚህ ረገድ ከውዉ Jorge Luis Borgesን፣ ከአንራችን ውስጥ ደግሞ አጻም ረታን መጥቀስ እንችላለን። አሰባለው አበራ ደግሞ ሌላው። (ገጾች 25፣ 31፣ 81፣ 94፣ 150 ተመልከት።)

2. Intertextuality:

በይነ ጺሊፐሊናዊ የሆኑ ቴክስቶችን በግስገባት የተረኩን አውድ ግስፋት ሌላው ቴክኒክ ሲሆን ደራሲው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በዋናው የተረክ አካል ውስጥ [ለምሳሌ፡ ገጽ 58] እንዲሁም በግርጌ በኩል [ገጽ 55፣56፣92] የተተረኩ ተረኮችን ማንሣት እንችላለን።

Intertextuality ከዚህም በላይ ቀድሞ የነበረን ሥነ ጽሑፍ ወይም ቴክስት አውድ በመጠቀም ሌላ ቴክስት ሰንን ማቅረብ ይቻላል። ለዚህም በዋቢነት በግረኩ ፕሮሚቲየስ አፈታሪክ ላይ ተመርኩዞ የተጻፈውን የMary Shellyን 'Frankenstein' እንዲሁም በHomer epic ግጥም 'Odyssey' ላይ ተንተርሶ የተጻፈውን የJames Joyceን 'Ulysses' መጥቀስ ይቻላል።

3. Literary minimalism:

ሊተራሪ ሚኒማሊዝም ግለት በጥቂት የተመጠኑ ቃላት ብቻ በመጠቀም መግለጽ የተፈለገውን ነገር መግለጽ የሆነ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለ የቃላት ኢኮኖሚ ነው። ለዚህ ዓይነት ሥነ ጽሑፍ የHemingwayን 'The sun also rises'፣ የAlbert Camus "The Stranger' እንዲሁም የSamuel Beckett ትሪለሎጂ የሆኑት 'Molly', 'Malone dies' እና The Unnamable ሳይጠቀሱ አይታለፉም። ይህ ቴክኒክ

ልቦለዱን ግጥግዊ ይዘት እንዲኖረው ያደርጉታል።[ገ]
ምሳሌዎች መስደን እንይ፡

"... ሕፃናት የለዋቂ ሕልምን ያልግሉ። ሽግግሌዎች እንደ ልጅ ቃሎተው ከአልጋ በብርክ ይነግሉ..." ገጽ 6
"... አባቴ በርቶግራፍ ላይ እንዳለ ከፍት ቦታ ነው አለም፣ የለምም።" ገጽ 19

በሌላ 'ግ' 'ዲ'ን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያነኝበት አጋጣሚ የተጻፈበትን [እንጀራ 9] ብንመለከት

"'እየተከተልከኝ ነበር?'

ብላ ጠየቀችኝ። ድምፆ ያምራል፣ ያስፈራልም።

'ላ..እ?'

ተርበተበትኩ ሐሳቤ ዘፈኑ ላይ ነበር።
'እየተከተልከኝ ነበር ወይ?' ደግማ ጠየቀችኝ።
'እረ አይደለም።' መንገድሽ መንገዴ ለለነበር ነው' ብዬ ዋሸኋት።" ገጽ 84-85

[ገ] "Minimalist fictions often straddles the boundary between prose and poetry, primarily because it is laconic yet highly implicative . . . Minimalist works often achieve a level of profundity generally associated with verses. The reason for this is that both forms necessarily omit relevant information as a means to create a heightened sense of implication." *American Literary Minimalism*, Robert C. Clark, 2011, p7

በዚህ ምልልስ ውስጥ ደራሲው ሳይነግረን የተረ ዝሙ መዘርዝር ያለ ቢሆንም ራሳችን እንድንረዳ ታሳቢንና እንባባቸውን መርሆ አስተምሮልናል። ለምሳሌ 'ዲ' ን እንዲያናግራት ፈልጋለች። ምናልባትም ኤርፎኗ ውስጥ ሙዚቃ የለም። ድምፆን የሚያምርም የሚያስፈራም አድርጋሞለች። በሁለቱ መሐል የተቃርኖ መሳሳብ እንዳለ ግንም እንባቢ ሳይነገረው ያውቃል።

"ገሸሽ መጀ ያማል? ደፍሰ መጀ ይገድላል? የሚያመው መናር ነው። የሚያመው ሕይወት ነውን?" ገጽ 122

ይህ የአጻጻፍ ስልት በአብዛኛው Pessimism እና ገዘን ያጠላበት ተረክ የሚተረክበት እንደሆነ ይነገራል። የአሱባለው አበራ ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለለንጅ ም ይሄ ስሜት ያጠላበት ሥራ ይመስላል።

4. Flash fiction:

የአጭር አጭር ልብ ወለድ። እነዚህ ለገጸባሕርይ እድገት (developmenet) ጊዜ የማይሰጡ በጣም ፈጣን ተረኮች ሲሆኑ ገጸባሕርዩው በአንድ የተወሰነ ሁኔታ (scenario) ውስጥ በመክተት ለሁኔታው የሚሰጠውን ግብረመልስ ይተርካሉ።[80] በጣም አጭር በመሆናቸው በኢሜል ወይም በሌላ የመልእክት አውታር መላክ ሁሉ ይቻላል።

[80] "In short short stories, there is little space to develop a character. Rather, the element of plot is central: a crisis occurs, and a sketched-in character simply has to react. Authors deploy clever narrative or linguistic patterns; in some cases, the short short resembles a prose poem." *Outline of American Literature, Kathryn VanSpanckeren, 1994, p139*

ደራሲው በተለይ በእንጀራ እምስት ("ጽጠኝ ምም ገጽ 40) ላይ እንደዚህ ዓይነት ቴክኒክ ተጠቅሟል። ተረኩ ከመጀመሩ በቅጽበት የሚያልቅ በመሆኑ እንጀራነቱ ካሲኖ[81] ነው ወደ ማለት ሊያደርሰን ይችላል።

5. Writing Degree Zero:

ቀለል ባለ አገላለጽ ደራሲው በገጸባሕርያት ሕይወትና አስተሳሰብ፣ እነሱ በሚወክሉት የማኅበረሰብ አካል ባህል እና ትውፊት ተጽዕኖ ሳይደርስበት እንዲሁም ቀድም በነበረው የሥነ ጽሑፍ ልማድና ሕግ ሳይገታ ገለልተኛ በሆነ መንገድ የሚተርክበት የተረክ ሂደት *Writing degree zero* ይባላል።[82]

ይህ አጻጻፍ በተለይ በድሕረ ዘመናዊው ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ነው። እንደምሳሌ የCamusን *'Outsider'* ማንሣት እንችላለን። እንደዚህ ዓይነት አጻጻፍ በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለለንጅ ላይም ይታያል።

[81] ትንሽ እንጀራ፡ ምጣድ ሲሶግ መጀመሪያ የሚጋገር

[82] "The new neutral writing takes its place in the midst of all those ejaculations and judgments, without becoming involved in any of them; it consists of precisely in their absence. But this absence is complete, it implies no refuge, no secret: one cannot therefore say that it is an impassive mode of writing; rather, that it is innocent. The aim ...is to go beyond Literature by entrusting one's fate to a sort of basic speech, equally far from living languages and from literary language proper." *Writing Degree Zero, Roland Barthes, 1968*

በእንጀራ አምስት "የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች" (ገጽ 32) እንዲሁም በእንጀራ አሥራ አንድ "መለየት" (ገጽ 90) ይሄ ቴክኒክ ጎልቶ ይስተዋላል።

መ. ፍልስፍና፡

በድሕረ ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ እጅግ ጎልቶ የሚወጣው አጠቃላዩ የሰው ልጆች ሁኔታ (The Human condition) ሲሆን በቅናነት የሚገለባረቁት ኤግዚስቴንሽያሊዝም (Existentialism) እና አብዝርዲዝም (Absurdism) ይመስለኛል። የዚህ ሥነ ጽሑፍ ጀግሮች እነCamus፣ Beckett፣ Burroughs፣ Hemingway እንዲሁም ከነእርሱ በኋላ የመጡት እነJoseph Heller፣ Kurt Vonnegut፣ Milan Kundera፣ Salman Rushdie ወዘተ ኤግዚስቴንሽያሊስቶችና አብዝርዲስቶች ናቸው።

በእሱባለው አበራ የተጻፈው ይሄ ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለእንጀ ም በእነዚህ ፍልስፍናዎች ጥላ ሥር የሚያርፍ ነው። ከመጽሐፉ ገጾች እየገለጥን በጥቂቱ እንኳን ብናይ፡

ደራሲው በእንጀራ አምስት "ዘጠኝ ሞት" (ገጽ 50) ላይ እንዲህ ይተርከልናል።

"ከተወለድኩበት ቀን ለንሥቶ በተሳሳተ ዓለም እንደ ተፈጠርኩ ይሰማኝ ነበር። የልጅነት ሕልሜ በወጣትነት መምታ ነበር። ጉርምስና ላይቀርምና— በቀጠሮው መጣ። እኔ ግን ሳልምት በሕይወት ቆየሁ። ለምን?"

ይሄን ተረክ ስናነብ መሠረታዊ ጥያቄ እንድንጠይቅ ይጋብዘናል። 'ሰው ለምን መሞት ይፈልጋል?' ወይም 'ሰው ለምን ራሱን ያጠፋል?' ወይም ደግሞ 'ሰው ለምን ይኖራል?'

ደራሲው ራሱ ". . . ለማችንም ምታችንም ትርጉም የለውም። ለለዚህ ለምን ለንምታለን? ለምንስ እንኖራለን?. . ."(ገጽ 55-56) እያለ ይጠይቀናል።

ለዚህ ኑረታዊ (Existential) ጥያቄ አልበርት ካምዩ የሚከተለውን የአብዝርዲዝም ትርጉምና መልስ ያስቀምጣል።

"Absurdism emanates from the dissonance between man's natural desire to find meaning in his life and the impossibility of finding that meaning in any rational way. The absurdity doesn't lie in a logical contradiction but in an existential contradiction; it is the primary puzzle of human existence. We long for meaning but we can't get it."[53]

Daniel Klein ደግሞ ከላይ ያለውን እንዳለ ያስተምተና የሚከተለውን ከCamus አሳጥሮ ይጽፋል።

"There are three basic responses to confronting this absurdity:

1. commit suicide

2. take a leap of faith to belief in God

3. accept the absurdity of it all but carry on anyhow."[54]

በእሱባለው መጽሐፍ ውስጥ ይህ ትርጉም የመሻትና ትርጉም ፍለጋ የመባዘን ይታያል። ትርጉም ሳይገኝ ሲቀር ደግሞ ሞት ምርጫ ሊሆን እናያለን። ለምሳሌ በእንጀራ አምስት "የመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች" (ገጽ 32) 'ጸ' የተባለው ገጸባሕርይ እንደዚህ ይላል፡

---

[53] The myth of Sisyphus, Albert Camus

[54] Every Time I Find the Meaning of Life, They Change It, Daniel Klein, 2015

". . . እንደ በለስ የበለስ ፍሬ የምት እጅ ላይ ሰለመውደቅ አስባለሁ። ገላ እንዲህ ይከብዳል? እያልኩ እጠይቃለሁ። ከገዛ ገላዬ በጽኑ ማረፍና መገላገል ፈልጌያለሁ። ምቱን 'አሁን' እንደሚመጣ እያወቅኩት ነው ለምታው የምሸው። ለመጣጡ ለያስደንግጠኝም። ድንገት ሳላስበው ለልደረስብኝም። ሄጀ ጠራሁት እንጂ መጥቶ ለልጠራኝም። ጉቃና ውሰደኝ ለልኩት እንጂ ተንሣና እንሂድ ለላለኝም. . ."

"ሁሉም ሰው የራሱን ምት እንደሚምት አውቃለሁና— የገዛ ምቱን ለልፈራም. . ." (ገጽ 53)

ከዚህ ሌላ ደግሞ በእንጂራ አሥራ አንድ "መለያየት" በተተረከው ተረክ ውስጥ የሞራልና ኢቲክስ ጥያቄ የሆነውን መሠረታዊ የግለሰብ ማንነት ጥያቄ ያጠይቃል።

'በመሠረታዊነት ሰው ክፉ ነውን'፣ 'ክፉነት፣ ወንጀለኛነት፣ መኖር ባሕርይስ የሚወረስ፣ ከውልደት እስከሞት የሚቆይ ባሕርይ ነውን' ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል።

'ሰውስ ባሕርዩው የሚቀየር ከሆነ አምና በፈጸመው ዘንድሮ ሊጠየቅ ይገባዋል ወይ?'፣ 'ተጸጽቶ ካመነ ሰውን መቅጣትስ ተገቢ ነውን?' እያልን እንድናብሰለስል ይገፋፋናል። በዚያውም እንግሊዛዊውን ፈላስፋ Derek Parfitን እንድናስታውስ ያደርገናል። Parfit አነጋጋሪ በሆነው የሞራል ፍልስፍናው ይታወቃል።

"People deserve much less punishment, or even perhaps no punishment, for what they did many years ago as compared to with what they did very recently."[85]

[85] *Reasons and Persons, Derek Parfit*

ሠ. ገለጻዎች፣ የቃላት አጣጣልና ተምሳሌት፡

ደራሲው በዚህ መጽሐፉ ከላይ በትርጽ እንደገለጽነው ለቃላት አጠቃቀም፣ ገለጻዎቹና ተምሳሌቶች (Symbols) ከፍተኛ ትኩረት ሰጠቀ ያስታውቃል። ገጽ በገጽ የምናገኛቸው እገላለጾች ብቻቸውን እንደ maxim ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው። ከእሁን በፊት የማናውቃቸውን ገላጭ ሐረጎችንም ተጠቅሟል። እያንጻንዱን ገለጻ ለእስረጅነት መጥቀስ ገጽ ማባከን ይሆናልና ስለመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ብቻ እናወራ።

"ከመስከረም መር በፀሐያማ ቀን ከሰማይ ማገፀገ ለንዲት የዝናብ ጠለላ ተምጣ ተወልዳ ነበር።" (ገጽ 5)

ደራሲው ስለዚች መግቢያ ዓረፍተ ነገር ተቀምጦ እንዳሰላሰለ፣ ብዙ እገደሰረዘ እና እንደተጨነቀ አስባለሁ።[86]

ዓረፍተነገሩ ተቃርኖን ባዘለ አንድ የጊዜ ነቁጥ ላይ የተፈጠረ፣ የማይለተዋል (significant የማይመለል) የድርጊት አሐድ ነው። የመግቢያውን ዓረፍተነገር ስናነብ ስለምን እናስባለን?

[86] *"Beginnings are the hardest: the beginning of a sentence, of a paragraph, of a section, of a stanza, of a whole piece. This is when you spend the most time not writing; sitting, staring off into space, chewing the pencil, furrowing your brow, feeling stuck. How can you write the beginning of something till you know what it's the beginning of? Till you know what it's leading upto? But how can you know that till you get your beginnings?" Writing without teachers, Peter Elbow*

ደራሲው ሥነልቦናዊ የሆነ የሕይወት ክፍል (existence) ሊያጠፉት በተቃናና በነባ እንድ እውነታ ሊደግሙ እነደማይችሉ እናያለን።

ይህንና ምስል በመከለት ደረጃ ደራሲው እዲስ ነገነት ገላጭ ሐረጉትና ምስል ከነች ማብራሪያዎችን ተጠቅሚል። ለምሳሌ በገጽ ፻፯ የዮዮርከውን የመልክ ሞት ምስል መጥቀስ እንችላለን።

ተምሳሌትን (symbolism) በተመለከተ 'ፕ' የተባለው ገጸባሕርይ ከሞተ በኋላ ወዳጂቹ ዓለም ውስጥ እንደተወርዋሪ ኮከብ ሲከሰት እናስተውላለን። እጅግ ግራኒ የሆነ የተረከ አቀራረብ ይመስለኛል። ነገር ግን እገዛዚ እንዲመራመርና በመሥመር መሐል እንዲያነብ ያስፈልጋል። Milan Kundera እንደሚለው "A reader's imagination completes a writer's vision." [፵]

ረ. እንግዳ ገጸ ባሕርያትና ድርጊቶች፡

ትጀታሽን ለለኔ፣ ትዝታዩ ለለንጅ ውስጥ የሚስተዋሉ እንግዳ የሆኑ ገጸባሕርያትና ድርጊቶች አሉ። እነዚህ የልብወለድ ባሕርያት (features) እንደነ የG. G. Marquez 'One Hundred Years of Solitude'፣ የአጻም ረታ 'ከሰግይ የወረደ ፍርፍር' ዓይነት ልብወለዶች ውስጥ የምናየው ማጂካል ሪያሊዝም (Magical Realism) ውስጥ የምናያቸው ናቸው። ደራሲው በዚህ ሥራው ውስጥ እየመጠ ስሏቸዋል። ለምሳሌ በእንጂራ ሁለት "መጺናና ዘለሰኛ" በተሰኘው ምዕራፍ ውስጥ በተቃርና የተሰናሰሉ ልዕለሰብ እና ተራ ሰው እናያለን። ከሁለቱ የመጀመሪያው በእውን ያልተለመደና በመጽሐፉ ሌላ ክፍል እንደመገፈለ ሲሠመር የምናየው ነው። *(ገጽ 69)*

[፵] The Art of the Novel, Milan Kundera, 1992

ለብወለዱ እንግዳ የሆኑ ክስተቶችንም ይዟል። ለምሳሌ በገጽ ፻፱ እንዲህ ይለናል፣

"ፈረሱን ኪጋማው ለሥርት መደቢት ለቀና። አንዲት እንደ እሳት ሮታበራ ለደይ ለበባ ለውጥቶ በገዘምታ ሰጥቶኝ ወደውሰተ ዘለቀ። እንባ ተደመኝ። በጊዘው ያስደንገጠኝ ነገር የአርሱ የቀኝ እጅ በእሳት መብለቡ ነበር። የለበሰው ሸማ ሚዩ ሚቶ እንደግለኛ ጨርቅ ተያየኋለ። ያቺ የእሳት ነበልባል የጉረሰች ለደይ ለበባ እርጅና ሳያኸት ባሪም መጻዩ ውስጥ በምሥጢር እያበራች ተቀምጣለች።"

ሌላም ደግሞ፣

"ምስኩቱን መጋረጃ ገለጥ ለድርጌ ከፈትኩት። ወደ ውጪ ብመለከት እንድ ነገር የግቢዩ መሐል ላይ ተንትር ቆሚለ። ደንግጬ ተረሁ። ጠፈትኩት መስኩት በነፋስ እየተወዛወዘ ከለቢ ጋር ይመታል። የተነተረው መልአክ ነበር። ጨለማ ከገርቹ እየር ላይ ከፍ ብለው ይርገበገባሉ። በለንድ እጁ ሰይፍ በሌላው ደግሞ ሰልቻ ይዟል።" *(ገጽ 112-113)*

ሰ. ድንገተኛ መግለጦች

(Instant Realizations) :

ድንገተኛ መግለጦች የእውነተኛ ዓለም ክስተቶች ናቸው። በልብወለድ ድርሰት ውስጥ ድንገት ሲከሰቱ መሠረታዊ የሆነ የተረከ frame የሚቀይሩ ክስተቶች ናቸው። ደራሲው እነዚህን በማሠሪያ ያልተጀጉ ንዑስ ክስተቶች እንደግብዓትነት መጠቀሙ መልካም ነገር ነው ብዩ አምናለሁ።

ለምሳሌ፡ "... በዚያን ቅጽበት በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ በሥጋ የተደፈነች ነፍሴን ሀልዎት ተጠራጠርኩኝ። ነፍሴ ኮብልላ ሰትጠፋ፥ በቀሜ ለምት፥ አለመኖር ሊወርሰኝና ከውስጤ አንዳች ነገር ሊጎድል ተሰማኝ። የማላውቀው ትላንቴን ወይ ገና ያላየሁት ነገዬን እገዳደበላሽብኝ ፈራሁ።" (ገጽ 29-30)

ሸ. ትዝታ (Nostalgia)፡

በትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ደራሲው ስለትዝታ ብዙ ይቆዝማል።

ከአርእስቱ ጀምሮ በግባያዎቹና በእንጀራዎቹ ውስጥ በትዝታ ይመሰጣል። በአጠቃላይ በትዝታ የታሸ ተረክ ነው ብንል ሰው አይታዘበንም። ለመሆኑ ግን ትዝታ ምንድነው? ትዝታ አንድ ትርጉም በቀላሉ ለመስጠት የሚሰቸገር ረቂቅ (Abstract) ፅንሰ ሐሳብ ነው።

ትናንትና ጥሎ ዛሬን ተንተርሶ

ከነገም ተውሶ ለምናንም ለድሶ

ይመጣል ትዝታ ጓዙን ለማበስብሶ[88]

እንዲል ዘፋኝ ትዝታ የጥንቱን በማስታወስ ቃኝቶ፣ መጪውን በሐሳብ ጓውሮ ለባለቤቱ መቆዘሚያ የሚሆን ማምሻ መክሰስ ነውና ያስቆዝማል። ብዙ የተጻፈ ነገር ባንመረምርም ትዝታ ለመተርጎም ከሞከሩት አንዱ በመጣጥፉ እንዲህ ይለናል።

[88] ትዝታ፣ ማሞ፡ድ ለሠሚድ

"In Amharic, the word 'tizita' has three related meanings. It can mean, in the first place, memory and the act of memory. Some dictionaries parenthetically add nostalgia, or the memory loss and longing— and nostalgia certainly evokes the world's attendant mood, its melancholy, discernible in the way Amharic speakers employ it even in their most quotidian exchange. Secondly, tizita refers to one of the scales or modes in secular Ethiopian music, one that conjures up in sonic terms the word's dictionary meaning. Thirdly, and incorporating the two, tizita refers to a signature ballad in the Amharic songbook, which always lack takes the form of an expression of loss."[89]

የአባባው መጽሐፍ በናፍቆት መታምም፣ ማዘንና መደሰትን የያዘ ከትውስታ የሚቀዳ ተረክ የያዘ የትዝታ አንገር ነው።

[89] Tizita: The new world interpretation, Degmawi Woubshet

ለንደ መውጫ፡

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለለንቺ መጣር ሐሳብችና ቴክኒኮችን የያዘ ሥራ መሆኑ ባያጠያይቅም በገጽ ብዛቱ ትንሽ በመሆኑ እንባቢ እያጣፈጠው ሲጨርስ መከፋቱ አይቀርም። ደራሲው የመጽሐፍ ዕድሜ የገደቡ ብዛት እንደሆነ የሚያምን ቢሆንም እንደዋና ገጸባሕርዩው (protagonist) መጽሐፉም በለጋ ዕድሜው እንደተቀጨ እንዲሰማንና እንድናዝን አድርጓል። በእርግጥ አሟር ሰውን አሟር ነው ተብሎ ሰው እያደለዘም አያባልም። አንድን ተረክም በደራሲው እያታ ካለቀ በኋላ ማሰረዘም አያቻልም።

ትዝታሽን ለእኔ፣ ትዝታዬ ለአንቺ ለአገራችን ሥነ ጽሑፍ አዳዲስ ነገር ያዩ በመምጣት የራሱን ቦታ የሚያገ ሥራ ነው። በዚህም ተግለጭ በሚመጡ ሥራዎች ላይ የራሱን ተጽዕኖ የሚያሳርፍና ሥራ እንደሚሆን አስባለሁ።

ደራሲው እሱባለሙ አበራ ለሥነ ጽሑፍ የሚሰጠውን ክፍ ያለ ቅርንም አሳይቶናል። በዚህ ሥራውም ላይ በእጅጉ እንደ ደከመበት እንባቢ የሚረዳው እውነት ይመስለኛል።

በቀጣይ ሥራዎቹ በዚህኛው መጽሐፉ ተንሥተው ያልጎለበቱ ሐሳቦችንና ደራሲው መጠቀም እየቻለ ያባከናቸውን ቴክኒኮች (ለምሳሌ intertextuality) የበለጠ በመጠቀም የሚያጠግብ ሥራ ያመራል የሚል እምነት አለኝ።